


የታማኝነትና ታማኝ አለመሆን
ርዕሶች
አባቶች
እና
ታማኝነት
አባቴ አባቴ
ዳግ ሂዋርድ ሚሊስ



የታማኝነትና ታማኝ አለመሆን
ርዕሶች
አባቶች
እና
ታማኝነት
አባቴ አባቴ
ትርጉም :- ፈቃዱ ገብሬ
አርትዖት :- መጋቢ ዘላለም ቸርነት
ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

ካልተገለፀ በቀር፣ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መፅሐፍ ቅዱስ ነው።


Email Dag Heward-Mills:
bishop@daghewrdmills.org
evangelist@daghewardmills.org

Find out more about Dag Heward-Mills at:
www. daghewardmills.org
www. lighthousechapel.org
www.healingjesuscrusade.org

Write to:
Dag Heward-Mills
P.o.Box 114
Korle-Bu
Accra
Ghana

ላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል
ስልክ +251912063821
መ.ሳ ቁጥር 15134
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ



ይህንን መፅሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያላሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከተለ ነው።


## ማውጫ


1. አባትን ማወቅ ... 1
2. በሕይወት የተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ አባቶችን እንዴት ማወቅና መቀበል እንደሚቻል ... 5
3. አስር ዓይነት አባቶች ... 11
4. ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉባቸው ሰባት ምክንያቶች ... 19
5. ችግሮችን የወረሱ ልጆች ... 25
6. የእውነተኛ ልጅ ሰባት ምልክቶች ... 31
7. አራት ዓይነት ልጆች ... 39
8. አደገኞች ልጆች ... 45
9. አርቀው የማያዩ ልጆች ... 75
10. አባቶችን በማክበር የሚገኙ ሦስት ሽልማቶች ... 83
11. ሰባት የአባት ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሎች ... 91
12. አባቶች እንዴት ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ምክንያት እንደሚሆኑ ... 103
13. አራት የአባት ምልክቶች ... 111
14. ልጅ "አሉስ" መሆን የሚገባው ሃያ ምክንያቶች ... 115
15. አንዳንድ ልጆች አባትን ማክበር ለምን እንደሚከብዳቸው ... 137

*ምዕራፍ 1*

# አባትን ማወቅ

በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጃአችኋለሁና።

1 ቆሮንቶስ 4፡15

"የአባትነት" ስጦታ ከስንት አንዴ የሚገኝ ስጦታ ነው፡፡ ሁሉም የእግዚአብሔር ሰው  አባት ሊሆን አይችልም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር ሁሉ አባት አይሆንም፡፡ ሁሉም ተጋባዥ አስተማሪዎችና ሰባኪዎችም  አባት አይሆኑም፡፡

ነቢይ ሁሉ አባት አይሆንም፤ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች ያመለከታቸው ይህን ነው፡፡

## አባት በቀላሉ የማይገኝ ስጦታ ነው

በሕይወትህ ውስጥ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ብዙመካሪዎችና አስተማሪዎች ሊኖሩ ቢችሉም ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ከአባቶች ይለያሉ፡፡ የአባት ግብአት ሁሉን የሚጠቀልል ነው፡፡ አባት ከመልካም ትምህርት የሚያልፍ ሙሉ ትጥቅ ይሰጥሃል፡፡ አስተማሪ ኃላፊነቱ መልካም ትምህርት መስጠት ነው፡፡ ነቢይ ደግሞ የእግዚአብሔርን ኃይል  በራእዮች፣ በሕልሞችና በእውቀት ቃሎች የሚያገለግል ሰው ነው፡፡ ነገር ግን አባት ለመላው ደህንነትህ ግድ የሚለው ነው፡፡

አባትነት ብዙ ነገሮችን ስለሚያጠቃልል ብዙ አባቶች የሉም! የተዘጋጁ ማስታወሻዎችን መሰረት በማድረግ ማስተማር ሙሉ

ክትትልን ከማድረግ ይልቅ ይቀላል። ሰዎች በጣም አስቸጋሪዎችና ምስጋናቢሶች ሊሆኑ ስለሚችሉ ሰዎችን ለዘለቄታ ሊሸከሙ የሚችሉ አባቶች ብቻ ናቸው።

እጅግ የበዙ መጋቢዎች፣ ወንጌላውያንና ነቢያት አሉ፣ ነገር ግን አባት የሚሆን ነቢይን-ማን ሊያገኝ ይችላል? ጳውሎስ "አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ፣ ብዙ አባቶች የሉአችሁም" ያለው ለዚህ ነው።

የአንድ አባት ልዩ ባሕርይ ዕድሜው ሳይሆን እርሱን መሰል ተከታዮች የማፍራት ችሎታው ነው። ምንም እንኳ ከአንዳንድ ሰዎች አስተያየት ጋር ቢጣረስም፣ የአባት ልብ ያላቸው ብዙ ወጣቶች ግን አሉ።

በተፈጥሮአዊው አካሄድ ሰዎች አባቶች የሚሆኑት በወጣትነት ዕድሜአቸው ነው። የአባትነት ማረጋገጫ፣ አባት በወለዳቸው ልጆች ውስጥ ይገኛል። ልጆችን ማሳደግ፣ ፍቅርን ራስን መስጠትና ትዕግሥትን ይጠይቃል። በመጨረሻም ልጆች የአንተን አባትነት ይመሰክራሉ።

ለምሳሌ የኤልያስንና የኤልሳዕን አገልግሎት ብታወዳድር፣ በአባታዊ ነቢይነትና አባታዊ ባልሆነ ነቢይነት መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ትችላለህ። እነዚህ ልዩነቶች፣ አገልግሎቶቻቸውን ስትመረምር በሚገባ ግልጽ ይሆናሉ። የኤልያስንና የኤልሳዕን አገልግሎቶች ስታወዳድር የአባት ልብ ባለውና በሌለው ሰው መካከል ያለውን ልዩነት በቀላሉ ማየት ትችላለህ።

ሁለቱም ኤልያስና ኤልሳዕ የተዋጣላቸው ነቢያት ነበሩ። ነገር ግን ኤልያስ አባት የመሆን ተጨማሪ ስጦታ ነበረው። ተተኪ ያገኘው ለዚህ ነበር። ኤልሳዕ ግን ተተኪ አልነበረውም። የእርሱን ፈለግ በመከተል እርሱን መተካት የሚችለውን ግያዝን ረግሞታል። ግያዝን የረገመው የንዋይ ስሕተት በመፈጸሙ ነበር። የአባት ልብ ብቸኛ ልጁን አይረግምም።





የእግዚአብሔር ሰው እርሱን የመሰለ ሰው እንዲያፈራ ሊያደርገው የሚችል የአባትነት መንፈስ ነው። በግልጽ ቋንቋ ሲነገር የአባትነት ስጦታ የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጫ ነው። የሚደረግላቸውን ነገር በሚገባ የማያውቁ ሰዎችን ማሳደግ ፍቅርን ይጠይቃል።

ለብዙ ዓመታት የማይረዱህን ሰዎች ማሳደግ ፍቅርን ይጠይቃል። እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚያገለግሉ በርካታ አስተማሪዎችን ይልክልናል። እነዚህ ሰዎች ትምህርቶችንና አስተምህሮን የሚመለከቱ ነጥቦችን በመስጠት ያገለግላሉ። ነገር ግን አባት ከእነዚህ በላይ ብዙ እርምጃዎችን አልፎ ይሄዳል። *ከማስተማር በተጨማሪ፣ አንተን ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ የሚያመጣውን ፍቅርና ትዕግሥት በማሳየት ያገለግላል።*

በአንድ አገልጋይ ውስጥ ያለ የምሉዕነት ባሕርይ ሁልጊዜም ፍጹምነትን እንዲፈልግ ያደርገዋል። ምሉዓንና ፍጹማውያን ብዙ ጊዜ ጥሩ አባቶች አይደሉም። በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ጸጋ በእርጋታ እየሠራ መሆኑን በአድናቆት አይቀበሉም። ሁልጊዜ በሰዎች ዘንድ የማይቻለውን ፍጹምነት እንዲመጣ ይጎተጉታሉ።

አንድን የእግዚአብሔር ሰው እንደ አስተማሪ ልትቀበል ትችላለህ። እንደ መጋቢም ልትቀበለው ትችላለህ። የእግዚአብሔርን ሰው እንደ ነቢይ ወይም እንደ ወንጌላዊ ልትቀበለው ትችላለህ። እንደ አባትም መቀበል የሚቻል ነው።

ለሕይወትህ አባት ለማግኘት የታደልህ ያድርግህ! አንተ ራስህም አባት ለመሆን የሚያስችልህን ችሎታ ለመቀበልም ያብቃህ!

## ምዕራፍ 2

# በሕይወት የተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ አባቶችን እንዴት ማወቅና መቀበል እንደሚቻል

**እግዚአብሔር የተለያዩ አባቶችን በተለያዩ ጊዜያት ይልክልሃል።**

በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ፣ ብዙ አባቶች የሉአችሁም፡ እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና።

1 ቆሮንቶስ 4፡15

እግዚአብሔር አባት እንዲሆኑህ ብዙ ሰዎችን ይልክልሃል። ከእነዚህ የመጀመሪያው በአግባቡ ልትይዘው የሚገባህ ምድራዊው አባትህ ነው። ምድራዊ አባትህ ከዘመናዊ ሕይወት ጋር ምንም ትውውቅ የሌለው "ዘመን ያለፈበት" ሰው አድርገህ መቁጠር አይገባህም።

የወለደህን አባት ዘመን ያለፈበት አድርገህ ከቆጠርህ፣ ከእርሱ ዘንድ ለምትቀበለው ታላቅ ጥበብ እንቅፋት ይሆንብሃል።

ወላጅ አባትህ በአባትነት ሚናው አንዳንድ እጥረቶች ሊኖሩት ይችላል። ይሁንና ብዙም ሳይቆይ ቅብብሎሹ ይጀምርና ለአንተ አባት የሚሆንህ ሰው ቀጥሎ ይመጣል። በቀጣዩ የሕይወት ደረጃ ለማለፍ የሚያስፈልግህን አባታዊ ክብካቤ ከዚህ ሰው አገልግሎት ትቀበላለህ። እንደዚሁም በሕይወትህ አባታዊ ሚና የሚጫወት ሌላ ሰውም ሊነሣ ይችላል። እንዲህ ያለ ቅብብሎሽ ሒደቱ ይቀጥላል! የአባትነት ዱላ ቅብብሎሹ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላኛው ሰው ይተላለፋል።

ወላጅ አባትህ ለአንተ የማይነግርህ ብዙ ነገሮች አሉ። ምናልባት ሁሉንም ነገር መንገር የሚገባው ቢሆንም፣ አይነግርህም። ለብዙዎቻችን ወላጆቻችን ሚስትን ወይም ባልን ለመምረጥ

የሚያስፈልጉ ደረጃ የጠበቁ ምክሮችን አልሰጡንም። አብዛኞቹ ወላጅ አባቶች በጋብቻ ውስጥ ስለሚነሡ የተለያዩ ጉዳዮች አስተያየቶችን ብቻይሰጣሉ።

ይህ እንግዲህ የጋብቻ ምክራቸውን በተመለከተ ያለ እውነታ ነው። ኃላፊነትን በመውሰድ ልጆችን ወደ ጋብቻ ስለሚመሩ መጋቢያን እግዚአብሔር ይመስገን። ስለዚህ በቅብብሎሹ መጋቢያን ቀጣይ አባት ይሆናሉ።

አንድ ቀን ሴት ልጄ፣ "አባባ፣ ሰዎች ነፍሰጡር የሚሆኑት እንዴት ነው?" ስትል ጥያቄ ጠየቀችኝ።

በጥያቄው ድንጋጤ ቢይዘኝም፣ "እግዚአብሔር ነፍሰጡር እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል" በማለት መለስሁላት።

ነገር ግን እርሷ አልለቅ በማለት፣ "እግዚአብሔር እንዲያረግዙ እንደሚያደርግ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ይህ የሚሆነው እንዴት ነው?" አለች።

የሆነ መልስ ሰጠኋትና ርእሱ እንዲቀየር አደረግሁ። በኋላ ባለቤቴ፣ "ስለ ወሲብ ከልጆችህ ጋር መነጋገር አለብህ" አለችኝ።

እኔም፣ "ለምን ብዬ *አንቺ* ራስሽ አናግሪያቸው" ብዬ መልስሁኝ። ክርክር ተያያዝንና፣ "የቤቱ ራስ አንተ ነህ፣ ስለሆነም ልታናግራቸው የሚገባህ አንተ ነህ" አለችኝ።

እኔም፣ "ነገር ግን እናታቸው *አንቺ* ነሽ፣ ሁልጊዜም ቢሆን የምታናግሪያቸው አንቺ ነሽ፣ *ታዲያ*፣ ስለዚህስ ነጥብ ለምን አትነግሪያቸውም?" አልሁኝ።

እርሷም በመቀጠል፣ "ይህ የአንተ ግዴታ ነው፣ ሚናህን መጫወት ይገባሃል!" አለችኝ።

ነገር ግን እኔ ሳልስማማበት ቀረሁ። የቤት ራስነቴን ሥልጣን ተጠቀምሁና ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከልጆቹ ጋር እንድትነጋገር ወከልኋት።





እየሀ የአባትነትና የእናትነት ችሎታችን እየተንገዳገደ ወዳለበት ቦታ ላይ ደርሰናል። የሌሎችን ሰዎች ልጆች እንዳገለገልን እግዚአብሔር ልጆቻችንን እንዲያገለግሉ ሌሎችን እንዲልክ ተመኘን። በቅብብሎሹ፣ ቀጣይ አባት በመድረኩ ተገልጦ ልጆችን ወደ ደህና ደረጃ እንዲመራቸው መጸለያችንን ቀጠልን።

*በመቶዎች በሚቆጠሩ ምግዚቶችና አስተማሪዎች መካከል ማን አባት እንደሆነ ሁልጊዜም ማወቁ አስፈላጊ ነው።* አባቶች ለሕይወትህ በብዙ የሚያስቡ ናቸው። አስተዋጽኦዋቸውም ከንግግራቸው አልፎ ይሄዳል። አገልግሎታቸው ለጤናማነትህ ሙሉ የሆነ ክብካቤ እንደሚያደርግ ወደ ግንዛቤ ትደርሳለህ። አገልግሎታቸው ለሕይወትህ ምስጢራዊና ደርዘ-ሰፊ ውጤት አለው፡ ፡

አባትን የማወቂያ ቁልፎች ከሆኑት አንዱ የሰማዩ አባታችን ፍቅር፣ ክብካቤና ምሪት በዚያ ሰው ውስጥ እየተላለፈልህ መሆኑን መገንዘብ ነው።

ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ አስር ሺህ አስተማሪዎች እንዳሉ፣ ነገር ግን አንድ አባት ብቻ እንዳለ አድርገው ይገነዘቡታል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ግን ብዙ አባቶች እንደሌሉ ነው። በሌላ አባባል የአባቶች ቁጥር ጥቂት እንደሆነ ይናገራል።

> አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ።
>
> ማቴዎስ 23፡9

*ለዚህ ምክንያቱ ማንም ሥጋ ለባሽ አባት መሆን የሚገባውን ያህል በእውነት መሆን ስለማይችል ነው። ሁሉም ሰዎች ከዚህ ሚናቸው የጎደሉ ስለሆኑ፣የአባትን ምንነት የሚያሳይ የሰማዩ አባት ብቻ ነው።*

ምድራዊ አባቶች እንዴት ከልጆቻቸው ጋር እንደሚፎካከሩና እንደሚጣሉ አላየህም? ወላጅ አባቶች እንኳ በልጆቻቸው ላይ ብዙ ጉዳትና ሥቃይ ሊያደርሱ ይችላሉ።

ብዙ ሰዎች አባቶቻቸውን ይጠላሉ። በአባቶቻቸው ምክንያትም ሕይወታቸው የተዛባባቸው ብዙ ልጆች አሉ። ይህ የተፈጥሮአዊው ሰው አባትነት በጉድለቶች የተከበበ መሆኑን ያሳያል።

እኔ "የአባቶች ቅብብሎሽ"ብዬ የምጠራው አስፈላጊ የሚሆነው ለዚህ ነው።

ቅብብሎሹ እግዚአብሔር ለተለያዩ የሕይወትህ ደረጃዎችና አገልግሎትህ ተራ በተራ የተለያዩ ሰዎችን እንደሚልክ የሚያመለክት ነው። እነዚህ የተለያዩ ሰዎች ወደ ሕይወትህ የሚገቡበትን ጊዜ ለይተህ ማወቅ አስፈላጊ ነገር ነው።

ኢየሱስ በማቴዎስ 21 ላይ ባለው ምሳሌ የሚያስረዳው ይህንን ነው። በእርግጥ እኛም እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ለላካቸው አባቶች ላሳየነው አቀባበል ለፍርድ እንቆማለን።

> ሌላ ምሳሌ ስሙ። የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፣ መጥመቂያም ማሰለት፣ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። የሚያፈራበትም ጊዜ ሲቀርብ፣ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮቹን ወደ ገበሬዎች ላከ።
>
> ገበሬዎቹም ባሮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት፣ አንዱንም ገደሉት፣ ሌላውንም ወገሩት። ደግሞ ከፊተኞች የሚበዙ ሌሎች ባሮችን ላከ፣ እንዲሁም አደረጉባቸው።
>
> በኋላ ግን ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው። ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ እርስ በርሳቸው ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ። ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደሉት።
>
> ማቴዎስ 21፡33-39

እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ለይተን የማናውቃቸውን አባቶች ወደ ሕይወታችን ይልካል። ሰዎች ከአባቶቻቸውም ጋር እንኳ ይጣላሉ! እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን የሚልካቸውን አባቶች መቀበልን መማር ያስፈልገናል።





## አባትን በመቀበልና አስተማሪን በመቀበል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

አስተማሪን መቀበል ከእግዚአብሔር ቃል የሚያቀርበውን ትምህርት መቀበልን ያካትታል። አባትን መቀበል በሕይወትህ ሕይወት-ለዋጭ አገልግሎትን በሚያስከትል ሁኔታ አንድን ሰው መቀበል ማለት ነው።

በተፈጥሮ ወላጅ አባትህ በብዙ መንገዶች በአንተ ላይ ተጽእኖ አለው። እንዴት መብላት፣ መልበስና መኖር እንደሚገባህ ያስተምርሃል። እውቀትን፣ ምክርንና ለሕይወት የሚጠቅሙ አነስተኛ ትምህርቶችን እንኳ ይሰጥሃል።የምትከተለውን ምሳሌ በሕይወቱ ያሳይሃል፣ ለመነሣሣትህና ለአቅጣጫህ እንደ መሠረት ሆኖም ያገለግልሃል።

ይህን ሁኔታ ከትምህርት ቤት አስተማሪህ ጋር አወዳድር። የትምህርት ቤት አስተማሪዎች አባት እንደሚያደርገው በሁሉም ዘርፍ አይመሩህም። መሠረተ-ሰፊ የሆነ በጎ ተጽእኖ በሕይወትህ የሚያመጣ ሰውን ስታገኝ፣ ምናልባት እግዚአብሔር ለአንተ ከሾመልህ አባቶች አንዱን ሳትገናኝ አልቀረህም ማለት ነው።

## አባትን እንደ ተራ አስተማሪ የመቀበል ስሕተትን አትፈጽም

አንዳንድ ሰዎች አባቶቻቸውን እንደ ተራ አስተማሪ የመቀበል ስሕተትን ይፈጽማሉ። ይህን የሚያደርጉት ወደ እነርሱ የሚመጣውን አባታዊ አስተዋጽኦ ባለመቀበል ነው። የእነዚህን አባቶች ግብአት በከፊል ብቻ በመቀበል ብዙ ጊዜ የአባቶችን ሚና ወደ አስተማሪነት ሚና እናወርዳለን። እግዚአብሔር አባት እንድሆንላቸው የጠራኝ ሰዎች አሉ። ነገር ግን ከእነርሱ ጋር የማደርገው ግንኙነት የአስተማሪ ዓይነት ነው።ለዚህ ምክንያቱ እነርሱ የሚፈልጉት ይህን ስለሆነ ነው።

በማቴዎስ 21 ላይ የተጠቀሰው ምሳሌ፣ እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚልካቸውን ሰዎች ካደረግንላቸው አቀባበል አንፃር እንደሚፈርድብን በግልጽ ያሳያል። እግዚአብሔር ለእኔ የላካቸው አባቶች አሉኝ።

አንድ ቀን፣ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገር ጌታ በእርሱ በኩል በሚያመጣልኝ መልእክት እየረካሁ ነበር። ይህ ሰው እንዲህ አለ፣ "ይህን ሰው ለአንተ አባት አድርጌ ልኬልሃለሁ። ከአሁን ጀምሮ እንደ አባት እንድትቀበለው እፈልጋለሁ።" ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚያ ንግግሮች የተቀረጹባቸውን ቴፕ በተለየ መንገድ ማየት ጀመርሁ።

በዚህ አገልጋይ በኩል ለእኔ የተሰጡኝን ማናቸውንም ዓይነት አገልግሎቶች ለመቀበል ልቤን ከፈትሁ።

ከዚያም የዚህ ሰው መጻሕፍትና ሲዲዎች ለእኔ ከፍተኛ ፍላጎት ፈጠሩብኝ። መጀመሪያ ላይ ከትምህርቶቹ የሚያስደስቱኝ አንዳንዶቹ ነበሩ። አሁን ግን ሁሉንም ነገሮቹን እፈልጋለሁ። በዚህ ሰው አማካኝነት በአዲስ የአገልግሎት ደረጃ እንደምገለጥም አወቅሁ።

አንድን ሰው እንደ አስተማሪ ተቀብለህ ከዚያም እንደ አባት ለመቀበል ወደ ላይ ከፍ ማለት እንደምትችል ማወቅ የቻልሁት በትክክል በዚህ ጊዜ ነበር።



*ምዕራፍ 3*

# አስር ዓይነት አባቶች

## 1. የሰማዩ አባትህ

. . . አላቸውም፣ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤

ሉቃስ 11:2

አብዛኞቻችን የሰማዩ አባት ክርስቶስ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ ሁላችንን በእሳት የሚያነድ ቁጡ አምላክ አድርገን እናስባለን። ብዙ ጊዜ እንድንቃጠል አሁንም ይፈልጋል የሚል ስሜትም አለን።

እግዚአብሔር በሚያስደንቅ ፍቅር የተሞላ አምላክ ነው። የሰማዩ አባታችን ለእኛ ይጠነቀቃል። የኮብላዩን ልጅ ታሪክ ጠለቅ ብሎ መመልከት አባት ለኃጢአተኞች ልጆቹ ያለውን አቋም ያሳያል። እርሱ ይወደናል። ሺህ ጊዜ ኃጢአት ብናደርግ እንኳ እንደዚያም ሆኖ ይወደናል።

ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፣ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው። ልጁም፣ አባቴ ሆይ፣ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፣ ወደ ፊትም ልጅ ልባል አይገባኝም አለው። አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ። ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት፣ ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፣ እንብላም ደስም ይበለን፤

ሉቃስ 15:20-24

## 2. በክርስቶስ አባትህ

ይህ አንተን ወደ ጌታ ያመጣ ሰው ነው። ሕይወትህን ለክርስቶስ የሰጠኸውና ዳግም ተወልደህ ክርስቲያን የሆንኸው በእርሱ ወይም በእርሷ አማካኝነት ነው። እግዚአብሔር በጌታ የሚወልዱንን ሰዎች ወደ እኛ ይልካል። ሁልጊዜም እነዚህን ሰዎች ማስደሰትና ማክበር

ይገባናል። በእነርሱ ምክንያት አንድ ቀን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንገባለን።

## 3. መንፈሳዊ አባትህ

ይህ ሰው በመንፈሳዊ ነገሮች የሚያሠለጥንህ ሰው ነው። ወደ ክርስቶስ የሚመራህ ሰው በመንፈሳዊ ነገር እያሳደግህ ይሆናል። መንፈሳዊ አባትህ ከጌታ ጋር የጥሞና ጊዜ እንዲኖርህ ያሠለጥንሃል። መንፈሳዊ አባትህ መንፈሳዊ ጀግና እንድትሆን የሚያስችሉህን ልምምዶችን ያስተዋውቅሃል። መንፈሳዊ አባትህ ከሌሎች ክርስቲያን ጓደኞች ጋር ሊያስተዋውቅህ ይችላል። መንፈሳዊ አባትህ ጥሩ ቤተክርስቲያኖችንና ኅብረቶችን ሊያስተዋውቅህ ይችላል። መንፈሳዊ አባትህ ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሊጸልይልህ ይችላል። መንፈሳዊ አባትህ ለክርስቶስ ጸንተህ እንድትቆም የሚረዱ መሠረታዊ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ቃል ያስተምርሃል።

## 4. የአገልግሎት አባትህ

ብዙ ጊዜ የአገልግሎት አባቶች በክርስቶስ አባት ከሆኑትና ከመንፈሳዊ አባቶች ጋር ይምታታሉ። በአጠቃላይ ሰዎች የአገልግሎት አባቶችን እንደ መንፈሳዊ አባቶች ይቆጥራሉ። ነገር ግን በክርስቶስ አባት የሆነ ሰው ከአገልግሎት አባትና ከመንፈሳዊ አባት በጣም ይለያል። በክርስቶስ አባት የሚሆንህ ሰው አንተን በኢየሱስ ክርስቶስ ይወልድሃል፣ የአገልግሎት አባትህ ግን አንተን ለአገልግሎት ሥራ የሚያሳድግህ ሰው ነው።

በእነርሱ አማካኝነት ሕይወቴ ሙሉ በሙሉ የተለወጠባቸውን የእግዚአብሔር ሰዎች በመስጠት እግዚአብሔር በእጅጉ ባርኮኛል። በእነርሱ የአባትነት ጸጋ አማካኝነት መጋቢና አገልጋይ መሆን ችያለሁ። በቅርቡ ጌታ ወደሚቀጥለው የአገልግሎት ደረጃ እንድወጣ ያነሣሣኝን አባት በመላክ ባርኮኛል።





የአገልግሎት አባት ለጌታ አገልግሎት የወለደህ ሰው ነው። በእርሱ አማካኝነት በዓለም ውስጥ እጅግ ተፈላጊ በሆኑ ሥራዎች ትሳተፋለህ።

## 5. ወላጅ አባትህ

ይህ ከአብራኩ የተወለድህለት አባትህ ነው። ብዙ ጊዜ የአባትነትን እውቅና የሚያገኘው ይህ ሰው ነው። ይሁንና ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። ምክንያቱም ለአንተ አባት የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል እርሱ ብቻ አይደለም። ኢየሱስ፣ "ማንንም ሰው አባት ብላችሁ አትጥሩ" ያለው ለዚህ ነው። ኢየሱስ ማንም ምድራዊ አባት ብቻውን ለማንም አባት መሆን እንደማይችል ያውቅ ነበርና።

> አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ።
>
> ማቴዎስ 23፡9

እግዚአብሔር ለልጆቼ በተለያዩ የሕይወት ደረጃዎቻቸው የሚረዳ አባትን እንዲያመጣላቸው ሁልጊዜ እጸልያለሁ።

አንድ ቀን በአንድ መነቃቃት ፕሮግራም ላይ ለተወሰኑ ወጣቶች እጸልይ ነበር። በዚህ ጊዜ የጸለይሁላቸው ከሙሉ ልቤ ነበር።

ከዚያም፣ "ሴት ልጄ ሃያ አንድ ዓመት በሚሆናት ጊዜ የሚጸልይላት ሰው ይኖር ይሆን?" የሚል ሃሳብ አእምሮዬን ጠቅ አደረገው።

በሕይወታቸው የተለያዩ ደረጃዎች እንዲባረኩና ክብካቤ እንዲያገኙ እግዚአብሔር ወደ ልጆቼ ሕይወት ሰዎችን እንዲልክ ጸለይሁ።

## 6. ምትክ አባትህ

አንዳንድ ጊዜ ወላጅ አባቶች ስለሞቱ፣ ወይም ስለተፋቱ ወይም ልጆቻቸውን ስለተዉ ላይገኙ ይችላሉ። ብዙ ሰዎች ትክክለኛ ባልሆነ ቤት ውስጥ ስለሚያድጉ እግዚአብሔር የአባትነትን ሥራ የሚሠሩላቸውን ሰዎች ያስነሣላቸዋል።

አንድ ቀን፣ ከመጋቢዎቼ አንዱ በሆነው ሰው አስከሬን አጠገብ በሐዘን እንደተዋጥሁ ቆሜ ነበር። የባሏን አስከሬን እያየች እየተንፈረፈረች የምታለቅሰውን ሚስቱን ለማጽናናት በመሞከር ደግፌአት ቆሜ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ በሆስፒታሉ ዋርድ ውስጥ ከነበሩት ዶክተሮች አንዱ እንዲህ አለኝ። የተናገረውን ፈጽሞ አልረሳውም።

እንዲህ አለኝ፣ "አትዘን። ለምን ሞተ ብለህ እያሰብህ እንደሆንህ አውቃለሁ። እንዲህ ያለ ጥሩ ሰው ለምን አሁን ይለየናል እያልህ ይሆናል።"

ቀጠለና፣ "አየህ ሞት የሕይወት አንዱ አካል ነው። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሁሉ አናውቅም።"

ከዚያ ቀጥሎ የተናገረው ነበር ያስደነቀኝ፣ "አባቴ የሞተው እኔ በእናቴ ማኅፀን ውስጥ እያለሁ በሃያ አምስት ዓመቱ ነበር።"

ከዚያም፣ "ሁኔታው ለእናቴ በጣም አሳዛኝ ሆነ። እኔም አባቴን ፈጽሞ አይቼው አላውቅም።"

ቀጠለና፣ "ምናልባት ወላጅ አባቴ ኖሮ ቢሆን በዓለም የታወቅሁ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ መሆን አልችልም ነበር።"

ይህ ሰው በዓለም ደረጃ እውቅ ከሚባሉ የቀዶ ሕክምና ባለሙያዎች አንዱ ለመሆን የበቃ ሲሆን በአገሪቱ በሁሉም ስፍራ በጣም የተከበረ ሰው ነበር። ይህን ታላቅ ደረጃ የደረሰው በወላጅ አባቱ እርዳታ ሳይሆን ነገር ግን በ"ምትክ አባት" አማካኝነት ነበር።

ምትክ አባት የአንድ ሕፃን አባት በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ አባት በመሆን የሚያገለግል ሰው ነው። አንዳንድ ጊዜ ምትክ አባቶች ከወላጅ አባቶች የተሻሉ ናቸው። ከዚህ የምንማራቸው ሁለት ትምህርቶች አሉ፡

ለመሞት አትፍራ። እግዚአብሔር ልጆችህን ይከባከባቸዋል። ከአንተ እንኳ የተሻሉ ምትክ አባቶችን ሊያስነሣልህ ይችላል።





አንድን ልጅ በማደጎ ወይም የሌላ ሰውን ልጅ በመንከባከብ አባት የመሆን እድል ቢገጥምህ ፍቅርህን አትንፈገው። አባት ለሌለው ልጅ እግዚአብሔር ያስነሣህ ምትክ አባት ልትሆን ትችላለህ።

## 7. አማትህ

*ሙሴም፣ የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር። ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፣ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ።*

ዘጸአት 3፡1

አማትህ ሌላኛው ጠቃሚ ሰው ነው። ሙሴ በአማቱ በጣም ተባርኳል። በአማቱ አማካኝነት ጠቃሚ ምክር አግኝቷል።

የእኔ አማት ለእኔም በጣም ታላቅ በረከት ነበር። ከዕዳ ነፃ እንድወጣና ቤት እንድሠራ ያነሣሣኝ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ሕይወቴን ለመባረክ በእርግጥም አማቴን ተጠቅሟል። ለባለቤቴ እንዴት የተባረከ አባት እንዳላት ገልጬ የተናገርሁባቸው በርካታ ጊዜያት ናቸው።

## 8. የቤተክርስቲያን አባት

የቤተክርስቲያን አባት የቤተክርስቲያን መሥራች ሰው ነው። ለቤተክርስቲያን መወለድ ምክንያት ስለሆነ አባት ነው። ቤተክርስቲያን ወደ መኖር የመጣችው በእርሱ አገልግሎት አማካኝነት ነው። ይህ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች፣ "በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና" እንዳለው ነው።

በክርስቶስ እልፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም፤ እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና።

1 ቆሮንቶስ 4፡15

## 9. የንቅናቄ አባት

እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብራሃም ልጆች እንደሆኑ እወቁ።

ገላትያ 3፡7

በተጨማሪ የንቅናቄ አባቶችም አሉ። ለምሳሌ አብርሃም የእምነት አባት ተደርጎ ይታያል። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ለትውልዶች መወለድ ምክንያት እንደሆኑ ተደርጎ ይታወቃል።

ኬነት ሄገን የዘመናዊ እምነት እንቅስቃሴ አባት ተደርጎ ይታያል።

ጆን ዌዝሊ የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ንቅናቄ መሥራች ተደርጎ ይታወቃል።

አባቶች ልዩ ነገሮች ናቸው። ልጆች ከአባቶች የበለጡ ሥራዎችን ይሠሩ ይሆናል፣ ነገር ግን እንዲያም ሆኖ እንደ አባቶች አይታወቁም። ለምሳሌ ዛሬ በአገልግሎት ታላላቅ ፈዋሾችና መጋቢዎች አሉ፣ ነገር ግን አባቶች ሁልጊዜም አባቶች ሆነው ይታወቃሉ።

ኤልሳዕ ኤልያስ ካደረገው ሥራ የላቀ ሥራ ሠርቷል። የኤልሳዕ ታምራት ብዙ ጊዜ ከኤልያስ ታምራት በኃይለኝነታቸውና በቁጥራቸውም እጥፍ ነበሩ።

ኢያሱ ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት ችሏል። እርሱ ድል ያደረገው ሙሴ ለመግባት ያልቻለውን ምድር ነበር። የሙሴን ሕልም በታላቅ የኃይል መገለጥ ፈጽሟል። ነገር ግን ኤልሳዕም ሆነ ኢያሱ ምንም ዓይነት ተተኪ አልነበራቸውም። ታላላቅ አገልጋዮች ቢሆኑም አባቶች ግን አልነበሩም።

በመገለጥ ተራራ ላይ ኤልሳዕም ሆነ ኢያሱ ከኢየሱስ ጋር አብረው አልተገኙም። አባቶች በራእይ የተገለጡቱ ነበሩ።

አባቶች ለጌታ ልዩ መሆናቸውን አትርሳ። ወጣቶች በስኬቶቻቸው መታለል የለባቸውም። አንተ ከአባትህ ታላቅ ነኝ ብለህ አታስብ! ወንድና ሴት ልጆች የሚያደርጉት ነገር ቢኖር በአባቶች በተሰራው ላይ ጨምሮ መገንባት ነው።





## 10. በኃጢአት አባትህ የሆነ

በኃጢአት አባት የሚሆንህ ለመጀመሪያ ጊዜ አንተን ከኃጢአት ሕይወት ጋር የሚያስተዋውቅ ሰው ነው።

አንዳንዶቻችን እጆቻችንን ይዘው ወደ ክፋት የመሩን ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ የኃጢአትን ጥልቀት ፈጽሞ ማወቅ አንችልም ነበር። አንዳንዶቻችን የወሲብ ኃጢአትን ያስተማሩን ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ ስለ ዝሙት ፈጽሞ ማወቅ አንችልም ነበር።

## ምዕራፍ 4

# ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉባቸው ሰባት ምክንያቶች

አባትህን ስለምትነቅፍበት ነገርመጠንቀቅ አለብህ። ምክንያቱም አባትህን የተዋጉ መጥፎ ባሕርያት አንድ ቀን አንተንም ይዋጉሃል።

የሚጠብቁህ እስከምታድግ ብቻ ነው።

ወደድህም ጠላህም፣ አንድ ቀን፣ "የአባትህን መጥፎ ባሕርያት" መዋጋት የግድ ይሆንብሃል።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ አለኝ፣ "ሰዎች ጡረታ ሊያወጡኝ ይፈልጋሉ! በዚህ አገር ካለኝ ሥልጣን ሊያወርዱኝ ይፈልጋሉ። ብዙ ችግሮች እንዳሉብኝ አድርገውም ያስባሉ።"

ከዚያም ቀጥሎ የተናገረው አንድ ነገር በቀላሉ የማልረሳው ነበር፡ "እኔ ከሄድሁም በኋላ እኔን የተዋጋኝ 'ነገር' እነርሱንም ይዋጋቸዋል።"

ይህ ዘላለማዊ መርህ ስለሆነ ልብ ገዝቶ በፍጥነት መረዳቱ ጥበብ ነው። ብዙ ልጆች በአባቶቻቸው ፈለግ ተከትለው ሲሄዱ እነርሱ የሠሩትን ስሕተቶች ራሳቸው በመድገም የተናገሯቸውን ቃሎች ለመዋጥ ተገደዋል። ይህ ነገር በአብርሃም፣ በይስሐቅ፣ በያዕቆብ፣ በዳዊትና በሰሎሞን እንዴት እንደተፈጸመ ልብ በል።

አባቱን የሚነቅፍ ልጅ ብዙ ጊዜ የአባቱን ችግሮችና መጥፎ ባሕርያት ይወርሳል። መንቀፍ በብዙ ምክንያቶች ለተነቃፊው ችግሮች አጋልጦ ይሰጥሃል።

# ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉባቸው ሰባት ምክንያቶች

## 1. ችግሮች ከአባቶች ወደሚያጉረመርሙና ወደሚነቅፉ ልጆች ይተላለፋሉ።

ማጉረምረምና መንቀፍ ኃጢአት ናቸው፣ ኃጢአቶች ደግሞ ለክፉ መናፍስት በሮችን ይከፍታሉ።

ክፉ መናፍስት የሚሠሩት በኃጢአት ጨለማ ውስጥ ነው። አባቶቻቸውን የሚነቅፉ ልጆች አሉ፣ ለዚህ ድርጊታቸውም ከባድ ዋጋ ይከፍሉበታል።

ማርያም በሙሴ ላይ ባጉረመረመች ጊዜ የማይድን በሽታ ክፉ መንፈስ በእርሷ ላይ ተጣበቀባት።

እስራኤላውያን በሙሴ ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ የሞትና የጥፋት ክፉ መንፈስ ወደቀባቸው። ከእነርሱ ወደ ተስፋይቱ ምድር የገባ ማንም አልነበረም።

በተመሳሳይ መንገድ፣ ካም አባቱን ባቃለለ ጊዜ የውርደት፣ የሥቃይ፣ የበታችኝነትና እልፍ ያለማለት መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደበት። ኖኅ ስለ ራቁትነቱ ውርደትና ሐፍረት ተሰምቶት ነበር። ነገር ግን፣ ካምና የእርሱ ተከታዮች በሕይወት ርካሽነት የሚዋረዱና የሚያፍሩ ሆኑ።

> ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ።
>
> እነርሱም፡- በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሮአልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ። እግዚአብሔርም ሰማ።
>
> (ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ አጅግ ትሑት ሰው ነበረ።)
>
> እግዚአብሔርም ወዲያው ሙሴንና አሮንን ማርያምንም፣ ሦስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ ብሎ ተናገረ፤ ሦስቱም ወጡ።





> እግዚአብሔርም በደመና ዓምድ ወረደ፣ በድንኳኑም ደጃፍ ቆመ፣ አሮንንና ማርያምን ጠራ፤ ሁለቱም ወጡ።
>
> እርሱም፡- ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፣ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፣ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ።
>
> ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፣ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው።
>
> እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፣ በምሳሌ አይደለም የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል፡ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም? አለ።
>
> እግዚአብሔርም ተቆጥቶባቸው ሄደ።
>
> ደመናውም ከድንኳኑ ተነሣ እነሆም፣ **ማርያም ለምጻም** *ሆነች፣* **እንደ ስመዳይም** *ነጭ* **ሆነች**፡ አሮንም ማርያምን ተመለከተ፣ እነሆም ለምጻም ሆና ነበር።
>
> ዘኍልቁ 12፡1-10

## 2. በአባቶቻቸው ላይ በሚያላግጡና በራሳቸው ላይ መርገምን በሚጠሩ ልጆች፣ ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች ይተላለፋሉ።

በአባት ላይ ማላገጥ አሞራዎች የልጆችን ዓይኖች ነጥጉጠው የሚያወጡበትን በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀውን እርግማን ያስከትላል።

በአባቶቻቸው ላይ የሚያላግጡ ልጆች አሉ። ሌላው ይቅርና የንቀት አመለካከት ማሳየት እንኳ እርግማንን ያስከትላል። አባቱን የሚንቅ ልጅ በሕይወቱ አንዳንድ እርግማኖች እንደሚፈጸሙ መጠበቅ የግድ ይሆንበታል። ልጅ የአባቱን ችግሮችና ሌሎችንም ጭምር የሚያስከትሉ እርግማኖችን ሊወርስ ይችላል። አባቶቻቸውን የሚንቁ ልጆች የተረገሙ ናቸው!

> በአባቷ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይነጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል።
>
> ምሳሌ 30፡17

### 3. የአባቶቻቸውን ምክር በሚንቁ ልጆች ችግሮች ከአባታቸው ወደ እነርሱ ይተላለፋሉ፡፡ የአባትህን ምክር መናቅ ሰነፍ ያደርግሃል፡፡

የአባታቸውን ምክር የሚንቁ ልጆች አሉ፡፡ ይህን ማድረጋቸው ሰነፎች ያደርጋቸዋል፡፡ ሰነፍ መሆን በዚህ ሕይወት ብዙ ጉዳቶችን ያስከትልብሃል፡፡

እስኪ ራስህ አንብበው፥ "ሰነፍ የአባቱን ምክር ይንቃል፥ ዘለፋን የሚቀበል ግን አእምሮው የበዛ ነው፡፡" (ምሳሌ 15:5)

". . . ሰነፍ ልጅ ግን እናቱን ይንቃል"(ምሳሌ 15:20)፡፡ ሰነፍ መሆን በሕይወትህ ጉዳቶችን እንድትቀበል ያደርጋል፡፡ አባትህን ባትንቅ ኖሮ እነዚያን ጉዳቶች አትቀበልም ነበር፡፡ በሕይወትህ የሚገጥሙህ ብዙዎቹ አሳዛኝ ተሞክሮዎች አባትህንና እናትህን በመናቅህ የምትቀበላቸው ጉዳቶች ናቸው፡፡ ከምትቀበላቸው ጉዳቶች ብዙዎቹ አባትህ በራሱ ጊዜ የተቀበላቸው መሆናቸውንም ትገነዘባለህ፡፡

> የሰነፍ ከንፈር በጥል ውስጥ ትገባለች፣ አፉም በትርን ትጠራለች፡፡
>
> ምሳሌ 18:6

### 4. ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉት በልጆች ውስጥ ትዕቢት ስለሚገባ ነው፡፡

አንድን ሰው የምትነቅፈው የእርሱን ያህል መልካም ነኝ ብለህ ስታስብ ብቻ ነው፡፡ ትሑት ሰው ታላላቅ ያባበጡ የትዕቢት ቃሎችን አይናገርም፡፡ ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ክርክር ሲጀምሩ፣ ምን ያህል ትልቅና ትዕቢተኛ እንደሆኑ ያሳያሉ፡፡ በትዕቢት ጠብ ብቻ ይሆናል (ምሳሌ 13:10)፡፡

ትዕቢት ውድቀትን ይቀድማል፡፡ ልጆች ከመውደቃቸው አስቀድሞ ትዕቢት ይገባባቸዋል፡፡ የአባቶች ስሕተት የትዕቢተኞች ልጆችን ነቃፊ መንፈስ ይቆሰቁሳል፡፡





ወደ ሕልውና ያመጣቸውንና ማንነትን የሰጣቸውን ሰው በጥላቻና በቁጣ ይናገራሉ፡፡ የማያውቁትን ነገር ይነቅፋሉ፣ ይህ የትዕቢት መንፈስ ደግሞ ለገዛ ራሳቸው ጥፋት በሮችን ይከፍታል፡፡

> ትዕቢት ጥፋትን፣ ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል፡፡
>
> ምሳሌ 16:18

### 5. ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉት በልጆች መታወር ምክንያት ነው፡፡

ዕውር ስትሆን በአባትህ ውስጥ ምንም መልካም ነገር ማየት ይሳንሃል፡፡ ዕውርነት ነቃፊ ሰዎችን የሚመታ በሽታ ነው፡፡ አባቶቻቸውን በመናቃቸውና በማዋረዳቸው የታወሩ ልጆች አሉ፡፡ የልጆች ዕውርነት የሚመጣው አክብሮት ከማጣታቸው የተነሣ ነው፡ ፡ ልጆች ሆን ብለው የአባቶቻቸውን ክብርሲያጣጥሉዕውርነት ይመጣል፡፡ የአባቶቻቸውን ተፈላጊነት በሚያጣጥሉበት ጊዜ የእነርሱን ጥበብ ለማየት፣ ከእነርሱ ልምዶች ለመማርና የሠሯቸውን ስሕተቶች ለምን እንዳደረጉ ለመገንዘብ አይችሉም፡፡ የአባቶቻቸውን ፈተናዎችና ችግሮች ማየትና መገንዘብ ይሳናቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ አባቶቻቸው በሄዱበት መንገድ ለመጓዝ እርምጃቸውን ይጀምራሉ፡፡

> በአባቷ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል፡፡
>
> ምሳሌ 30:17

### 6. ችግሮች ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፉት፣ ልጆች የአባቶቻቸውን ቃሎች ክብደት ሰጥተው ስለማይቀበሉ ነው፡፡

አባትህን መናቅ ቃሉን ክብደት ሰጥተህ እንዳትቀበል ያደርግሃል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን፣ 'በሕይወትህ የእርሱን ቃሎች አለመጠበቅ' በማለት ይገልጸዋል፡፡ ብዙ ልጆች አባቶቻቸው አንድን ነገር

ሊያስተምሯቸው በሚሞክሩበት ወቅት ዝርዝር ጉዳዮችን በአጽንኦት አይከታተሉም። አንዳንድ ችግሮች ለምን እንደሚከሰቱ ሲያስረዷቸው ልብ ብለው አይሰሙም። ሰሎሞን ልጁን ለሚናገረው ነገር ልቡን እንዲሰጥ እንዴት እንደሚጎተጉተው አስተውል።

> እኔም አባቴን የምሰማ ልጅ ነበርሁና፣ በእናቴም ዘንድ እወደድ ነበር፡፡
>
> ያስተምረኝም ነበር፣ እንዲህም ይለኝ ነበር፣**ልብህ ቃሌን ይቀበል** ትእዛዜን ጠብቅ በሕይወትም ትኖራለህ፡፡ጥበብን አግኝ ማስተዋልን አግኝ አትርሳም፣ ከአፌም ቃል ፈቀቅ አትበል፡፡አትተዋት፣ ትደግፍህማለች ውደዳት፣ ትጠብቅህማለች፡፡ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናትና ጥበብን አግኝ ከሀብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ፡፡ከፍ ከፍ አድርጋት፣ እርስዋም ከፍ ከፍ ታደርግሃለች ብታቅፋትም ታከብርሃለች፡፡ለራስህ የሞገስ አክሊልን ትሰጥሃለች፣ የተዋበ ዘውድንም ታበረክትሃለች፡፡ልጄ ሆይ፣ ስማ፣ ንግግሬንም ተቀበል የሕይወትህም ዘመን ትበዛልሃለች፡፡
>
> ምሳሌ 4:3-10

## 7. እንደ አባቶች የተሰጡአቸውን ታላላቅ ሰዎች እውቅና ለማይሰጡና ለማያከብሩ ልጆች ችግሮች ከአባቶች ወደ እነርሱ ይተላለፋሉ።

ለእነርሱ እንደ አባቶች የተሰጡአቸውን ታላላቅ ሰዎች የማያውቁ ልጆች ጥፋት ይመጣባቸዋል። ወደ እነርሱ የተላኩ ሰዎችን ታላቅነት በማይገነዘቡ ሰዎች ላይ ጥፋት እንደሚመጣ ተነግሮላቸዋል። ሰዎች አባቶቻቸው የሚሆኑ ታላላቅ ሰዎች እያሏቸው ነገር ግን አያውቋቸውም። በማክበር ፈንታ ይገድሏቸዋል። በኢየሱስ ላይ የሆነውም በቀጥታ ይህ ነበር።

> ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም፣ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፣ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፣ እናንተም አልወደዳችሁም፡፡
>
> እነሆ፣ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል፡፡ እላችኋለሁም፣ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም፡፡
>
> ሉቃስ 13:34-35



*ምዕራፍ 5*

# ችግሮችን የወረሱ ልጆች

በተለያዩ ልጆችና በአባቶቻቸው ላይ የተደረገው ጥናት ምስጢራዊ የሆነ የድግግሞሽ ኡደተረ መኖሩን ያሳያል። ልጆች ለምን በዚያው በአባቶች ችግር ውስጥ እንደሚዘፈቁ ትጠይቅ ይሆናል። ሰዎች ከታሪክ እንደማይማሩ፣ታሪክ ራሱ ያስተምረናል! ብዙ ልጆች አባቶቻቸው ከተማሩት ትምህርት ተነጥለው የቀሩ መሆናቸው ይብስ ያሳዝናል። ብዙ ልጆች አባቶቻቸው የነበሯቸው ችግሮች፣ ለእነርሱ ብቻ የተወሰኑ ልዩ ችግሮች አድርገው ያስባሉ። ምክር ይሰጣል፣ ነገር ግን የሚከተለው የለም። ብዙ ልጆች በአባቶቻቸው አማካኝነት ለሚተላለፍላቸው ትምህርቶች ምንም አጽንኦት አይሰጡም።

የዚህ አክብሮት የለሽ አቋም ውጤት የአባቶች መቅሰፍቶችና መከራዎች በልጆችም ላይ መደገማቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም እንዴት ሚስቱን እንደካዳት ያሳየናል።የጌራር ሰው ለሆነው አቤሜሌክ እኅቴ ናት በማለት ዋሸ። ከብዙ ዓመታት በኋላ ልጁ ይስሐቅ ያንኑ ደገመ።

ንጉሥ ዳዊት የሌላ ሰውን ሚስት በመተኛቱ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ትልቅ ችግር ደረሰረበት። ልጆቹም ያንኑ በመድገም ሕይወታቸውን አበላሹ። አምኖን አባቱ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ስላደረገው ነገር ሳያዝን አልቀረም። ነገር ግን የራሱ ታሪክም የተደመደመው የገዛ እኅቱን ትዕማርን በመድፈር ነበር።

አቤሰሎምም አባቱ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በመተኛቱ ሳይናደድ አልቀረም። በተጨማሪም አምኖን እኅቱን ትዕማርን ከደፈረ በኋላ ሳይቀጣ በመቅረቱ ሳያዝን አልቀረም። ዳዊት በእነዚህ ሁኔታዎች

**ላይ ችላ ማለቱ በአቤሰሎም ውስጥ ዓመጽ እንዲቀሰቀስ ያደረገ ይመስላል። ነገር ግን የአቤሰሎም ፍጻሜ የተደመደመው ከሁሉም የአባቶቹ ሚስቶች ጋር በመተኛት ነበር።**

**ሰሎሞንም ቢሆን ከሴቶች ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት ሕይወቱ የተበላሸ ሰው ነበር። ሰሎሞን ከአባቱ ስሕተቶች ይማራል ብለህ ጠብቀህ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ተምሮ ይሆናል። ምናልባትም የተማረከላት መስሎ የሚሰማውን ማናቸውንም ሴት ለማግባት ሳይወስንም አልቀረም። ሰሎሞን ከሴቶች ጋር የነበረው ችግር እንዲያውም ይበልጥ የተወሳሰበ ሆነ። ምክንያቱም እርሱን ከያህዌ ያራቁት እነዚህ ችግሮች ነበሩ። ሰሎሞን በመጨረሻ ጣዖት አምላኪ መሆኑን ሲናገር መስማት ያሳዝናል። አባቶቻቸው በገቡበት ችግር ከመዘፈቅ እግዚአብሔር ልጆችን ይታደግ።**

## አብርሃምና ልጁ ይስሐቅ

## አብርሃም እንዴት ሚስቱን እንደካደ

አብርሃምም ከዚያ ተነሥቶ ወደ አዜብ ምድር ሄደ፣ በቃዴስና በሱር መካከልም ተቀመጠ በጌራራም በእንግድነት ተቀመጠ።፡አብርሃምም ሚስቱን ሣራን፡- **እኅቴ** *ናት* አለ፡ የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክም ላከና ሣራን ወሰዳት። እግዚአብሔርም ሌሊት በሕልም ወደ አቢሜሌክ መጣ፣ እንዲህም አለው፡- እነሆ፣ አንተ ስለ ወሰድሃት ሴት ምውት *ነህ* እርስዋ ባለ ባል ናትና።፡አቢሜሌክ ግን አልቀረባትም ነበር፤ እንዲህም አለ፡- አቤቱ፣ ጻድቁን ሕዝብ ደግሞ ታጠፋለህን?

**እኅቴ ናት** ያለኝ እርሱ አይደለምን? እርስዋም ደግሞ ራስዋ፡- ወንድሜ ነው አለች፡ በልቤ ቅንነትና በእጄ ንጹሕነት ይህንን አደረግሁ።፡እግዚአብሔርም በሕልም አለው፡ - ይህን በልብህ ቅንነት እንዳደረግህ እኔ አወቅሁ፤ እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ፡ ስለዚህም ትነካት ዘንድ አልተውሁም።፡

አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ፤ ነቢይ ነውና፣ ስለ አንተም ይጸልያል፣ ትድናለህም፡ ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት፣ ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ።፡

ዘፍጥረት 20፡1-7





## ይስሐቅ እንዴት ሚስቱን እንደካደ

በምድርም ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከሆነው ራብ በላይ ራብ ሆነ። ይስሐቅም ወደ ፍልስጥኤም ንጉሥ ወደ አቢሜሌክ ወደ ጌራራ ሄደ።፡

እግዚአብሔር ተገለጠለት፣ እንዲህም አለው፡- ወደ ግብፅ አትውረድ፤ እኔ በምልህ ምድር ተቀመጥ እንጂ፡በዚህች ምድር ተቀመጥ፣ ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፣ እባርክሃለሁም፤ እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለአንተም፣ ለዘርህም እሰጣለሁና፣ ለአባትህ ለአብርሃም የማልሁለትንም መሐላ አጸናለሁ፤

ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ፣ እነዚህንም ምድሮች ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤አብርሃም ቃሌን ሰምቶአልና፣ ፍርዴን፣ ትእዛዜን፣ ሥርዓቴን፣ ሕጌንም ጠብቆአልና።፡ይስሐቅም በጌራራ ተቀመጠ፡

የዚያም ስፍራ ሰዎች ስለ ሚስቱ *ጠየቁት* እርሱም፡- እኅቴ *ናት* አለ፡ የዚህ ስፍራ ሰዎች ለርብቃ ሲሉ እንዳይገድሉኝ *ብሎ* ሚስቴ *ናት* ማለትን ፈርቶአልና እርስዋ ውብ *ነበረችና*፡በዚያም ብዙ ቀን ከተቀመጠ በኋላ የፍልስጥኤም ንጉሥ አቢሜሌክ በመስኮት ሆኖ ጎበኘ፣ ይስሐቅም ሚስቱን ርብቃን ሲዳራት አየ።፡

አቢሜሌክም ይስሐቅን ጠራ፣ እንዲህም አለው፡- እነሆ ሚስትህ *ናት* እንዴትስ እርስዋን፡- እኅቴ ናት አልህ? ይስሐቅም፡- በእርስዋ ምክንያት እንዳልሞት ብዬ ነው አለው።፡አቢሜሌክም አለ፡- ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? ከሕዝብ አንዱ ከሚስትህ ጋር ሊተኛ ጥቂት በቀረው ነበር፣ ኃጢአትንም ልታመጣብን ነበር።፡

አቢሜሌክም *ሕዝቡን* ሁሉ፡- ይህን ሰው፣ ሚስቱንም የሚነካ ሞትን ይሙት ብሎ አዘዘ።፡

ዘፍጥረት 26፡1-11

## ዳዊትና ልጆቹ አምኖን፣ አቤሰሎምና ሰሎሞን

## ዳዊት እንዴት ከሴቶች ጋር ችግር እንደገጠመው

እንዲህም ሆነ ወደ ማታ ጊዜ ዳዊት ከምንጣፉ ተነሣ፣ በንጉሥም ቤት በሰገነት ላይ ተመላለሰ፡ በሰገነቱ ሳለ አንዲት ሴት ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም መልከ መልካም ነበረች። ዳዊትም መልእክተኞች ልኮ አስመጣት፤ ወደ እርሱም ገባች፣ ከርኩሰትዋም ነጽታ ነበርና ከእርስዋ ጋር ተኛ፡ ወደ ቤትዋም ተመለሰች።፡

2 ሳሙኤል 11፡2፤4

## አምኖን እንዴት ከሴቶች ጋር ችግር ውስጥ እንደገባ

ከዚህም በኋላ እንዲህ ሆነ፣ ለዳዊት ልጅ ለአቤሴሎም አንዲት የተዋበች እኅት ነበረች፣ ስምዋም ትዕማር ነበረ፤ የዳዊትም ልጅ አምኖን ወደዳት።

አምኖንም ከእኅቱ ከትዕማር የተነሣ እጅግ ስለተከዘ *ታመመ*፤ ድንግልም ነበረችና አንዳች ያደርጋት ዘንድ በዓይኑ ፊት ጭንቅ ሆኖበት ነበር።ለአምኖንም የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ኢዮናዳብ የሚባል ወዳጅ ነበረው፤ ኢዮናዳብም እጅግ ብልህ ሰው ነበረ።እርሱም፦ የንጉሥ ልጅ ሆይ፣ ስለ ምን ቀን በቀን እንዲህ ከሳህ? አትነግረኝምን? አለው። አምኖንም፣ የወንድሜን የአቤሴሎምን እኅት ትዕማርን እወድዳታለሁ አለው።

ኢዮናዳብም፣ ታምሜአለሁ ብለህ በአልጋህ ላይ ተኛ፣ አባትህም ሊያይህ በመጣ ጊዜ፣ እኅቴ ትዕማር እንድትመጣና እኔ የምበላውን እንጀራ እንድትሰጠኝ፣ መብሉንም እኔ እያየሁ እንድታዘጋጅልኝ፣ ከእጅዋም እንድበላው እለምንሃለሁ በል አለው።እንዲሁም አምኖን፦ ታምሜአለሁ ብሎ ተኛ፣ ንጉሡም ሊያየው በመጣ ጊዜ አምኖን ንጉሡን፦ እኅቴ ትዕማር እንድትመጣና እኔ እያየሁ ሁለት እንጎቻ እንድታደርግልኝ፣ ከእጅዋም እንድበላ እለምንሃለሁ አለው።

ዳዊትም፦ መብልን ታዘጋጂለት ዘንድ ወደ ወንድምሽ ወደ አምኖን ቤት ሂጂ ብሎ መልእክተኞችን ወደ ትዕማር ቤት ላከ።ትዕማርም ወደ ወንድምዋ ወደ አምኖን ቤት ሄደች፤ ተኝቶም ነበር። ዱቄትም ወስዳ ለወሰች፣ እያየም እንጎቻ *አደረገች፣ ጋገረችም*።ምጣዱንም ወስዳ በፊቱ ገለበጠች እርሱ ግን ይበላ ዘንድ እንቢ አለ። አምኖንም፣ ሰውን ሁሉ ከእኔ ዘንድ አስወጡ አለ። ሰውም ከእርሱ ዘንድ ወጣ።

አምኖንም፣ ከእጅሽ እበላ ዘንድ መብሉን ወደ እልፍኙ አግቢው አላት። ትዕማርም የሠራችውን እንጎቻ ወስዳ ወንድምዋ አምኖን ወዳለበት እልፍኝ *አገባችው። መብሉንም* ባቀረበች ጊዜ ያዛትና፣ እኅቴ ሆይ፣ ነዪ ከእኔም ጋር ተኚ አላት። እርስዋ መልሳ፣ ወንድሜ ሆይ፣ አይሆንም እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ዘንድ አይገባምና አታሳፍረኝ፤ ይህንም ነውረኛ ሥራ አታድርግ። እኔም ነውሬን ወዴት ልሸከም? አንተም፣ በእስራኤል ዘንድ ከምናምንቴዎች እንደ አንዱ ትሆናለህ። እንግዲህስ ለንጉሡ ንገረው፤ እኔንም አይነሣህም አለችው።

ቃልዋን ግን .አልሰማም፣ ከእርስዋም ይልቅ ብርቱ ነበረና በግድ አስነወራት፤ ከእርስዋም ጋር ተኛ።

ከዚያም በኋላ አምኖን ፈጽሞ ጠላት፤ አስቀድሞም ከወደዳት ውድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በለጠ። አምኖንም፣ ተነሥተሽ ሂጂ አላት።

2 ሳሙኤል 13፡1-15





## አቤሴሎም በሴቶች ምክንያት እንዴት ችግር ውስጥ እንደገባ

አቤሴሎም አኪጦፌልን፦ ምከሩ ምን እናድርግ? አለው።

አኪጦፌልም አቤሴሎምን፦ ቤት ሊጠብቁ ወደ ተዋቸው ወደ አባትህ ቁባቶች ግባ እስራኤልም ሁሉ አባትህን እንዳሳፈርኸው ይሰማሉ ከአንተም ጋር ያሉት ሁሉ እጃቸው ይበረታል አለው።

ለአቤሴሎምም በሰገነት ላይ ድንኳን ተከሉለት አቤሴሎምም በእስራኤል ሁሉ ፊት ወደ አባቱ ቁባቶች ገባ።

በዚያም ወራት የመከራት የአኪጦፌል ምክር የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መጠየቅ ነበረች የአኪጦፌልም ምክር ሁሉ ከዳዊትና ከአቤሴሎም ጋር እንዲህ ነበረች።

2 ሳሙኤል 16፡20-23

## ሰሎሞን በሴቶች ምክንያት እንዴት ችግር ውስጥ እንደገባ

ንጉሡም ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ ሌላ፣ በሞዓባውያንና በአሞናውያን፣ በኤዶማውያን፣ በሲዶናውያንና በኬጢያውያን ሴቶች፣ **በብዙ እንግዶች ሴቶች ፍቅር ተነደፈ**።

**እግዚአብሔር** የእስራኤልን ልጆች፣ አምላኮቻቸውን፡ ትከተሉ ዘንድ ልባችሁን በእውነት ያዘነብላሉና ወደ እነርሱ አትግቡ፣ እነርሱም ወደ እናንተ አይግቡ ካላቸው ከአሕዛብ፣ ከእነዚህ ጋር ሰሎሞን በፍቅር ተጣበቀ።

ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት፡ **ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት**።

1 ነገሥት 11፡1-3

## አብርሃም፣ ልጁ ይስሐቅና የልጅ ልጁ ያዕቆብ

### አብርሃም የበኩር ልጁን እንዴት እንዳገለለ

አብርሃምም ማልዶ ተነሣ፣ እንጀራንም ወሰደ፣ የውኃ አቁማዳንም ለአጋር በትከሻዋ አሸከማት፣ ብላቴናውንም ሰጥቶ አስወጣት፡ እርስዋም ሄደች፣ በቤርሳቤህም ምድረ በዳ ተቅበዘበዘች።

ዘፍጥረት 21፡14

## ይስሐቅ የበኩር ልጁን እንዴት እንዳገለለው

**ይስሐቅም ያዕቆብን ባርኮ ከፈጸመ በኋላ**፣ ያዕቆብም ከአባቱ ከይስሐቅ ፊት ከወጣ በኋላ፣ ወዲያው በዚያው ጊዜ ዔሳው ከአደኑ መጥቶ ገባ።

እርሱም ደግሞ ጣፋጭ መብል አዘጋጀ፣ ለአባቱም አገባ አባቱንም፣ አባቴ ይነሣ፣ ነፍስህም ትባርከኝ ዘንድ ከልጁ አደን ይብላ አለው።

አባቱ ይስሐቅም፣ አንተ ማን *ነህ?* አለው እርሱም፡- እኔ የበኩር ልጅህ ዔሳው *ነኝ* አለው።

*ይስሐቅም እጅግ ደነገጠ እንዲህም አለ፡- ያደነውን ሲደን ወደ እኔ ያመጣ ማን ነው? አንተ ሳትመጣም ከሁሉ በላሁ፣ ባረክሁትም እርሱም የተባረከ ሆኖ ይኖራል።*

ዔሳውም የአባቱን ቃል በሰማ ጊዜ ታላቅ እጅግም መራራ ጩኸት ጮኸ፣ አባቱንም፣ አባቴ ሆይ፣ *እኔንም* ደግሞ ባርከኝ አለው።

እርሱም፡- ወንድምህ በተንኮል ገብቶ በረከትህን ወሰደብህ አለ።

እርሱም አለ፡- በእውነት ስሙ ያዕቆብ ተባለ፣ ሁለት ጊዜ አሰናከሎኛልና ብኩርናዬን ወሰደ፣ አሁንም እነሆ በረከቴን ወሰደ። ደግሞም፡- ለእኔ በረከትን አላስቀረህልኝምን? አለ።

ይስሐቅም መለሰ ዔሳውንም አለው። እነሆ፣ ጌታህ አደረግሁት፣ ወንድሞቹንም ሁሉ ለእርሱ ተገዦች ይሆኑ ዘንድ ሰጠሁት፣ በእህልም በወይንም አበረታሁት፡ ለአንተ ግን፣ ልጄ ሆይ፣ ምን ላድርግ?

ዘፍጥረት 27፡30-37

## ያዕቆብ የበኩር ልጁን እንዴት እንዳገለለው

ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አለ፡- በኋለኛው ዘመን የሚያገኛችሁን እንድነግራችሁ ተሰብሰቡ።

እናንተ የያዕቆብ ልጆች ተሰብሰቡ፣ ስሙም፣ አባታችሁ እስራኤልንም አድምጡ።

ሮቤል፣ አንተ በኩር ልጄና ኃይሌ፣ የጉብዝናዬም መጀመሪያ ነህ። የክብር አለቃና የኃይል አለቃ።

እንደ ውኃ የምትዋልል ነህ፣ አለቅነት ለአንተ አይሁን። ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና አረከስኸውም፤ ወደ አልጋዬም ወጣ።

ዘፍጥረት 49፡1-4



*ምዕራፍ 6*

# የእውነተኛ ልጅ ሰባት ምልክቶች

አንድ ቀን የምክር አገልግሎት በምሰጥበት ጠረጴዛ አንፃር ባልና ሚስት ተቀምጠው ነበር። ሴትየዋ፣ "ቢሾፕ፣ እኔ ሴት ልጅህ ነኝ" አለችኝ። እኔም አረምኋትና፣ "አንቺ ልጄ አይደለሽም፣ አንቺ የቤተክርስቲያን አባል ብቻ ነሽ" አልኋት።

ቅር የተሰኘች መሰለች፣ እኔ ግን ቀጠልሁና፣ "አንቺ ሁልጊዜ ፈገግታ የምታሳዩና የምታበረታቺን በጣም ጥሩ የቤተክርስቲያን አባል ነሽ። ያን ማድረግሽ ደግሞ ልጅ አያደርግሽም። አንቺ በጣም ጥሩ ሰው እንጂ ልጅ አይደለሽም" አልኋት።

አምስት ዓይነት የቤተክርስቲያን አባላት አሉ፡ እነዚህም፣ በጣም ጥሩ ሰዎች፣ በጣም የሚያበረታቱ ሰዎች፣ በጣም ተፈላጊ ሰዎች፣ በጣም አስፈላጊ ሰዎችና በጣም አደገኞች ሰዎች ናቸው።

ማብራራቴን በመቀጠል፡

"ልጆቼ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሯሯጡ ስታዪ፣ የእኔ ልጆች መሆናቸውን የምታውቂው እንዴት ነው?" ብዬ ጠየቅኋት።

እርሷ ምላሽ ስላልሰጠችኝ እኔ ራሴ፣"እኔን ይመስላሉ። ልጆቼ እኔን እንደሚመስሉ ማየት አትችዪም?"በማለት መለስሁ።

እርሷም በራሷ ንቅናቄ አዎንታዊ መልስ ሰጠች።

ከዚያም ቀጥዬ፣ "በአንቺና በእኔ መካከል ምን ተመሳሳይነት አለ? አንቺ በአገልግሎት ሥራ ውስጥ ተሳታፊ አይደለሽም። አንቺ እረኛ አይደለሽም። ለመርዳት የምታደርጊው ምንም ነገር የለም። በቤተክርስቲያን ውስጥ የምትሠሪው ምንም ነገር የለም። አንቺ በጣም ጥሩ ሴት እንጂ ልጅ አይደለሽም!"አልኋት።

በመጨረሻ የምናገረው ነገር ገባት፡፡ እንዲሁ ወዲያና ወዲህ ማለትና ጥሩ መሆን ወንድ ወይም ሴት ልጅ አያደርግም፡፡ በዚያን ቀን ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚጫወቱ ብዙ ልጆች ነበሩ፡፡ ነገር ግን የእኔዎቹ ልጆች ሁለቱ ብቻ ነበሩ፡፡ በአካባቢው መገኘት ልጅ አያደርግህም፡፡ ታዲያ ልጅ የሚያደርጉህ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ወንድ ወይም ሴት ልጅ እንድትሆን የሚያደርጉ ነገሮች አሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ለአንተ ለማካፈል የምፈልገውም ይህንን ነው፡፡

## ሰባት የወንድና የሴት ልጅነት ምልክቶች

### 1. ወንድ ወይም ሴት ልጅ አባታቸውን ይመስላሉ፡፡

> ኢየሱስም አለው፡- አንተ ፊልጶስ፣ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ?
>
> ዮሐንስ 14፡9

ወንድና ሴት ልጆቼን በአገልግሎት ውስጥ ስታዩ፣ ከእኔ ጋር የተወሰነ መመሳሰል እንዳላቸው ታውቃላችሁ፡፡ በወንድ ልጆችና በአባቶች መካከል ያለው ተመሳሳይነት በአባቶችና በልጆች መካከል ያለውን የግንኙነት ምልክት ያሳያል፡፡

በተፈጥሮ ልጆቼ የሚመስሉት እኔን ሲሆን የቆዳቸው ቀለምም የእኔ ዓይነት ነው፡፡ በመንፈሳዊ ነገርና በአገልግሎትም፣ በጌታ በወለድኋቸው ልጆቼና በእኔ መካከል ብዙ ተመሳሳይነት አለ፡፡ ኢየሱስ፣ "እኔን ያየ አብን አይቷል" ማለቱ ይታወሳል፡፡

የእኔ ወንድና ሴት ልጆች በዚያ በኃይል እያገለገሉ ስላሉ፣ በየቤተክርስቲያኖች እየተሯሯጥሁ መስበክ አያስፈልገኝም፡፡ ልጅን ካየህ አባትን አይተሃል ማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ ልጅ የአባት ግልባጭ ወይም ፎቶኮፒ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከአባቱ የተቀበላቸው በጣም ጠቃሚ የሆኑ ባሕርያት አሉት፡፡ እያንዳንዱ ልጅ የአባቱ ጂን፣ የደም ዓይነትና ዲ ኤን ኤ አለው፡፡ የአባታቸውን ነገር ከመውረሳቸው የተነሣ በጣም





አባታቸውን የሚመስሉ አንዳንድ ልጆች አሉ፡፡ በሌላ በኩል እውነተኞች ልጆች ሆነው እያሉ እንኳ ከአባቶቻቸው ጋር ጥቂት አምሳያ ብቻ ያላቸው ልጆችም አሉ፡፡

### 2. ወንድ ወይም ሴት ልጅ ለዘላለም ልጆች ናቸው፡፡

> ባሪያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል፡፡
>
> ዮሐንስ 8፡35

እውነተኞች ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁልጊዜ የቤቱ አባል ናቸው፡፡ የተፈጥሮ ልጅህ ምንም ነገር ያድርግ፣ ሁልጊዜም ከቤተሰቡ እንዳንዱ ነው፡፡ የተለያዩ እምነቶች ሊኖሩት ይችላል፣ ነገር ግን የቤቱ አባል ነው፡፡

እርሱም በልቡ የማን እንደሆነ ያውቃል፣ አሁን የሆነውን እንዲሆን ማን እንዳደረገውና እንዳሳደገውም ያውቃል፡፡

> ከእኛ ዘንድ ወጡ፣ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ፡፡
>
> 1 ዮሐንስ 2፡19

### 3. ወንድና ሴት ልጆች በአባቶቻቸው ያምናሉ፣በማንኛቸውም ነገር ይመኩባቸዋል፡፡

> እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡፡ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፡ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤
>
> ማቴዎስ 6፡9-13

እውነተኞች ልጆች ብዙ መተማመን በውስጣቸው የሞላባቸው ናቸው፡፡ ብዙዎቹ የሥራ ቦታዎች መተማመን በሌላቸው ሰዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ የበታች ሠራተኞች አለቆቻቸውን አያምኗቸውም፡፡ አለቆችም በፊናቸው የበታች ሠራተኞቻቸውን አያምኑም፡፡

ነገር ግን በቤተሰብ ውስጥ ልጆች ብዙ ጊዜ አባቶቻቸውን ፍጹም ያምናሉ። ልጆች በአባቶቻቸው ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ ሰምቼ አላውቅም።

እግዚአብሔርን ይበልጥ በተማመንነን መጠን፣ የእርሱን በረከቶች በበለጠ ደረጃ እንቀበላለን። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባሉ ልጆች መካከል ልዩነት የሚፈጠረው ብዙ ጊዜ ለአባታቸው ካላቸው የተለያየ የመተማመን ደረጃ የተነሣ ነው።

በአገልግሎትም የማየው ይህንኑ ነው። ይበልጥ ለሚተማመኑ ወንድና ሴት ልጆች የእግዚአብሔር በረከቶችና ቅባቶች በእኔ በኩል ይፈስላቸዋል። አንዳንድ ወንድና ሴት ልጆች ጠበኞችና ተጠራጣሪዎች ናቸው። ሌሎች ደግሞ የሚተማመኑና በእምነት የተሞሉ ናቸው። የሚተማመኑ ልጆች ሁልጊዜ የአባታቸውን ብልጫ በረከቶች ይቀበላሉ። እነዚህ ልዩነቶች የሚከሰቱት በአባታቸው ላይ ካላቸው የተለያዩ የእምነት ደረጃዎችና አባቶቻቸው ከሚናገሯቸው ነገሮች ነው።

> እንኪያስ፣ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ . . .
>
> ሉቃስ 11:13

ኢየሱስ በአባቱ ችሎታ ይተማመን ነበር። ኢየሱስ አባቱ ኃያል መሆኑን ያምን ነበር። ኢየሱስ የአባቱን ኃይል ያውቅ ነበር። በመስቀል ላይ የተናገረው የመጨረሻ ቃሉ ራሱን ለአባቱ እጅ አሳልፎ ማስረከቡን የሚገልጽ ነበር። "አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ።"

በእነዚያ ቃሎች ነፍሱን ከሞት መንጋጋዎች ፈልቅቆ በማውጣት በአባቱ እጆች አኖረ።

> ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ። አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።
>
> ሉቃስ 23:46





የሞት ማስፈራሪያዎች ወደ እርሱ እየቀረቡ ቢሆኑም እንኳ፣ እርሱን ለመታደግ ማን ኃይል እንዳለው ስላወቀ በአባቱ ተማመነ። ያ ኢየሱስ ያከበረው፣ የአባት ኃይል ይህ ነው። በምድር ላይ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃሎቹ ልጅ በአባቱ ስላለው እምነት እውነትን መፈንጠቃቸው የሚያስገርም አይደለምን? እፁብ ድንቅ!

## 4. ልጅ አባቱን ያከብራል

> እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ፣ ልጅ አባቱን፣ ባሪያም ጌታውን ያከብራል። እኔስ አባት ከሆንኩ ክብሬ ወዴት አለ?
>
> ሚልክያስ 1:6

ከአሽከሮች ወይም ከሠራተኞች ክብርን አትጠብቁ። ከሠራተኞች መጠበቅ የምትችሉት ጮማ አፍና የማስመሰል ፈገግታ ብቻ ነው። ክብርን ግን ከእውነተኛ ልጅ መጠበቅ ትችላላችሁ። በብሉይ ኪዳን ካህናት የሚባሉት በመሠረቱ ከአባቶቻቸው ጎን የሚያገለግሉ የልጆች ቡድን ነበሩ።

የአንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን መጋቢ እንዲህ አለኝ፣ "ከሌሎች ቤተክርስቲያኖችና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የወጡ መጋቢያንን በመሾሜ በርካታ መጥፎ ተሞክሮዎች ነበሩኝ። አሁን ግን በአገልግሎቱ ውስጥ ከእኔ ጋር የሚሠሩት የራሴ መንፈሳዊ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ብቻ ናቸው።"

መሆን ያለበት እንዲህ ነው! ክብርን የሚያመጡልህ እውነተኞቹ ልጆችህ ብቻ ናቸው። ከአንዳንድ ኮብላይ ልጆች በስተቀር፣ አብዛኞቹ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለአባታቸው ክብርና ደስታን ያመጣሉ።

አባት የሆኑትን ሰዎች እንዳከብር እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ መርቶኛል። በግልም ሆነ በሕዝብ ፊት ላከብራቸው ሞክሬአለሁ። በንግግሬም፣ በስጦታዬም አክብሬአቸዋለሁ።

እውነተኞች ወንዶችና ሴቶች ልጆች አባታቸውን በገንዘብ ያከብራሉ። ልትረዳቸው እየቻልህ አባትህና እናትህ በገንዘብ እጦት

መጨነቃቸው እንዴት አሳዛኝ ነው። ወላጆችህ አንተን ገንዘብ እንዲሰጡህ ትፈልጋለህ? ይህ አባትህን ማክበር አይደለም! ይህ እርሱን ማዋረድ ነው።

አባትህና እናትህ ምንም ሳያስፈልጋቸውም እንኳ፣ በስጦታ ልታከብራቸው ይገባል። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይህን ነው።

> እናንተ ስሜን የምታቃልሉ ካህናት ሆይ፣ ልጅ አባቱን፣ ባሪያ ጌታውን ያከብራል፡ እኔስ አባት ከሆንሁ ክብሬ ወዴት አለ? ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ ወዴት አለ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡- እናንተም፣ ስምህን ያቃለልን በምንድር ነው? ብላችኋል። በመሠዊያዬ ላይ ርኩስ እንጀራ ታቀርባላችሁ። እናንተም፣ ያረከስንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። የእግዚአብሔር ገበታ የተነቀፈ ነው በማለታችሁ ነው። ዕውር መሥዋዕትንም ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን? አንካሳውንና የታመመውን ስታቀርቡ፣ ይህ ክፉ አይደለምን? ያንን ለአለቃህ አቅርብ፤ በውኑ በአንተ ደስ ይለዋልን?ወይስ ፊትህን ይቀበላልን? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡-
>
> ሚልክያስ 1:6-8

## 5. ልጆች አባቶቻቸውን ይታዘዛሉ።

> ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።
>
> ኤፌሶን 6:1-3

ብዙ ዓመፀኞች ሰዎች ራሳቸውን ወንድና ሴት ልጆች ነን ብለው መጥራት ይወዳሉ። እኔ የሥነ-ጠፈር ባለሙያ ያልሆንሁትን ያህል እነርሱም ወንድና ሴት ልጆች አይደሉም። እውነተኞች ልጆች አባቶቻቸውን ይታዘዛሉ! በአገልግሎት ውስጥ እውነተኞች ወንድና ሴት ልጆች ባልሆኑት ላይ ሥልጣንን ለመጠቀም አትሞክር። የአንተ እውነተኞች ወንድና ሴት ልጆች ስላልሆኑ ታዛዦች አይደሉም። የሚታዘዙህ እውነተኞቹ ወንድና ሴት ልጆችህ ናቸው።





አንድ ሰው ወንድ ወይም ሴት ልጅ አለመሆኑ ሲሰማኝ፣ እንዲያደርግ በምነግረው ነገር በጣም እቆጠባለሁ። የሚታዘዙ እውነተኛ ወንድና ሴት ልጆች ብቻ ናቸው።

## 6. ወንድና ሴት ልጆች አባቶቻቸው ሲያደርጉ የሚያዩትን ያደርጋሉ።

> ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ፣ እንዲህም አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን ያደርጋልና።
>
> ዮሐንስ 5:19

እውነተኛ ልጅ አባቱ የሚያደርገውን በጥብቅ ይከታተላል። አባቱ የሚሠራውን ነገር ይወዳል፣ ትክክለኛውን መንገድ ያውቃል ብሎም ያስባል። ኢየሱስ ያደረገው ይህን ነው። አባቱ ሲፈውሳቸው ያያቸውን ብቻ ፈወሰ፣ አባቱ ሲሰብክ ያየውን ብቻ ሰበከ።

ልጆች ከአባቶቻቸው ይበልጥ ብልህ የሚሆኑት ከስንት አንዴ ቢሆን ነው። ኢየሱስ በቤተሰይዳ መጥመቂያ አጠገብ የነበሩትን ጭፍራ ሰዎች ሁሉ ለምን አልፈወሰም? አንዱን ሰው ከፈወሰ በኋላ ሌሎቹን አልነካቸውም። ወደ ሆስፒታል ሄዶ አንድን ሰው ብቻ እንደመፈወስ ነው። ለአእምሮህ ባይመችህም አብ ያደረገው ግን ይህን ነው። ኢየሱስ አባቱ ሲያደርግ ያየውን በማድረግ ይደሰት ነበር።

በአገልግሎት ውስጥ እኔ ሳደርግ ያዩትን በማድረጋቸው እየበለጸጉ ያሉ ወንድና ሴት ልጆች አሉኝ። እኔ የምሰብከውን ይሰብካሉ፣ እኔ የማስተምረውንም ያስተምራሉ። እኔ የታመሙትን ስፈውስ ያዩና እነርሱም ሕሙማንን መፈወስ ይጀምራሉ። ይህን የሚያደርጉት ማሰብ የማይችሉ ግልባጮች ስለሆኑ አይደለም፤ ይልቁንስ ጥሩ ወንድና ሴት ልጆች ስለሆኑ ብቻ ነው! ጥሩ ልጆች ፈጣን ተከታዮች ናቸው።

በእርግጥ ማንኛው፣ *ሥጋዊ* አባት (እኔም) ፍጹም አይደለንም፤ ደግሞም ሕይወታችን ሊከተሉት የሚገባ ፍጹም ምሳሌ ሊሆንም አይችልም። ዋነኛው ምሳሌያችን ክርስቶስ ነው! ነገር ግን በዚህ ምድር እግዚአብሔር የምንከተላቸው ተግባራዊ ምሳሌዎች እንዲኖሩን አባቶችን ይሰጠናል።

7. ልጆች የአባቶቻቸውን ቃሎች ይይዛሉ።

የእውነተኛ ልጅ ምልክት የአባቱን ቃሎች መያዙ ነው። የአባቱን ቃሎች ብዙ ጊዜ ይሰማል፤ ደግሞም በተቻለው ጊዜ ሁሉ ይደጋግማቸዋል። አንዳንድ ጊዜ የአባቱን ቃሎች በንግግር ውስጥ ሲደግምና አንዳንድ ጊዜም አባቱ የሰበከውን ሲሰብክ ትሰማዋለህ። ኢየሱስ፣ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" ብሏል።

ሰዎች ልጆችን "እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከየት አገኛችሁ? ይህንንስ ጥበብ ከየት አገኛችሁ?" ብለው ይጠይቋቸዋል።

ነገር ግን ጉዳዩ የአባቶቻቸውን ቃሎች መደጋገማቸው ብቻ መሆኑ እሙን ነው።

> እኔ አባቴን የምሰማ ልጅ ነበርሁና፣ በእናቴም ዘንድ እወደድ ነበር። ያስተምረኝም ነበር እንዲህም ይለኝ ነበር። ⍰ልብህ ቃሌን ይቀበል፤ ትእዛዜን ጠብቅ በሕይወትም ትኖራለህ።⍰
>
> ምሳሌ 4፡3-4



*ምዕራፍ 7*

# አራት ዓይነት ልጆች

የልጅ ማንነት የሚገለጠው ለአባት በሚሰጠው ምላሽ ነው። ብዙ ጊዜ፣ ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ መልካም፣ መጥፎና አስቀያሚ ነገር ይወጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አራት ዓይነት ልጆች ይናገራል - እነርሱም፣ ኮብላይ ልጅ፣ ታላቅ ልጅ፣ የተወደደ ልጅና እልከኛና ዓመፀኛ ልጅ ናቸው።

1. የኮብላይ ልጅ ባሕርያት

> እንዲህም አለ፡- አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፡ ከእነርሱም ታናሹ *ለባቱን* አባቴ ሆይ፣ ከገንዘብህ *የሚደርሰኝን* ክፍል ስጠኝ አለው። *ገንዘቡንም* አካፈላቸው። ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፣ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ።
>
> ሉቃስ 15፡11-13

1. ኮብላይ ልጅ ከአባቱና ከአባቱ ቤት ይሄዳል።
2. ኮብላይ ልጅ የተቻለውን ያህል ከቤት መራቅ ይፈልጋል።
3. ኮብላይ ልጅ የሕይወት እድሎቹን ያባክናል።
4. ኮብላይ ልጅ በሕይወቱ መካከል ስሕተቶቹን ተገንዝቦ ወደ አባቱ ይመለሳል።
5. ኮብላይ ልጅ ከሞኝነቱና ከዓመፃዊ መንገዶቹ የተነሣ ብዙ ነገሮችን ያጣል።

## 2. የታላቅ ልጅ ባሕርያት

ታላቁ ልጁ በእርሻ ነበረ፤ መጥቶም ወደ ቤት በቀረበ ጊዜ የመሰንቆና የዘፈን ድምፅ ሰማ፤ ከብላቴናዎችም አንዱን ጠርቶ ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ።

እርሱም፡- ወንድምህ መጥቶአልና፣ በደኅና ስላገኘው አባትህ የሰባውን ፍሪዳ አረደለት አለው። ተቆጣም ሊገባም አልወደደም፤ አባቱም ወጥቶ ለመነው።

እርሱ ግን መልሶ አባቱን እነሆ፣ ይህን ያህል ዓመት እንደ ባሪያ ተገዝቼልህ ከትእዛዝህም አልተላለፍሁም፤ ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም፤

ነገር ግን ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ፣ የሰባውን ፊሪዳ አረድህለት አለው።

እርሱ ግን፡- ልጄ ሆይ፣ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፣ ለእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፤

ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ፣ ሕያው ስለሆነ ጠፍቶም ነበር፣ ስለተገኘ፡ ደስ እንዲለን ፍሥኃ እንድናደርግ ይገባናል አለው።

ሉቃስ 15፡25-32

1. ታላቅ ልጅ በቤት ከአባቱ ጋር ይኖራል።
2. ታላቅ ልጅ ከባድ ኃጢአቶችን ፈጽሞ አያደርግም።
3. ታላቅ ልጅ ወላጆቹ ካኖሩለት ቀጥተኛና ጠባብ መንገድ ወጥቶ አይጠፋም።
4. ታላቅ ልጅ የተድላና የአባካኝነት ሕይወት አይኖርም።
5. ታላቅ ልጅ ከመንገድ በሚኮበልሉ ላይ የግለ-ጽድቅና የፈራጅነት አቋም ይይዛል። ከእነዚህ ኃጢአቶች አንዱንም እንኳ እርሱ ፈጽሞ ስላላደረገ፣ ሰዎች በእንደነዚህ ዓይነት ስንፍናዎች ለምን እንደሚዘፈቁ ጥያቄ ይሆንበታል። ኮብላዩ ልጅ በመጨረሻ በሚመለስበት ወቅት አባት





በሕይወት እንዲኖር ጸለይ። ኮብላዩ ልጅ ከታላቁ ልጅ እጅ ላይ ወድቆ ቢሆን ኖሮ ለእርሱ መልካም ባልሆነለት ነበር፡
፡

## 3. የተወዳጅ ልጅ ባሕርያት

ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፣ ሰማያት ተከፈቱ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ፣ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤

እነሆም ደምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።

ማቴዎስ 3፡16-17

ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው።

በፊታቸውም ተለወጠ፡ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፣ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።

እነሆም፣ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።

ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፣ ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፡ ብትወድስ፣ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ።

እርሱም ገና ሲናገር፣ እነሆ፣ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፡እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ **የምወደው ልጄ ይህ ነው**፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

ማቴዎስ 17፡1-5

1. በሁለት በተለያዩ ጊዜያት፣ የሰማዩ አባት ኢየሱስ ክርስቶስን በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ (ጥምቀት) እና በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ (ፊቱ በተለወጠ ጊዜ) የምወደው ልጅ ብሎ ጠርቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ተወዳጅ ልጅ የተባለው አንዲት ስብከት ሳይሰብክ ወይም አንድ ሕመምተኛ ሳይፈውስ ነበር።

2. ተወዳጅ ልጅ ለሥልጣን ራሱን የሚያስገዛ ሰው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ተወዳጅ ልጅ የተባለው ገና በአገልግሎት ጅማሮ ሲሆን ቀለል ባለ ሁኔታ የተጠራውን መጠራት በተቀበለ ጊዜ ነበር።ተወዳጅ

ልጅ ትሑት ነው። ኢየሱስ ተወዳጅ ልጅ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ መጥምቁን ዮሐንስ አጎንብሶ በማክበሩ ነበር።

3. ተወዳጅ ልጅ ማናቸውንም ትእዛዞች የሚታዘዝ ነው። ተወዳጅ ልጅ ትርጉም ቢሰጠውም ባይሰጠውም ትእዛዞችን ይቀበላል። ተወዳጅ ልጅ ቢቀለውም፣ ቢከብደውም ትእዛዞችን ይቀበላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ታዛዥ የነበረው ለመልካሞችና ለቀላል ትእዛዞች ብቻ አልነበረም። በማናቸውም ደረጃ ታዛዥ ነበር። ተወዳጅ ልጆች በማናቸውም የተለያዩ የመታዘዝ ደረጃዎች ሁሉ ትእዛዝን ይቀበላሉ።

በእርግጥ የተለያዩ የመታዘዝ ደረጃዎች ቢኖሩም ተወዳጅ ልጅ በእነዚህ ደረጃዎች ሁሉ ራሱን ለይቶ ያቀርባል። እያንዳንዱ የመታዘዝ ደረጃ ወደ ተለያዩ በረከቶች ይመራል። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለእኛ ለማሳየት አባቱን ታዝዞ ወደዚህ ምድር መጣ። ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መጨረሻው በመሄድ አባቱን እስከ መስቀል ሞት ድረስ እንኳ ታዟል። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ወደተለዩ ዓይነት ሞቶች የሚያደርሷቸውን ትእዛዞች መቀበል ያስቸግራቸዋል። ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ አይደለም! እርሱ ልዕለ-ፍጹማዊ "ተወዳጅ ልጅ" ነበር።

## 4. እልከኛና ዓመፀኛ ልጅ

ማንም ሰው ለአባቱ ቃልና ለእናቱ ቃል የማይታዘዝ ቢቀጡትም የማይሰማቸው እልከኛና ዓመፀኛ ልጅ ቢኖረው፣

አባቱና እናቱ ይዘው ወደ ከተማው፣ ሽማግሌዎች ወደሚኖሩበትም ስፍራ በር ያምጡት፤

የከተማውንም ሽማግሌዎች ይህ ልጃችን እልከኛና ዓመፀኛ ነው፣ ለቃላችንም አይታዘዝም ስስታምና ሰካራም ነው ይበሉአቸው።

የከተማውም ሰዎች ሁሉ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩት፣ እንዲህም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታርቃለህ፤ እስራኤልም ሁሉ ሰምተው ይፈራሉ።

ዘዳግም 21፡18-21





አንተ ግን፣ የሰው ልጅ ሆይ፣ የምነግርህን ስማ፤ እንደዚያ እንደ ዓመፀኛው ቤት ዓመፀኛ አትሁን።አፍህን ከፈት የምሰጥህንም ብላ።

ሕዝቅኤል 2፡8

1. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች ትእዛዞችን አይሰሙም።
2. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች ትእዛዞችን ይቃወማሉ።
3. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች የአባታቸውን ማንነት አይወዱም።
4. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች የአባታቸውን ስልቶች አይወዱም።
5. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች የአባታቸውን መንገዶች እየጠሉ ያድጋሉ።
6. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች ከአባታቸው የተለየ ሥራ ይፈልጋሉ።
7. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች ከአባታቸው የተለየ አኗኗር ይፈልጋሉ።
8. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች የሚለብሱት፣ የሚያደርጉትና ሁሉንም ነገር የሚከውኑት ከአባታቸው በተለየ መንገድ ነው።
9. እልከኞችና ዓመፀኞች ልጆች የእርምት ነገር ያናድዳቸዋል፤ ደግሞም ሲታረሙ ስለሚናደዱ እርምት የግድ ይሆንባቸዋል።

## *ምዕራፍ 8*

# አደገኞች ልጆች

ከመንፈሳዊ አብራክህ የሚወጡ እውነተኞች ልጆችህ የሆኑ ሰዎች አሉ:: ምንም እንኳ ልጆችህ ቢሆኑም፣ ትልቅ ችግር ሊፈጥሩብህ ይችላሉ:: እንደ አንድ መሪ፣ የምታሳድጋቸውና የምታሠለጥናቸው ሰዎች እንደ ዱር ነብር በአንተ ላይ ተመልሰው ቢዘሉ አትገረም::

የአቤሴሎም ዓይነት መንፈስ ያላቸው ልጆች አሉ:: እንደነዚህ ያሉ ሰዎች አደገኞች ናቸው:: *አደገኞች ናቸው የምለው የአንተ አካል ሆነው ነገር ግን አንተኑ መልሰው ስለሚወጉ ነው::* የአንተን ርስት የእኔ ነው ይላሉ! እንዲያውም አንተን ይመስላሉ፣ ነገር ግን በእነርሱ ላይ ያለ የአቤሴሎም መንፈስ ሁሉንም ነገር ይለውጥባቸዋል::

አንተን ለመግደል የሚነሣ ልጅን እንዴት አድርገህ ትለያለህ? እንደ ወትሮው ሁሉ ለማናቸውም ነገር ከሁሉም የላቀ መመሪያ የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው::

## አስራ ሁለት የአደገኛ ልጆች ምልክቶች

1. አደገኛ ልጅ ይቅርታ ባለማድረግና በመራራነት የተሞላ ነው::

**አቤሴሎምም** እኅቱን ትዕማርን ስላሳፈራት **አምኖንን ጠልቶታልና** አቤሴሎም አምኖንን ከፉም ሆነ መልካም አልተናገረውም::

2 ሳሙኤል 13:22

የዳዊትም ወንድም የሳምዓ ልጅ ኢዮናደብ፣ ጌታዬ ጎልማሶቹ ልጆች ሁሉ እንደሞቱ አያስብ:: **እኅቱን ትዕማርን በግድ ካስነወራት ጀምሮ አቤሴሎም ዘንድ የቀረጠ ነገር ነበረና** የሞተ አምኖን ብቻ ነው::

2 ሳሙኤል 13:32

አቤሴሎም እኅቱን ትዕማርን በማስነወሩ ምክንያት ወንድሙን ይቅር ያላለ ሰው ነበር። ለሁለት ዓመት በልቡ ጥላቻን አከረመ። በቀልን አቅዶ በመጨረሻ ተግባራዊ አደረገው። ይህች ዓለም ብዙ ግፍ ያለባት ቦታ ነች። ብዙ ነገሮች በቤተክርስቲያን ሊያስቀይሙህ ይችላሉ። መራርነትን አዳፍኖ መያዝ አገልጋይ ማድረግ ከሚገባው ነገሮች የመጨረሻው ቢሆን ይሻላል።

ለአንድ አገልጋይ ታላቁ ፈተና ይቅርታ አለማድረግ ነው። ይህ ኃጢአት ብቻውን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊነጥልህ ይችላል። በብሉይ ኪዳን ካህን ለመሆን የሚያስፈልጉ አንዳንድ ግዴታዎች ነበሩ። ካህን ያልተፈወሱ ቁስሎችና ሕመሞች ሊኖሩት አይገባም። ያልዳነ ቁስል ጠቅላላውን ሰውነት እስከሚበክል ድረስ በሽታው ሊባባስ ይችላልና።

ካህን ወይም መጋቢ ያልተፈወሱ ቁስሎችን ይዞ መመላለስ አይፈቀድለትም ነበር። "ዕውር፣ ወይም አንካሳ፣ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፣ ወይም ትርፍ አካል ያለው፣ ወይም እግረ ሰባራ፣ ወይም እጀ ሰባራ፣ ወይም ጎባጣ፣ ወይም ድንክ፣ ወይም ዓይነ መጭማጫ፣ ወይም *እከካም፣* ወይም *ቋቁቻም፣* ወይም ጃንደረባ፣ ወይም ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ። ከካህኑ ከአሮን ዘር ነውር ያለበት ሰው የእግዚአብሔርን የእሳት ቁርባን ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። ነውረኛ ነው፤ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። የቅዱሱንና የቅድስተ ቅዱሳኑን የአምላኩን እንጀራ ይብላ፤ ነገር ግን ነውረኛ ነውና መቅደሶቼን እንዳያረክስ *ወደ መጋረጃው አይግባ፣ ወደ መሠዊያውም አይቅረብ።* የምቀድሳቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ" (ዘሌዋውያን 21፡18-23)።

በወይን ማሳ የሚሠራ እውነተኛ አገልጋይ በተደጋጋሚ ይቆስላል። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ የቆሰለ ቢሆንም ነገር ግን ይቅር ብሏል። ይህ መከተል ያለብን ምሳሌ ነው።

መጋቢዎች ከሚደርስባቸው የዘወትር ቁስሎች አንዱ ምስጋናቢሶችና እምነት አጉዳዮች የሚያደርሱት ነው። ሰዎች ለእነርሱ ምን ያህል በረከት እንደሆንክላቸው እንዴት እንደሚረሱ በጣም ያስደንቃል።





በአንተ ላይ ይነሣሉ። ብዙ አገልጋዮች የሰዎችን ምስጋናቢስነትና እምነት አጉዳይነት መቀበል ይሳናቸዋል። ምስጋና ቢስነትን ለመቀበል ያለመቻላቸው ብዙ ጊዜ ለሕይወታቸውና ለአገልግሎቶቻቸው አቅጣጫ ለውጥ ምክንያት ይሆናል።

ዴሬክ ፕሪንስ በመጨረሻ ቃለ ምልልሱ ወቅት የያዛቸው ቅሬታዎች እንዳሉትና እንደሌሉት ተጠየቀ። በሚያስደንቅ ሁኔታ እርሱን የበደሉትን ሰዎች ማድረግ በሚገባው ትክክለኛ ጊዜ ይቅር አለማለቱ ቅር እንደሚያሰኘው ተናገረ።

አገልጋይ መሆን ተጨማሪ ምሕረትን ከእግዚአብሔር መቀበል ነው፡ ፡ ይህ ምሕረት ለተርታው ክርስቲያን ከሚሆነው በላይና ላቅ ያለ ነው። "ስለዚህ ምክንያት ምሕረት እንደተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም" (2 ቆሮንቶስ 4፡1)።

ስለዚህም ምሕረትንና ይቅርታን ለሚያስቀይሙን ማሳየት ይጠበቅብናል።

አንድ ቀን በረዳቱ አልፎ ከተሰጠ መጋቢ ጋር ለመናፈስ አብረን ወጥተን ነበር። አሳልፎ ስለሰጠው ሰው ሲናገር እንዴት እያየሁት እንደተንገበገበ አስተዋልሁ። ይህ እምነት አጉዳይ ረዳት በእርሱ ላይ የሠራውን ማመን አልቻለም ነበር። ለተደረገለት መልካምነት ሁሉ የሰጠው ምላሽ ፊቱን በጥፊ መመታት ሆነ።በወቅቱ በዚህ ወንድሜ ፊት ላይ ሰንበሮችንና ትኩስ ቁስሎችን በቀጥታ ማየት ቻልሁ። በእውነት የተጎዳ ሰው ስለነበር ርኅራኄ ተሰማኝ። ነገር ግን ይህ የአገልግሎቱ መጨረሻ ሊሆን ይችላል ብዬም ተጨነቅሁለት።

አየህ፣ የአቤሴሎም ይቅርታ አለማድረግ ለጥፋቱ የጉዞው መጀመሪያ ነበር። ምናልባት አቤሴሎም ከዳዊት ቀጥሎ ንጉሥ መሆን ይችል ነበር። ነገር ግን የአምኖን ቁስል አቤሴሎምን በጥላቻ የተሞላ ገዳይ አውሬ እንዲሆን አደረገው።

መጋቢዎች ወደ መራራ ባሕርይ ውስጥ የሚገቡት ከውጭ በእነርሱ ላይ በተደረገ ቁስል አማካኝነት ነው። ለአንድ ነገር የምታሳየው ምላሽ ሊገድልህ ይችላል።

አስም ይቅርታ አለማድረግን የሚያስታውሰኝ በሽታ ነው። አስም ሳንባን ለሚያስቆጡ ንጥረ ነገሮች ሰውነት የሚያሳየው ከመጠን ያለፈ አጸፋ ምላሽ ውጤት ነው። ሌሎች ተጨማሪ አስቆጪ ንጥረ ነገሮችን ላለማስገባት የአየር ቧንቧዎች ሲኮማተሩ አየር ወደ ውስጥ መሳብ አስቸጋሪ ይሆናል። ይህ አጸፋ ምላሽ ከልኩ አልፎ ሲገኝ ሞት ይከሰታል።

አቤሴሎም በወንድሙ ወንጀል ላይ ከሚገባው በላይ አጸፋ ምላሽ ተሰማው። አቤሴሎም ይቅርታ በመንፈግ፣ በምሬትና በበቀል ጎዳና ሲቀጥል የራሱን ሕይወትና አገልግሎቱን መና አስቀረ።

እግዚአብሔር በሆነ መንገድ አለፍ ብለን ይቅርታ እንድናደርግ ይጠብቅብናል። ምናልባት ከፍተኛ የሆነ በደል የሚመጣው ከትዳር ጓደኛ ሊሆን ይችላል። ጋብቻ አካላዊና ተፈጥሮአዊ አንድነትን ያካተተ ስለሆነ፣ አገልጋዮች ለተደራራቢ ሥጋዊ ቁስለቶች የተጋለጡ ናቸው። እያንዳንዱ/ዷ አገልጋይ በጋብቻ እስከ መጨረሻው ለመዝለቅ ባለው ወይም ባላት ቁርጠኝነት የማያወላውሉ መሆን ይገባቸዋል።

ስለ ትዳር ጓደኛህ ፈጽሞ አቋምህን አትቀይር። ቁስሎችህና ጉዳቶችህ ወደ ስሕተት ውስጥ እንዲመሩህ አትፍቀድ። በአእምሮህ ሊኖሩ ከሚችሉ ሌሎች አማራጮች ያህል ጋብቻህ የጎዳህን ያህል ይጎዱሃል። ምንም አማራጭ የለህም። እግዚአብሔር ከሰጠህ/ከሰጠሽ ጋር እስከ መጨረሻው ቆይ/ዪ።

ጆን ዌዝሊ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። የእርሱ ትዳር በጣም አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ከዚያቹ የትዳር ጓደኛው ጋር አብሮ ዘለቀ። ከሚስቱ ጋር መኖር የማይቻል እንኳ





ሆኖ እያለ፣ ከእርሷ ጋር በትዳር ቆየ። ከእርሷ ተለይቶ ቢያውቅም ነገር ግን ፈጽሞ አልፈታትም።

ጋብቻ ለዕድሜ ልክ ነው። መልካም ይሁን መጥፎ እግዚአብሔር ይቅር እንድትልና በፍቅር እንድትገዝ ይጠብቅብሃል። ይቅርታ የማያደርጉና የማይረሱ ሰዎችን ተጠንቀቅ።

## 2. አደገኞች ልጆች ወንድሞቻቸውን ያጠቃሉ።

> አቤሴሎምም እንደ ንጉሥ ግብዣ ያለ ግብዣ አደረገ። አቤሴሎምም አገልጋዮቹን፦ አምኖን የወይን ጠጅ ጠጥቶ ልቡን ደስ ባለው ጊዜ እዩ። አምኖንን ግደሉ ባልኋችሁም ጊዜ ግደሉት፣ አትፍሩም፡ ያዘዝኋችሁም እኔ ነኝና በርቱ ጽኑም ብሎ አዘዛቸው።
>
> 2 ሳሙኤል 13፡28

አደገኞች ልጆች ልምድ ላለው የሰው ዓይንም የሚያስጨንቅ ባሕርያትን ያሳያሉ። የገዛ ወንድምህን ማጥቃትና መግደል በጣም አስከፊ ምልክትና የስጋትም መንስኤ ነው። ሌሎች ባልደረቦቻቸውን የሚያጠቁ አገልጋዮችን የአደጋ ምልክቶች ማወቅ ይገባሃል።

ብዙ መጋቢዎች፣ አብዛኞቹ ንግግሮቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ከማድረግ ይልቅ በሌሎች ላይ እንደሚያነጣጥሩ አይገነዘቡም። የማያቋርጥ ነገር መሰንጠቅ፣ ሂስና ሹፈት በአንዳንድ መጋቢዎች ንግግር ውስጥ እጅግ የተለመደ ነው።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብዙ ጊዜም የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርትና መገለጦች እርስ በርስ ለመከፋፈል እንኳ አይቻልም።

የምቀኛ መጋቢዎች ንግግሮች ሌላ ሰው በሚያደርገው ነገር ላይ ያተኮሩ ይመስላሉ። እኔ እንደነዚህ ካሉ አገልጋዮች ኅብረት ራሴን ሳገል አይቻለሁ።

## 3. አደገኞች ልጆች በዓመታት መከራና ችግር አይለወጡም።

> አቤሴሎምም በኢየሩሳሌም ሁለት ዓመት ሙሉ የንጉሡን ፊት ሳያይ ተቀመጠ።
>
> 2 ሳሙኤል 14፡28

አቤሴሎም በሁለት ዓመታት የግዞት መከራ ተሠቃይቷል:: ስለሆነም የልብ ለውጥ ያገኛል ብሎ ማሰብ ይቻላል:: የምትቀጧቸውንና የምትገሥጹአቸውን መጋቢዎች ተጠንቀቁአቸው:: በቅጣት ውስጥ ማለፋቸው በራሱ ንስኃ ገብተዋል ማለት አይደለም:: ይቅርታ የመንፈግና የዓመፅ መንፈስ ከውስጥ እየተብላላ ሊሆን ይችላል::

አንድ የቀጣነውን የሥራ ባልደረባ አስታውሳለሁ:: "ትክክል አልነበርሁም፣ ስላደርግሁት ስሕተት ይቅርታ እጠይቃለሁ" በማለት የይቅርታ ደብዳቤ ጻፈ:: ይህን ደብዳቤውን ካስገባ በኋላ ለተወሰኑ ወራት ከሥራ ታገደ:: ከወራት እገዳ በኋላ ይህ የእኔ የሆነ ልጅ በሆነ መንገድ በዓመፅ በእኔ ላይ ተነሣ:: እኔንና የእርሱ የሆነችውን ቤተክርስቲያን ማጥቃት ያዘ::

በአንድ ወቅት ላይ "ከዚህ ከተማ ድራሽህን አጠፋለሁ" የሚል መልእክት ጻፈልኝ:: ምናልባት ሃሳቡ በከተማዪቱ ውስጥ ለመቆየት እስከማፍር ድረስ የሚችለውን ያህል ስሜን ማጥፋት የነበር ይመስላል::

እነዚህ ስጋቶች በአንተም ዘንድ የተለመዱ አይመስሉህም? አቤሴሎም ዳዊትን ከኢየሩሳሌም ለማባረር አልሞከረም?በእርግጥ አቤሴሎም ዳዊትን ለተወሰኑ ቀናት ከኢየሩሳሌም ለማባረር ችሎ ነበር::

ነገሩ እንዲህ ነው፡ የአቤሴሎም መንፈስ በቅጣትና እንዲያውም በዓመታት ከባድ ግሣጼ አይታረምም:: አቤሴሎም በቅጣት፣ በመከራ ወይም በድህነት ወቅቶች ውስጥ እንኳ ቢያልፍም ተለውጧል ብለህ በማሰብ እንዳትስት::

*አንዳንድ ሰዎች በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ይለፉ ለምን ፈጽሞ ይቅርታ እንደማይሉ ይህ ያስረዳል::* ብዙ መከራ ቢያዩም እንኳ ራሳቸውን አዋርደው ንስኃ አይገቡም:: እነዚህ ሰዎች የአቤሴሎም ዳግም አምሳል ብቻ ናቸው! የሁለት ዓመታት ስደትና መከራ





የአቤሴሎምን ልብ አልለወጠም:: በጣም በመደንደኑ እንዲያውም ይበልጥ አደገኛ ሆነ! እውነተኛው "አቤሴሎም" በአስጨናቂ ተሞክሮዎቹ አይንበረከክም:: እነዚህ ሁኔታዎችም እርሱን ሊለውጡት አይችሉም!

## 4. አደገኞች ልጆች የሚባረሩ ሆኖ አይሰማቸውም::

> አቤሴሎምም ኢዮአብን መለሰ፡- ከጌሹር ለምን መጣሁ? በዚያም ተቀምጬ ብሆን ይሻለኝ ነበር ብለህ እንድትነግረው ወደ ንጉሡ እልክህ ዘንድ ወደ እኔ ጠራሁህ:: አሁንም የንጉሡን ፊት ልይ፣ ኃጢአት ቢሆንብኝ ይግደለኝ አለው::
>
> 2 ሳሙኤል 14:32

አንድ ሰው ቁልፍ ሰው ስለሆንሁ አልነካም የሚል ስሜት ከያዘ ለአካባቢው አደገኛ ሰው ይሆናል:: አንዳንድ ሰዎች ሊነኩ የማይችሉ ስለሆኑ ሊወገዱ እንደማይችሉ ያስባሉ::

አቤሴሎም ሊወገድ እንደማይችል ተሰምቶት ነበር:: በምንም ዓይነት መንገድ ከቦታው ሊነሣ እንደማይችል ተሰማው::

አቤሴሎም ኢዮአብን ንጉሡ ዳዊት በእርሱ ምንም ዓይነት ስሕተት ቢያገኝ ዝም ብሎ እንዲገድለው እንዴት እንደነገረው እናነባለን::

አቤሴሎም አባቱ ሊገድለው እንደማይችል ተሰማው:: አቤሴሎም ዳዊት በሆነ መንገድ ሊቀጣው ወይም ሊያስተካክለው እንደሚችል እርግጠኛ አልነበረም::

እነዚህ የአቤሴሎም ቃሎች የአደገኛ ሰውን የአእምሮ ይዘት የሚያሳዩ ናቸው:: "አባቴ ሊያባርረኝ አይችልም"፣ "አባቴ ሊቀጣኝ አይችልም"፣ "አባቴ ሊነካኝ አይችልም::" በሌላ አነጋገር እኔ እንደማልነካ አውቃለሁ! ማለት ነው::

አልነካም ብሎ የሚያስብ ሰው ሁሉ የተሳሳተ አቋም የያዘ ሰው ነው::

አንድ ቀን፣ ከአንድ የትልቅ ቤተክርስቲያን አንጋፋ ሰው ጋር እጫወት ነበር። ይህ ሰው ወደ ሌላ ከተማ እንዲዛወር በመደረጉ ውስጡ እየተብሰለሰለ ነበር።

ይህ አንጋፋ መጋቢ በውስጡ እያደገ የነበረውንና በፍጥነት ወደ ሌላ ከተማ እንዲዛወር ያደረገውን ዓመፅ ተገንዝቧል።

ነገር ግን ይህ ሰው ራሱን የማይነካ አድርጎ ቆጥሮ ነበር። በተጨማሪም ከቤተክርስቲያኑ ዋና መሥሪያ ቤት መዛወር ስድብ ሆኖ ተሰምቶት ነበር።

ከዚህ ሰው ጋር በቅርንጫፍ ቤተክርስቲያን ስለሚኖረው የሥራ ደረጃ መነጋገራችንን ቀጠልን።

እንዲህ አለ፣ "እኔ አንጋፋ ተባባሪ አገልጋይ ነኝ። ደግሞም እዚህ ለብዙ ዓመታት ሠርቻለሁ። በእኔ ደረጃ ላለ ሰው የመዛወር ነገር ሊደረግ አይገባውም። እኔ መዛወር ከሚባል ነገር ውጭ ነኝ።"

በመቀጠልም፣ "*ዝውውር* የተሰኘው ቃል እንኳ ለእኔ የሚገባ አልነበረም. . . " አለ።

ይህ ሰው ራሱን የማይነካ አድርጎ የተቀበለ ነበር። ባለበት ደረጃ ለዘላለም የተተከለ መሰለው። የሚያሳዝነው ስለ ራስህ የማልነካ ነኝ ብለህ ማሰብ ስትጀምር፣ እየታበይህና እየሳትህ መሆንህ ነው። ልክ እንደ አቤሴሎም፣ ስሕተቶችህ ወደ ገዛ ጥፋትህ ያደርሱሃል። ትዕቢት ሁልጊዜ ከውድቀት ትቀድማለች።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ልዩና የተወደዱ ይመስላቸውና ይህን ሁኔታ ላላቸው ልዩ ቦታ መጠቀሚያ ያደርጉታል። ይህም ስሕተት ነው። አባት ሊያደርገው የማይፈልገውን ነገር የሚሠራ ኢዮአብ ሁልጊዜም እንደሚኖር ሊታወቅ ይገባል።

ካለው ጥሩ ደረጃ ሁሉ የሳተንና የታበየን ልጅ የሚያስወግዱ ሁኔታዎች ሁልጊዜም ቢሆን ይኖራሉ። እድልህን ሞክርና ማንም የማይነካ እንደሌለ ለራስህ ድረስበት።





## ከቻልህ አባረኝ

አንድ ጊዜ፣ በላዩ ካለው ሥልጣን የተነሳ ልዩ ልጁ የሆነ ሰው አክብሮት በጎደለው መንገድ ተንቀሳቀሰ። ያለመገዛት ብዙ ድርጊቶችንም አሳየ። ከእርሱ ጋር ለመወቃቀስ ብዬ ስልክ ብደውልለት እንኳ፣ለስልኬ መልስ ሊሰጥ ፈቃደኛ አልነበረም።

በምላሽ መስጫ መሣሪያው የእኔን ድምፅ ይሰማና ልገናኘውና ላነጋግረው በጽኑ እየሞከርሁ እንዳለሁ ይረዳል። ነገር ግን ምላሽ ለመስጠት ፍንክችም አልል አለ።ኃላፊው በስልክ እስከሚያገኘው አንድ ቀን ድረስ፣ ሁላችንንም በጋጠወጥነት ዘጋን። በእርሱና በኃላፊው መካከል አጭር ንግግር ተካሄደ። ከዚያ በኋላ ይህ ወጣት ለሁላችን የላከውን አስደንጋጭ መልእክት አስታውሳለሁ።

ኃላፊው፣ "የምታደርገውን ታውቃለህን?

እንዴት በጋጠወጥነት እየሠራህ እንዳለህ ይገባሃል?

ሁኔታው እንዴት አደጋ ላይ እንደደረሰ ታውቃለህ?

ለምትሠራቸው አንድምታዎቹ ምን እንደሆኑ ተገንዝበሃል?"በማለት ጠየቀው።

እርሱም ሲመልስ፣ "አውቃለሁ። የምሠራውን አውቃለሁ። የሁሉንም ነገር አንድምታ አውቃለሁ" አለ።

ኃላፊው፣ "ታዲያ የምታደርገውን እያደረግህ ያለኸው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።

በዚህ ጊዜ በንቀት ፀጥ አለ። ከዚያ ቀጠለና፣ "ምናልባት እኔን ማባረር ያስፈልግህ ይሆናል" አለ።

ኃላፊው እንደመንተባተብ እያለ፣ "ትክክል ነው የሰማሁህ?ምንድን ነው ያልኸው?" ብሎ ጠየቀው።

እርሱም ቀጠለና፣ "የትኛውም ጥሩ ድርጅት እንደ እኔ ያለውን ሰው ባባረረ ነበር። ማባረር መብትህ ነው" አለ።

ንግግሩ ፍጻሜ ላይ ደረሰና ኃላፊው ማመን እያቃተው ስልኩን ቁጭ አደረገ።

ይህ ኃላፊ ከዚህ ልጅ ጋር ስለነበረው ንግግር በነገረኝ ጊዜ ምን እየሆነ እንዳለ ተገነዘብሁ። አየሁ ይህ ሰው ላባርረው እንደማልችል አስቦ ነበር። እርሱ ልዩ ሰው መሆኑን ስለሚያውቅ ነገሮች እስከ ጫፍ ድረስ ይገፋ ነበር። ይህ ልጅ መሞት የሚገባው ቢሆንም እንኳ አባቱ እንደማይገድለው የሚያውቅ "አቤሴሎማዊ ልጅ" ነው።

በቀላሉ ላባርረው አለመቻሌም ደግሞ እውነት ነበር። ይህን ሰው እንዳባርር በተጠየቅሁ ጊዜ እንኳ፣ የእርሱን መባረር ለማስቀረት አንድ መላ ለመምታት ወሰንሁ። ሚስቱን ጠራሁና ባለቤቷን እኔ ከማባርረው በፊት እርሱ በክብር ሥራውን ለማቋረጥ እንዲጠይቅ እንድትመክረው ነገርኋት።

በዚህ አካሄዴ እንደ አባት ልጅ ራሱን ፈጽሞ እንዳያጠፋ ለመከላከል መንገድ እየፈለግሁ ነበር!

አቤሴሎም አባቱ ዳዊት ምን ያህል ይወደው እንደነበር ስለሚያውቅ ያንን መንገድ አድርጎ በመጠቀም፣ "ከቻለ እስኪ ይግደለኝ" አለ።

ኢዮአብ አቤሴሎምን በገደለ ጊዜ እንኳ ዳዊት ስለ ልጁ በጣም አዘነ።

> ንጉሡም እጅግ አዘነ፣ በበሩም ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ። ሲሄድም፣ ልጄ አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄ፣ ልጄ አቤሴሎም ሆይ፣ በአንተ ፋንታ ሞቼ ኖሮ ቢሆን፣ ልጄ አቤሴሎም፣ ልጄ ሆይ ይል ነበር። በዚያም ቀን፦ ንጉሡ ስለ ልጁ አዘነ ሲባል ሕዝቡ ሰምቶአልና የዚያ ቀን ድል በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ወደ ኀዘን ተለወጠ።
>
> 2 ሳሙኤል 18፡33-19፡2

## አይነኬ ሚስቶች

ሊፈቱ እንደማይችሉ የሚያስቡ ሚስቶችም በዚህ ጎራ ይፈረጃሉ። አንዳንድ ሚስቶች ፍቺን የሚቃወመውን የጋብቻ ቃልኪዳን ሥልጣን ያለ አግባብ በመጠቀም ጨካኞችና ዓመፀኞች ይሆናሉ።





ሊባረሩ፣ ሊፈቱ ወይም ሊተኩ እንደማይችሉ ያስባሉ! የባላቸውን ለእግዚአብሔር ቃል መስጠት ያዩና ይህን የአይነኬነት ደረጃቸውን ከአፍ እስከ ገደፍ ያለ አግባብ ይጠቀሙበታል።

ከዚህ መጋረጃ በስተኋላ ይደበቁና ዓቅም አልባ በሆኑት ባሎቻቸው ላይ የቻሉትን ያህል አስቀያሚ ባሕርይ ያሳያሉ።

ያገባ አገልጋይ መጮኽ እንደሚችል ነገር ግን መንከስ እንደማይችል ጥርስ ወላቃ ውሻ ነው። ሊያስጠነቅቅ፣ እንደ እብድ ሊጮኽና እንደ መብረቅ ሊቆጣ ቢችልም ሊያባርራት አይችልም! ሚስቶች ደግሞ ይህን ያውቁታል! በርካታ አገልጋዮች፣ "ልትፈታኝ አትችልም" የሚለውን አንቀጽ ከገደብ ውጭ በሚጠቀሙ እአምሮ በጎደላቸውና ክፉ ሴቶች እጅ በዝምታ ይሠቃያሉ። ይ-ይ-ይቅርታ!

5. አደገኞች ልጆች አባቶቻቸውን መተካት እንደሚችሉ ያስባሉ።

> አቤሴሎምም፣ ነገርና ክርክር ያለው ሁሉ ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ ቅንም ፍርድ እፈርድለት ዘንድ በአገር ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ ይል ነበር!
>
> 2 ሳሙኤል 15፡4

አቤሴሎም አባቱን ለመውረስና ለመተካት ምኞት ነበረው።

አቤሴሎም እንደ አባቱ እንደ ዳዊት ጥሩ ሰው ነኝ ብሎ አሰበ። "አባቴን አሁን መተካት እችላለሁ፣ እፈልጋለሁም።"ማለት የአቤሴሎም መንፈስ ነው። ይህ አባቱን በትሕትና መንፈስ ለመምሰል ከሚመኝ ልጅ ሁኔታ የተለየ ነው። ይህ "የግልበጣ" ወይም "የመተካት" መንፈስ ነው።

## ሊሰማህ ይችላል

ቢሾፕ ጓደኛዬ በዙሪያው ሁሉ የአቤሴሎም መንፈስ ይሰማው ነበር። "የግልበጣ መንፈስ የተጸናወታቸው አደገኞች ልጆች" በአገልግሎቱ ዙሪያ እያደቡ እንዳሉ ተገነዘበ። እነዚህ፣ መንፈሳዊ አባታቸው

ከእንግዲህ ወዲያ ቦታ የሌለው ሆኖ የሚሰማቸው ጭልፊቶች ናቸው፡፡

"አንዳንድ ሰዎች እኔን ጡረታ ሊያስገቡ ይፈልጋሉ፣ እኔ ግን ጡረታ መውጣት አልችልም!" በማለት ሳያስበው ድንገት ከአፉ አወጣ፡፡ ይህ ሰው አንዳንድ ሰዎች አካባቢውን እንዲለቅ እንደሚፈልጉ አውቋል፡፡

ቀጠለና፣ "የማያውቁት ነገር እኔ ከሄድሁ ወዲያ፣ እኔን ይዋጋኝ የነበረ 'ነገር' እነርሱንም የሚዋጋቸው መሆኑን ነው" አለ፡፡

## ሦስት የመተካት መንፈስ ምልክቶች

እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቤተክርስቲያን በሚመሠርቱበት ጊዜ ሁሉ፣ አባታቸው ወደነበረበት ደረጃ በፍጥነት ለመድረስ ያላቸውን ምኞት መደበቅ ያቅታቸዋል፡፡ "አቤሴሎም" አባቱን ለመውረስና ለመተካት ለብዙ ዓመታት የነበረውን ምኞቱን መደበቅ አልቻለም፡፡

አቤሴሎም . . . በአገሩ ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ? አለ (2 ሳሙኤል 15:4)፡፡

ይህ የመጀመሪያው የአቤሴሎም ጩኸት የዛሬ ዘመን "አቤሴሎሞች" ከሚጮኹት ጩኸት ጋር አንድ ነው፡፡

ይህ የእነዚህ አደገኞች ልጆች ድብቅ ምኞት ነው!

እነዚህ አደገኞች ሰዎች ሲሠሩ ማየት ያስገርማል፡፡ ድርጊታቸውን የሚያጋልጠው የመጡበት የዘር ሐረግ ብቻ ነው፡፡ በአቤሴሎሞች የተመሠረቱ አዳዲስና በዓመፅ የተሞሉ አገልግሎቶች የተወሰኑ ባሕርያት አሏቸው፡፡

የአቤሴሎም መንፈስ ባላቸው አደገኞች ልጆች የተቆረቆሩ ቤተክርስቲያኖችና አገልግሎቶች ያሏቸውን ሦስት የጋራ ባሕርያት ለማሳየት እፈልጋለሁ፡፡

ሀ) አዲሱን ቤተክርስቲያናቸውን ጥለዉት ከወጡት ቤተክርስቲያን አቅራቢያ መክፈት ይወዳሉ፡፡





ቤተክርስቲያኖቹ ብዙ ጊዜ የሚመሠረቱት የመጀመሪያ ቤተክርስቲያን ባለበት በዚያው ቦታ ነው፡፡ አንድ እኔ የምከታተለው ቤተክርስቲያን፣ ተገንጥሎ የሄደ አንድ ታዋቂ ተባባሪ መጋቢ ነበረው፡፡ ይህ ሰው በአንጋፋ መጋቢያችን ላይ ጎጂ የሆነ መረጃ የያዘ በራሪ ወረቀት አሳተመ፡፡ አንድ እሑድ ጠዋት ሁላችንም ወደ ቤተክርስቲያን መጥተን ባለንበት፣ እነዚህን በራሪ ጽሑፎች ማሰራጨት ጀመረ፡፡ ይሁንና ከጥቂት ጊዜ በኋላ አስተናጋጆች በጋራ ተነሥተው ገፈታትረው በመግቢያ በሩ አስወጡት፡፡

ይህ ሰው፣ እርሱ ብቃት የለውም ብሎ ላሰበው ሰው፣ ሕዝቡ ታማኝ መሆን መቻላቸው አስደንቆት በውጭ እንደቆመ ቀረ፡፡ በእርሱ ቤት መላው መንጋ እርሱን እንዲከተል የሚያደርግ በቂ መረጃ ያለው መስሎት ነበር፡፡ በዚህ ፈንታ እርሱ ታማኝ በሆኑ አስተናጋጆች ተወርውሮ ወጣ፡፡

የሚያስደንቀው በዚያው መንገድ መቶ ሜትሮች ወረድ ብሎ፣ሁሉም አባላት ይከተሉኛል ብሎ በማሰብ አዳራሽ ተከራየ፡፡ ይሁንና በጥቂት ወራት ውስጥ ያቋቋመው ቤተክርስቲያን ፍርስርሱ ወጣ፡፡ "አቤሴሎሞች" አንዳንድ ጊዜ መጨረሻቸው በጣም ግልጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር የአቤሴሎምን ሥራ አይባርክም፡፡

ለ) የአደገኞች ልጆች ሌላኛው ባሕርይ አባታቸው ይጠቀም የነበረውን ስም ለራሳቸው ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ፣ የአባታቸው ቤተክርስቲያን "ሉዘርስ ኢንተርናሽናል" የሚል ከሆነ፣ የአቤሴሎም ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ "ዲፌት ኢንተርናሽናል" የሚል ስያሜ ይይዛል፡፡ በሌላ በኩል፣ የአባት ቤተክርስቲያን "ሔቭን ቻፐል ኢንተርናሽናል" ከሆነ የአቤሴሎም ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ "ፓራዳይዝ ቻፐል ኢንተርናሽናል" የሚል ስያሜ ይኖረዋል፡፡

እንዲያውም በቤተክርስቲያናቸው ውስጥ ለነገሮች ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ስሞችን ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ የአባት ቤተክርስቲያን

መዘምራን "ዘ ሮዝስ" የሚል ስም ካላቸው የአቤሴሎም ቤተክርስቲያን መዘምራን ስም "ዘ ሊሊስ" ይሆናል።

የሕዋስ ቡድኖች "ሆም ፌሎሺፕስ" ከተባሉ፣ የአቤሴሎም የሕዋስ ቡድኖች "ሃውስ ፌሎሺፕስ" ይባላሉ።

ለእነዚህ አምሳያዎች ምክንያት የሚሆነው በእርግጥ ልጆች ስለሆኑና ልጅ ከአባቱ ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ ስላለው ነው። ቀደም ሲል እንዳልሁት እነዚህ "አቤሴሎሞች" ከአባታቸው ጋር የመተባበራቸውን መለያ መደበቅ አይችሉም።

"አቤሴሎም" እንዲያውም በአንዳንድ ሁኔታዎች የአባቱን አገልግሎት ስም ይዞ በመገኘት ስለ ስሙ ከአባቱ ጋር ይጣላል። ተገንጥለው የወጡበትን የመጀመሪያ አገልግሎት ስም እንደ ራሳቸው ስም ለመቀጠል የጣሩ የብዙ ተገንጣይ ቤተክርስቲያኖች አስደናቂ ምሳሌዎችን አይቻለሁ። አይገርምም?

ሐ) አደገኞች ልጆች የአባታቸውን ዓይነት ተመሳሳይ ተግባራትን ይፈጽማሉ።

አቤሴሎም የሚያውቀውን ሁሉ የተማረው ከአባቱ ስለሆነ፣ በራሱ ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ተግባራትን ይፈጽማል። ለምሳሌ የአባት ቤተክርስቲያን የሳምንት አጋማሽ አገልግሎቱ ሐሙስ ከሆነ፣ አቤሴሎምም እንዲሁ የሳምንት አጋማሽ አገልግሎቱን ሐሙስ ያደርጋል።

የአባቱ ቤተክርስቲያን አባላትን የሚያመላልስ አውቶብስ ካለው፣ አቤሴሎምም ብዙ ጊዜ ያንኑ ያደርጋል።

በእርግጥም አቤሴሎም ልጅ ነገር ሆኖም ግን አደገኛ ልጅ ለመሆኑ እነዚህ ጥቂት አምሳያዎች ናቸው።





## 6. አደገኞች ልጆች አባቶቻቸውን ይቃወማሉ።

> አቤሴሎምም ነገርህ እውነትና ቅን ነው፤ ነገር ግን ከንጉሥ ታዝዞ የሚሰማህ የለም ይለው ነበር። አቤሴሎምም፣ ነገርና ክርክር ያለው ሁሉ ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ ቅንም ፍርድ እፈርድለት ዘንድ በአገር ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ? ይል ነበር።
>
> 2 ሳሙኤል 15፡3-4

አቤሴሎም አባቱ የሚመራበትን የአገር አስተዳደር ሁኔታ ተቃወመ። ተቃውሞ ከክፉ መንፈስ ይወለዳል። ተቃውሞን ትክክል የሚያደርግ ምንም ነገር የለም። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የተቃውሞ ተግባር ይኮንናል።

## የዱር አሳማ ራእይ

እኔ አንድ ጊዜ በተራሮች መካከል ረጅም መንገድ ብቻዬን ስጓዝ ራእይ አየሁ። ብዙ ርቀቶችን እስከማይ ድረስ ዙሪያዬ ግልጽ ነበር። በራእዩ ውስጥ፣ ከሁለት ሌሎች መጋቢዎች ጋር እያወራሁ አብረን እንራመድ ነበር።

አንድ ደረጃ ላይ ስለ አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ሃሳብ አቀረብሁ። አስተያየቱ የምስጋና ወይም እንዲሁ ክፉም ደግም ያልሆነ አልነበረም፡ ይህ ሰው ስለሠራው አንድ ነገር የሚነቅፍ ነበር፡
፡

ቃሎች ከአፌ ውስጥ ገና ሲወጡ፣ እንደ ዱር አሳማ ያለ ፍጥረት በእኔ አቅጣጫ መራመድ ሲጀምር አየሁ።

ከእኛ በስተኋላ በማይሎች ርቀት ላይ ነበር። ነገር ግን ወደ እኔ መንገድ የጀመረው ያን አስተያየቴን ገና እንደተናገርሁ ነበር። ያ ፍጥረት የእኔን አስተያየት የሰማ ይመስላል። *በሆነ መንገድ ተቃውሞዬ ወደ እኔ ጉዞ እንዲጀምር ምልክት ሆኖለታል።*

መጀመሪያ ላይ፣ የዚያ እንስሳ እንቅስቃሴ ከእኔ ጋር ምንም ግንኙነት የነበረው አልመሰለኝም። ነገር ግን ሰላም ሊሰማኝ ባለመቻሉ ወደኋላ እየተመለስሁ ማየት ጀመርሁ።

ይባስ ብሎ እንስሳው ወደ እኔ መገሥገሡን ቀጠለ። በአደጋ ላይ መሆኔን አወቅሁኝና ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ በፍጥነትና በቁርጠኝነት ወደ እኛ የሚመጣውን ፍጥረት ለመቋቋም ዞር አልን። በመጨረሻ ያ ፍጡር ደረሰብን። ያ አሳማ ጓደኞቼን ትቶ ወደ ደረቴ አነጣጥሮ ዘለለብኝ። በደረቴ ውስጥ ሰንጥቆ ሲገባ እሪ እንዳልሁ ወዲያው ነቃሁ።

ጌታ እንዲህ አለኝ፣ "ባሪያዎቼን በምትቃወምበት ማናቸውም ጊዜ ወደ ሕይወትህ ክፉ መናፍስትን ትጋብዛለህ።"

እነዚህ ክፉ መናፍስት በሕይወትህ በሽታና ሌሎች ደዌዎችን ያመጡብሃል። ከዚያ በኋላ በማናቸውም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ላይ መናገር በጣም አደገኛ መሆኑን ተገነዘብሁ።

በዚያ ራእይ በጣም ተብረከረክሁ።

ማናቸውም መንፈሳዊ የሆነ ሰው፣ ምንም ምክንያት ይኑረው እግዚአብሔር በቀባቸው ላይ ከመናገር ይቆጠባል። ማርያም በሙሴ ላይ ለመናገር በቂ ምክንያት ያላት ሆኖ ተሰምቷት ነበር።

ሙሴን በተቃወመች ጊዜ በለምጽ ተመታች፣ እግዚአብሔርም፣ " . . . በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም?" (ዘኁልቁ 12፡8) በማለት ጠየቃት።

## የኢያሱ ትውልድ

ሙሴን የተከተሉት ሕዝብ የተስፋይቱን ምድር ፈጽሞ አልወረሱም፡፡ የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ያልቻሉት በአንድ ምክንያት ነበር፡ የተቃውሞ፣ የማጉረምረም፣ የጥርጣሬና የነቀፋ መንፈስ ስለነበራቸው።

> ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።
>
> ዕብራውያን 3፡19





ይህ አለማመን የተገለጠው እንዴት ነበር? አለማመን የሚገለጸው በማጉረምረምና በተቃውሞ ነው። እስራኤላውያን ስለ ማናቸውም ነገር ይቃወሙ ነበር። በመጨረሻም፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳይገቡ ቀሩ። የሙሴ ትውልድ ወደ ተስፋይቱ ምድር አልገባም፤ ነገር ግን የኢያሱ ትውልድ ገባባት።

የኢያሱ ትውልድ ቅሬታንና ማንጎራጎርን ያስወገደ ትውልድ ነበር።

የተስፋይቱ ምድር የምትወረሰው ማጉረምረሙን በሚያቆም ትውልድ ነው። ማናቸውንም ዓይነት ማጉተምተምና ማንጎራጎር ማቆም ከቻልህ በቤተክርስቲያንህ፣ እግዚአብሔር በአገልግሎትህ የገባልህን ተስፋ ታያለህ።

የኢያሱ ትውልድ ማንጎራጎር የሚያስከትላቸው አጥፊ ውጤቶች የገባው ትውልድ ነበር።

> እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ብለው መለሱለት። ያዘዝኸንን ነገር ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደምትልከንም ስፍራ እንሄዳለን። በሁሉም ለሙሴ እንደ ታዘዝን እንዲሁ ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን ብቻ አምላክህ **እግዚአብሔር** ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ ከአንተ ጋር ይሁን።
>
> በትእዛዝህ *የሚያምፅ* ሁሉ የምታዝዘውንም ቃል ሁሉ የማይሰማ፣ እርሱ ይገደል ብቻ ጽና፣ አይዞህ።
>
> ኢያሱ 1፡16-18

## ካም፣ አደገኛው ልጅ

በቤትህ አድጎ፣ ካለህ ነገር ሁሉ ተጠቃሚ ሆኖ፣ ነገር ግን አንተን የማያምን ልጅ አደገኛ ልጅ ነው። እንደነዚህ ያሉ አደገኞች ልጆች አባታቸው ባይኖር ኖሮ መኖር እንደማይችሉ ይዘነጋሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ሌላ ሰው እንዲቻላቸው ባያደርግላቸው ኖሮ በአገልግሎት ላይ መሆን እንደማይችሉ ይዘነጋሉ።

ካም አባቱ መስከሩን እንዳወቀ ስለ ነገሩ ለሌሎች ለመንገር ወሰነ። በገዛ አባቱ ላይ ተሳለቀ! ካም የረሳው ነገር ኖኅ መርከብ ባይሠራ ኖሮ ሊኖር አይችልም ነበር! ካም በሕይወት ባይኖር ኖሮ፣ እንዴት አድርጎ አባቱን ኖኅን መቃወም ይችል ነበር? የካም እርግማን እንደዚያ ከባድ የሆነው ለዚህ ነው። አባትህ ቢሰክርም እንኳ ቢሆን አትቃወመው። ይልቅ አንተም እንዲህ ዓይነት የጠጪነት ችግር እንዳይኖርብህ ለራስህ ጸልይ።

## የሐሰት ትምህርት ሰነድ

በአንድ ወቅት በአገልግሎት ያሳደግኋቸውና ያሠለጠንኋቸው ልጆች ነበሩ። ገና ሳገኛቸው አገልጋዮች ከመሆንም በጣም የራቁ ተርታ የሆኑ ክርስቲያኖች ነበሩ። አሠለጠንኋቸውና መጋቢዎች አድርጌ በመሾም በቤተክርስቲያን ውስጥ መደብኋቸው።እያበረታታኋቸው ወጣት አገልጋዮችን ከሚያጠፉ ነገሮች ተከላከልኋቸው ። እነዚህ መጋቢዎች ምእመኖቻቸው በእነርሱ ላይ እንዲነሡ የሚያደርጉ ግልጽ ስሕተቶችን የሠሩባቸው ጊዜያት ነበሩ። ነገር ግን እኔ ጉድለታቸውን በመሸፈን ሰዎች በእነርሱ ላይ እንዲያምፁ አልፈቀድሁም።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ከእነርሱ መካከል አንዱን መጋቢ ማድረግ መቻሌን ሲሰማ፣ "አንተ ታምር እየሠራህ ነህ!" በማለት አዳነቀ።

በሌላ ቀን፣ ለዚህ ወጣት መጋቢ እጅግ ከመከላከሌ የተነሣ የተለዩ ዓላማዎች አሉት ተብዬ ተከሰስሁ። አንዳንድ ጊዜ ወጣት አገልጋዮች ሊሸፈንና ተቀባይነት ሊሰጠው የማይችል ባሕርይ ያንፀባርቃሉ። ይሁንና፣ እንደ አባት፣ በገዛ ሁለት እግሮቻቸው መቆም እስከሚችሉ ድረስ ልጆቼን መጠበቅ የእኔ ሃላፊነት ነው። ከጊዜ በኋላ፣ እነዚህ ወገኖች ከአገልግሎቴ ተለዩና ከቤተክርስቲያንም ራሳቸውን አገለሉ። ከአደገኞች ልጆች ጋር እየሠራሁ እንዳለሁ ስለተገነዘብሁ፣ ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት መቀጠሉ ደስ የማያሰኝ ተሞክሮ ሆነብኝ።





እነዚህ ወጣቶች ልጆች ነበሩ፤ ነገር ግን እንደ አቤሴሎም አባታቸውን የማያስደስቱ ሆኑ። እናፍቃቸዋለሁ፣ እንዲሁም ብዙ ጊዜም አስባቸዋለሁ። በሕይወታቸው ድጋፍ ለማድረግም እመኛለሁ፡ ፡ ይሁንና ሊሆን አልቻለም።

የተሰማኝ ትልቁ ድንጋጤ ስለ ስሕተት ትምህርት የሚናገር ሰነድ ከእነርሱ ባገኘሁ ጊዜ ነበር። በዚህ ሰነድ ውስጥ የስሕተት ትምህርቶች ባሕርያት ተዘርዝረዋል። ስሕተት ትምህርቶችን እንዴት መለየት እንደሚቻልና እንዴት መራቅ እንደሚቻል!

የሚያሳዝነው፣ እነዚህ ሁለቱ የእኔ ልጆች ያሳደገቻቸው የላይት ሃውስ ቻፐል የስሕተት ትምህርት ባሕርያት እንደለባት በዚህ ትምህርት ማወቃቸውን መናገራቸው ነው። ወደ እነዚህ "እውነቶች" በአንድ ላይ እንደደረሱና አሁን እኔም እንድማረው ቅጂ ለእኔ መላካቸው ነበር። የተላከልኝን የስሕተት ትምህርት ቅጂ ሰነድ ተቀበልሁ። ፍላጎታቸው የምሠራውን ሥራ የስሕተት ትምህርት የሚያሰኙብኝን የትኞቹ የአገልግሎቴ ባሕርያት እንደሆኑ እኔው ራሴ መርምሬ እንድደርስበት ነበር።

በእርግጥ እኔ የስሕተት ትምህርት መጋቢ እንደሆንሁ አላምንም። ከእንደዚህ ዓይነት ነገር እንድጠበቅ ጸጋና ምሕረት እንዲበዛልኝም እጸልያለሁ። ይሁንና፣ ለክርስቶስ መናቅንም ቢሆን እንደ ክብር እቆጥረዋለሁ።

እነዚህ ወጣቶች አሁን የስሕተት ትምህርት ባሕርያትን ያዩባት ቤተክርስቲያን እነርሱን ለአገልግሎት የሾመች መሆንኗን ዘንግተዋል፡ ፡

እኔ ራሴ ያሳደግሁት ሰው እኔና አገልግሎቴ የስሕተት ትምህርት አምሳያ እንዳለን ሲያስብ አያስደንቅም! እንደነዚህ ያሉ ነገሮችን መናገር የቻሉ የውጭ ሰዎችን እንኳ አላውቅም። ነገር ግን ሕይወት እንዲህ ነው። ወንዶችና ሴቶች ልጆች አባታቸው በሆነ ሰው ላይ አስተያየቶችን በሚሰጡበትወቅት መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል!

ኢየሱስ አጋንንትን ባወጣ ጊዜ የሆነ ሰው የብዔል ዜቡብን መንፈስ ይጠቀማል ብሎ አስተያየቱን ማሰማቱ የሚታወስ ነው። ኢየሱስ በዚህ ጊዜ እጅግ ከባድ የሆነ ማስጠንቀቂያ ሰጠ፡

> ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም።
>
> በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።
>
> ማቴዎስ 12:31-32

## 7. አደገኞች ልጆች በአባታቸው ላይ ሌሎችን ያነሣሣሉ።

> የተጠሩትም ሁለት መቶ ሰዎች ከአቤሴሎም ጋር በየዋህነት ከኢየሩሳሌም ሄዱ፤ የሚሆነውንም ነገር ከቶ አያውቁም ነበር።
>
> 2 ሳሙኤል 15:11

ሐሳዊ መሪዎች የሚከብሩት በተከታዮቻቸው ድንቁርና ነው። አንዳንድ ሰዎች “ታማኝነትና ታማኝ አለመሆን” የተሰኘውን መጽሐፌን በእጅጉ ይጠሉታል።

በታማኝነት ላይ የተጻፉ መጻሕፍት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ተራ ሰዎችን ስለ እምነት አጉዳይነት መዘዞች ያስተምራሉ። ከእንደነዚህ ትምህርቶች በኋላ ተርታው የቤተክርስቲያን አባል እምነት አጉዳይ የሆኑ መሪዎችን በቀላሉ ይለያል። አጉረምራሚና ዓመፀኛ መሪ የታማኝነትና የእምነት አጉዳይነት ትምህርቶች በሚሰጡበት ወቅት እንደታመመ አውራ ጣት ስለሚለይ በትምህርቱ ሊያብብ አይችልም።

አንድ ጊዜ በአንድ ቤተክርስቲያን እንድሰብክ ተጋብዤ ነበር። በዚያ ቤተክርስቲያን ከፊት ለፊት በመደዳ የተቀመጡ በርካታ መጋቢዎች ነበሩ። እኔም ስለ ታማኝነትና ስለ እምነት አጉዳይነት ማስተማር ጀመርሁ። ከአገልግሎቴ በኋላ ሁላቸውም በፈገግታ ፊት ስለ ስብከቱ መልካምና ነፃ አስተያየት ሰጡ።





“ተባርኬበታለሁ”፣“ጥሩ ስብከት”፣ ወዘተ የሚሉ ነገሮችን ተናገሩ። የሚያሳዝነው አንዳንዶቻቸው መልእክቱን ጠሉት። በኋላ ላይ አንደኛቸው አንድ አስተያየት ሰጠ።

“ያ ‘ታማኝነትና ታማኝ ያለመሆን’ የተሰኘ መጽሐፍ ቆሻሻ ነገር ነው” አለ።

ከመጋቢዎቹ አንዱ ደግሞ፣ “ከዚህ ሌላ የሚሰብከው ነገር የለውም?” አለ።

አሁን ሌላው፣ “የሚያውቀው ታማኝነትና እምነት አጉዳይነት ብቻ ነው?” ሲል ጠየቀ።

የሚያስደንቀው መልእክቱን የጠሉት ሁሉ እምነት አጉዳይ የሆኑ መጋቢዎች ነበሩ። በጥቂት ዓመታት ውስጥ እነዚያ እምነት አጉዳይ መጋቢዎች ቤተክርስቲያኒቱን ለቀው ሄዱ።

እውቀት ለሌላቸው ተከታዮችህ በዚያ ውስጥ ያለውን ነገር ፈጽመው እንዳያገኙት አንድን መጽሐፍ ዋጋ አሳጥቶ ማቅረብ ብልጣብልጥ ስልት ነው።

አቤሴሎም የሚለማውና የሚያብበው በሕዝቡ ድንቁርናና አለማወቅ ነው። አንተንም በገዛ ራስህ አባት ላይም እንድትነሣ በመሞከር በአባቶቻቸው ላይ በተቃውሞ ዘመቻ የሚወጡ ሰዎችን ተጠንቀቅ።

## 8. አደገኛ ልጅ የሕዝቡን ልብ ከአባቶቻቸው ይሰርቃል።

> እንዲሁም አቤሴሎም ከንጉሥ ፍርድ ሊሰማ ከእስራኤል ዘንድ በሚመጣ ሁሉ ያደርግ ነበር፤ አቤሴሎምም የእስራኤልን ሰዎች ልብ ሰረቀ።
>
> 2 ሳሙኤል 15:6

> ለዳዊትም፡- የእስራኤል ሰዎች ልብ ከአቤሴሎም ጋር ሆኖአል የሚል ወሬኛ መጣለት።
>
> 2 ሳሜኤል 15:13

አቤሴሎም ተከታይ ማግኘት ያስፈልገው ነበርና ማድረግ የሚገባውን ነገር አወቀ። በመሆኑም የሰዎችን ልብ መስረቅ ነበረበት። የሚያሳዝነው፣ አቤሴሎም የሕዝቡን ልብ የመስረቅ መብት አልነበረውም። መጽሐፍ ቅዱስ "የሕዝቡን ልብ *ሰረቀ*" በማለት የሚናገረው ለዚህ ነው።

አደገኞች ልጆች ለእነርሱ ያልሆነውን ነገር ይፈልጋሉ። አንድ መሪ ካለው ንብረት ሁሉ ለእርሱ እጅግ የሚልቀው የተከታዮቹ ልብ ነው፡ ፡ የእነርሱ ልብ ከአንተ ጋር ከሆነ፣ ያን ጊዜ ትቆጣጠራቸዋለህ ማለት ነው።

መሪነት የምትመራቸውን ሰዎች ልብ የመማረክ ጉዳይ ነው። ዳዊት፣ የእስራኤልን መንግሥት ከምንም አንሥቶ የገነባ መሪ ነበር፡ ፡ የሕዝቡ ልብ ከአቤሴሎም ጋር መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ መሸሽ እንዳለበት ተረዳ።

"አቤሴሎሞች" ብዙ ጊዜ ውቦችና ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ናቸው። የሚያሳዝነው ደግሞ "አቤሴሎሞች" ለመሆን የሚፈተኑት ተሰጥኦ ያላቸው፣ የተቀቡና ስኬታማ የሆኑ አገልጋዮች ናቸው ። አቤሴሎም ረጅም የሚዘናፈል ፀጉር ስለነበረው የተዋበ ሰው መሆኑ አያጠያይቅም።

እያንዳንዱ አንጋፋ መጋቢ "ተሰጥኦ ያላቸውን" ሰዎች በቅርበት መከታተል ያስፈልገዋል። ተሰጥኦ ሲኖርህ አደገኛ ልጅ የመሆን እውነተኛ ፈተና ይጋረጥብሃል።

ለሰው በማይገባ መንገድ እግዚአብሔር ራሱ የሚሰጥህ ስጦታ ለራስህ ወጥመድ ሊሆንብህ ይችላል። አንድ ሰው፣ "የተባረክህ ሆነህ መጽናት ትችላለህ?"ብሎ እንደጠየቀው ነው።

ቅባትህን እንደያዝህ መቀጠል ትችላለህ? ቅባትህን ለረጅም ጊዜ መጠበቅ ትችላለህ?





እምነት አጉዳይ ሳትሆን ባለ ስጦታ መሆን ትችላለህ? አቤሴሎም ሳትሆን የተባረክህ ልጅ መሆን ትችላለህ?

ትዕቢተኛ ሳትሆን ሀብታም ባለጸጋ መሆን ትችላለህ?

ልባቸውን ሳትሰርቅ ወደ ሕዝቡ መቅረብ ትችላለህ?

የሆነ ሰው እርሱን ሳትገለብጠው በቤተክርስቲያኑ በኃላፊነት ስፍራ ሊያስቀምጥህ ይችላል?

አንድ ሰው የመሠረተውን ቤተክርስቲያን የሕዝቡን ልብ ሳትሰርቅ ለአንድ ዓመት በአንተ ኃላፊነት ሥር ሊተው ይችላል?

ተሰጥኦህ እንዲያጠምድህ አትፍቀድ። በመጨረሻ አቤሴሎም ተማርኮ የተገደለው በረጅም፣ በሚዘናፈል ፀጉሩ ምክንያት ነበር። የሚያጠፋህ እግዚአብሔር የሰጠህ በረከት ራሱ ሊሆን ይችላል። ይህ እንዴት የዕለት ተዕለት ተግባር እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። "አቤሴሎም ከዳዊት ባሪያዎች ጋር በድንገት ተገናኘ። አቤሴሎምም በበቅሎ ተቀምጦ ነበር፣ በቅሎውም ብዙ ቅርንጫፍ ባለው በታላቅ ዛፍ በታች ገባ፣ ራሱም በዛፉ ተያዘ፤ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠለጠለ፣ ተቀምጦበትም የነበረ በቅሎ አለፈ።" (2 ሳሙኤል 18፡ 9)።

## 9. አደገኛ ልጅ የአባቱን ተድላዎችና ጥቅሞች ይፈልጋል።

> ለአቤሴሎምም በሰገነት ላይ ድንኳን ተከሉለት፤ አቤሴሎምም በእስራኤል ሁሉ ፊት ወደ አባቱ ቁባቶች ገባ።
>
> 2 ሳሙኤል 16:22

የአባት ጥቅሞች ልዩ ናቸው። እግዚአብሔር ለአባቶች የሰጠውን ጥቅም ማክበር አስፈላጊ ነው። የአባቱን ጥቅሞች የሚመኝ ልጅ እውነተኛ አቤሴሎም ነው። ብዙ አገልጋዮች አገልግሎቶቻቸውን እንዲጀምሩ እግዚአብሔር እንደመራቸው ይናገራሉ። በእርግጥ፣ ከእነዚህ አንዳንዶች የአባታቸውን ጥቅሞች ሊደሰቱባቸው የሚሹ "አቤሴሎሞች" ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ባላቸው ነገር አይረኩም። ስለሆነም ሌላው ሰው ወፋፍራም ጥቅሞችን ሲያገኝ እኛ ለምን የበይ ተመልካች እንሆናለን የሚል ጥያቄ ያነሣሉ።

እግዚአብሔር የራስህን አገልግሎት እንድትጀምር ጠርቶህ ከሆነ፣ እባክህ የአንጋፋ መጋቢዎችን ተድላና ጥቅሞች የምትመኝ ሌላኛው አቤሴሎም አለመሆንህን አረጋግጥ። የግያዝና የአቤሴሎም መንፈስ በዚህ ነጥብ ላይ ጥምረት ይፈጥራሉ።

ግያዝ ብዙ ጥቅሞችን ሲፈልግ አቤሴሎም ግን የአባቱን ቁባቶች ተመኘ። "አቤሴሎሞች" ብዙ መኪናዎችን፣ ቤቶችንና ገንዘብ ይፈልጋሉ። ታላቅ መሆን ይፈልጋሉ፣ ይህንንም በፍጥነት መጨበጥ ይፈልጋሉ።

*"ለእውነት" ተጋድሎ እየተባለ የሚነገርለት ብዙ ጊዜ የጥቅም ተጋድሎ ሆኖ ይገኛል።* ለእውነት እንጋደላለን ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም እንጋደላለን በሚል ሽፋን ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚጋደሉት ለበለጠ ጥቅምና ተድላ ነው። ይቅር ይበላቸው!

## 10. አደገኞች ልጆች አጥፊ አዝማሚያ አላቸው።

> አቤሴሎምም ወደ ንጉሡ ይልከው ዘንድ ወደ ኢዮአብ ላከ፤ ወደ እርሱም ሊመጣ አልወደደም፤ ሁለተኛም ላከበት፤ ሊመጣ ግን አልወደደም። ባሪያዎቹንም፣ በእርሻዬ አጠገብ ያለውን የኢዮአብን እርሻ እዩ፤ በዚያም ገብስ አለው፤ ሂዳችሁ በእሳት አቃጥሉት አላቸው። የአቤሴሎምም ባሪያዎች እርሻውን አቃጠሉት።
>
> 2 ሳሙኤል 14:29-30

አቤሴሎም የእርሱን አጽንኦት ያገኝ ዘንድ የኢዮአብን እርሻ አቃጠለ፡ ፡ ወደፈለገበት ለመድርስ የማይፈነቅለው ድንጋይ አልነበረም። በዚህ የኢዮአብን እርሻ በማቃጠል ተግባሩ በአቤሴሎም ውስጥ ያለውን ጭካኔ ማየት ትችላለህ። ጨካኝ ሰው አደገኛ ሰው ነው። ለሥልጣን ካላቸው ጥማት የተነሣ ምንም ነገር ከማድረግ አይመለሱም።





ወዳሰቡበት ለመድረስ መላውን አገልግሎት ወይም የአባቶቻቸውን ስም ቢያቃጥሉ ደንታ አይሰጣቸውም።

## 11. አደገኞች ልጆች ሴራን፣ ምስጢራዊ ግንኙነቶችንና የጎን ዱለታዎችን በማካሄድ ይታወቃሉ።

> አቤሴሎምም የዳዊት መካር የነበረውን የጊሎ ሰው አኪጦፌልን ከከተማው ከጊሎ መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ አስጠራው። ሴራውም ጽኑ ሆነ፤ ከአቤሴሎምም ጋር ያለ ሕዝብ እየበዛ ሄደ።
>
> 2 ሳሙኤል 15:12

አቤሴሎም በርካታ የምስጢር ስብሰባዎችን ከአኪጦፌልና ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር አካሄደ። እነዚህ የምስጢር ስብሰባዎች ጠንካራ የሆነ ሴራ ለማካሄድ አስፈላጊ ነበሩ። አጠገባቸው እያለህም እንኳ ማሾክሾክ የሚወዱ ሰዎች አሉ። የሚሉት ሁሉ የማይመለከትህ ፈጽሞ ላይመስል ይችላል! ታማኝ ተከታዮች በሚባሉት ውስጥ ሴራዎች መኖራቸውን መመርመርና መለየት አስፈላጊ ነው።

የአንድ ተልእኮ ስኬት ከአንተ ጋር ባሉት ሰዎች ታማኝነት ላይ ይመረኮዛል። ታማኝነት እንዲሰፍን ተጋደል።

ከመደበኛው ስብሰባ በኋላ ስብሰባዎችን በሚያካሂዱት ሰዎች ላይ ዓይኖችህን ከፍተህ ተከታተል።

በጎን ሆነው ሌላ ማንም ሰው በማይገባው የግል ቀልዶች ውይይቶችን የሚያካሂዱትን ሰዎች ተጠንቀቅ። እነዚህ ሁሉ ከአንተ የተደበቀ መረጃ ስለመኖሩ ምልክቶች ናቸው።

## 12. አደገኞች ልጆች በተከታዮቻቸው ታማኝነትን የማስረፅ ብቃት ማነስ አለባቸው።

አደገኞች ልጆች ታማኝነትን የማስረፅ ብቃታቸው የተሰለበ ስለሆኑ በአገልግሎታቸው ለወድቀት የተመደቡ ናቸው። የታማኝነት የዘር ቋታቸው የተወገደ ስለሆነ ታማኝ ተከታዮችን የሚያመነጭ ዘር የላቸውም።

አባትህን ለመግደል የሕዝብ ሰራዊትን ከመራህ በኋላ እንዴት አድርገህ በአባትነት ተደላድለህ ትኖራለህ?

ዋነኛው የታማኝነትና የመስጠት መሠረትህ ድባቅ ተመትቷል። አንተ የመራሃቸው ሕዝብ የገዛ አባትህን ስትደመስስ አይተውሃል። *የጻፉና እግዚአብሔር የሾማቸው መሪዎች ሲገለበጡ በምሳሌ ተምረዋል።*

## *መሠረቶችን መናድ*

የአንድን ቤተ እምነት ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያን ገልብጦ የያዘ አንድ መጋቢ መጎብኘቴን አስታውሳለሁ። የቤተክርስቲያኑን የመጀመሪያ ስም በቀለም አጥፍቶ አዲስ ስም ሰጥቶት ነበር።

መላውን ቤተክርስቲያን፣ ንብረቶቹንና ምእመኑን ጭምርበቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ፣ ከግብረአበሮቹ ጋር ሆኖ በቤተ-እምነት ዋና መሥሪያ ቤት ላይ በመመሳጠር ዓመፅ አካሄደ።

ይህን ወዳጄን፣ "እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋለህ?" ብዬ አፋጠጥሁት።

በስብሰባው አዳራሽ ከእርሱ ጋር ቆሜ "ያ የአንተ አትሮንስ አይደለም፣ ደግሞም እነዚህ የአንተ ወንበሮች አይደሉም።" አልሁት፡ ፡

በመቀጠልም፣ "ቤተክርስቲያንን በዚህ ዓይነት መንገድ መንጠቅ ትክክል አይደለም።" አልሁት።

ነገር ግን እርሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው በሚል ግትር አቋሙን አስተጋባ።

"ዋናው ኃላፊያችን ወደኋላ የተመለሰ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ አቁሞአል። የሚያነበው 'አቲላ ዘ ሃን' የሚሉትን ዓይነት እንግዳ የሆኑ መጻሕፍትን ነው" ብሎ ሊያስረዳኝ ሞከረ።

"አቲላ ዘ ሃን ምንድን ነው?"ብዬ ጠየቅሁት።





እርሱም፣ "እኔ ራሴም ብሆን አቲላ ዘ ሃን ምን እንደሆነ አላውቅም፣ ምክንያቱም ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር እንደነዚህ ያሉ መጻሕፍትን አላነብም" አለኝ።

ከዚያም ቀጠለና፣ "ና፣ አንድ ነገር ላሳይህ" አለኝ።

ከዚያም ወደ ውጭ ወሰደኝ። ከፋብሪካ የወጣ አዲስ፣ የሚያብረቀርቅ፣ ጥቁር በጀርመን አገር የተሠራ መኪና ቆሞ ነበር። እንዲህም አለኝ፣ "መገልበጤን የሰማ ሰው እኔን ለማበረታታት፣ ይህን አዲስ መኪና ገዝቶ እንደ ስጦታ ላከልኝ። ይህን ያደረገው ስለሠራሁት መልካም ሥራ 'አመሰግንሃለሁ' ለማለት ነበር።"

በዚህ ውብ መኪና አጠገብ እንደቆምን፣ መጋቢው ወደ እኔ ዞር አለና ፊቴን እያየ፣ "ታዲያ ይህ ዲያብሎስ ሊሆን ይችላል? ይህን ያደረገው በሥራ ላይ ያለ እግዚአብሔር አይደለምን? ዲያብሎስ እንዲህ ያለ ውብና ውድ መኪና ይሰጠኛል?" በማለት ጠየቀ።

ለእርሱ፣ የዚህ አዲስ መኪና ዱብዕዳ ስጦታ ትክክለኛ ነገር ለማድረጉ ማረጋገጫ ነበር።

ከዚያም እኔ፣ "ይህን አዲስ ቤተክርስቲያን እንዴት አድርገህ ነው የምትመራው?" ብዬ ጠየቅሁት።

እርሱም፣ "እኔ መጋቢ ነኝ፣ ነገር ግን በዙሪያ ያሉ ሌሎችም የመሪነቱን ድርሻ ይጋራሉ። የቀድሞ ኃላፊዬ እንዳደረገው የአንድ ሰው መድረክ አላደርገውም።"

"እኔ የተለየሁ ዓይነት መሪ እሆናለሁ" ብሎ መለሰልኝ።

ከዚያ ስንለያይ፣ ይህ ወንድም የጥንካሬ፣ የመሪነትና የታማኝነት መሠረቶችን እንደናደ አወቅሁ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ተባባሪ መጋቢዎቹ ከእነርሱ እንዲለይ ነገሩት፡ ፡ በእርሱ ላይም የተለያዩ ክሶችን መሥርተው እንዲሄድ በሩን አሳዩት። ለዚያ ቤተክርስቲያን ምንም ዓይነት መሠረት ስላልጣለ በተባባሪዎቹ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን አጣ። አሁን ራሱ

በቶሰቶሰውን የዓመፅ ማዕበል ውስጥ የሚቆምበት ዓቅም አልነበረውም።

## መከርን ለማጨድ መዳረግ

በዙሪያህ ያሉ ሰዎች ባያምፁም እንኳ፣ የዘራኸውን ለማጨድ ግን ትገደዳለህ። ገላትያ 6፡7 ላይ እንዳለው ካሉህ መልካም ስብከት፣ መልካም መርሆች፣ ወብ መልክና የብልጠት ስልቶች በተፃራሪ ይሠራብሃል። ነገሩ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። አስር ዓመታት ሊወስድ ይችላል፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ አይዋሽም።

አቤሴሎምን በተመለከተ፣ የዘራውን ያጨደው ወዲያውኑ ነው ማለት ያስደፍራል። በመጀመሪያው የካቢኔ ስብሰባው፣ በስሕተት ታማኝ ያልሆነ ሰውን ዋነኛ አማካሪው አድርጎ መረጠ።

እግዚአብሔር አቤሴሎምን ለማጥፋት ስለወሰነ ጌታ አቤሴሎም ታማኝ ያልሆነ ሰውን ምክር እንዲመርጥ አቀናበረ።

አኪጦፌል የሴራው አንዱ አካል ሆኖ ለወራት ምናልባትም ለዓመታት የሠራ ሰው ነበር። አርካዊው ኩሲ የዳዊት ታማኝ ወዳጅ የነበረ ሲሆን አቤሴሎምን ሊያስት በአቤሴሎም ጎራ የተመደበ ሰው ነበር። አቤሴሎም አባቱ የሁለቱን ቁንጮ ብልኅ ሰዎች ማለትም የአርካዊውን ኩሲና የጊሎ ሰው የአኪጦፌልን ምክር እንደሚተማመን ያውቅ ነበር። በዚያች ጠንቀኛ ሌሊት አቤሴሎም የረጅም ጊዜና ታማኝ አማካሪውን የአኪጦፌልን ምክር ላለመቀበል መምረጡን ማመን ትችላለህ? አቤሴሎም በውጊያው እንዲረታ ያደረገው ነገር ይህ ብቻ ነው። ታማኝ ያልሆነ ሰውን እንደ ቀኝ እጁ አድርጎ መረጠ።

## ኩሲ፡ የአቤሴሎም እምነት አጉዳይነት መከር

ነፋስን ዘርተዋል፤ ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ አገዳ የለውም፤ ከፍሬውም ዱቄት አይገኝም፤ ቢገኝም እንግዶች ይበሉታል።

ሆሴዕ 8፡7





"አቤሴሎም" ከሆንህ፣ እግዚአብሔር ክፉን እንድትመርጥ ያደርግብሃል። ምክንያቱም አንተም ለሌላ ሰው ክፉ ስለነበርህ ነው። ሳታውቅ ክፉና ታማኝ ያልሆኑ ሰዎችን ትመርጣለህ። ውሸታሞችና ሌቦች ዙሪያህን ከበው ዳንኪራ ይረግጣሉ። ገንዘብህን የሚቆጥሩና የሚቆጣጠሩ ሰዎች ያለማቋረጥ ስለሚሰርቁት ገንዘብህ ፈጽሞ በቂ አይሆንልህም።

አጭበርባሪ ሴቶች፣ ከሞት እጅግ የመረሩ፣ ሕይወትህን ድባቅ እንዲመቱ ይላኩብሃል። ምሕረት ያምጣልን! ከእግዚአብሔር ቅጣቶች አንዱ ይህ ነው፡ "እኔም ከሞት ይልቅ የመረረ ነገር መርምሬ አገኘሁ፤ እርስዋም ልብዋ ወጥመድና መርበብ የሆነ፣ ደጆችዋም እግር ብረት የሆኑ ሴት ናት፤ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነ ከእርስዋ ያመልጣል፣ ኃጢአተኛ ግን ይጠመድባታል፡ ፡" (መክብብ 7፡26)

የሂሳብ ሠራተኞችህ ጠንቋዮች ይሆናሉ። ሳታውቅ ሟርተኞችን በአገልግሎትህ እንዲረዱህ ትቀጥራለህ። ይህም አንተ በተቀጠርህ ጊዜ፣ ለአሠሪህ ሟርተኛና ጠንቋይ ስለነበርህ ነው። *በመጥፎ ሰውና በመልካም ሰው መካከል ምርጫ በሚኖርበት ማናቸውም ጊዜ ምርጫህ መጥፎ ሰው ላይ ይሆናል።* ትክክል ያልሆነ ባል ትመርጫለሽ፣ ትክክል ያልሆነች ሚስት ትመርጣለህ። ታማኝ ሰው ስላልሆንህ ለተቀረው የሕይወት ዘመንህ ሁሉ ቅጣትና ወጥመድ ይሆንብሃል።

መልካም መኪናና ጉድለት ያለበት መኪና ቢኖር፣ ሁልጊዜም ጉድለት ያለበትን ትመርጣለህ፣ ምክንያቱም አንተም በተመርጥህ ጊዜ ለመራጭህ ክፉ ሆነህበታልና። መልካም ሰውና ክፉ ሰው ቢኖሩ፣ ሁልጊዜም ክፉውን ሰው ትመርጣለህ። ለወደደህ ሰው አንተም ወጥመድ ስለነበርህ ለራስህ ክፉ ነገሮችን ትመኛለህ፤ ደግሞም ወጥመዶችንና መሰናክሎችን ትመርጣለህ።

የእምነት አጉዳይነትህንና የተንኮልህን መቶ እጅ ትቀበላለህ። ነፋስን የሚዘራ ዐውሎ ነፋስን ያጭዳል!

ብዙ ሰዎች አብረዋቸው የሚሠሩትና የሚደገፉባቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር ለእነርሱ የተሰጡ መሆናቸውን አይገነዘቡም። *አቤሴሎም እጅግ የላቁ ምርጫዎች የነበሩት ሲሆን፣ ነገር ግን ትክክል ያልሆኑትን ለመምረጥ ተዳረገ።* ይህም እርሱ ራሱ ለአባቱ "ትክክል ያልሆነ" ልጅ ስለነበር ነው።

እግዚአብሔር የማይጎዱኝን መልካም ሰዎች እንድመርጥ እንዲመራኝ ሁልጊዜ እጸልያለሁ። መዝራትና ማጨድ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል መርሆች ናቸው። ለእግዚአብሔር እየሠራሁ ነኝ የሚል ማናቸውም ሰው ይህን ሕግ ማክበር ይገባዋል።



## ምዕራፍ 9

# አርቀው የማያዩ ልጆች

እንዲህም አለ፦ አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት።

ከእነርሱም ታናሹ አባቱን አባቴ ሆይ፣ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው።

ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፣ . . .

ሉቃስ 15፡11-13

አባት ማን እንደሆነ ባላቸው ግንዛቤ አርቀው የማያስቡ ልጆች መኖራቸው ግልጽ ነው። በዚህ ምዕራፍ አርቀው የማያስቡ ልጆች ባሕርያት ናቸው ብዬ የማምናቸውን ላካፍልህ እወዳለሁ።

1. **አርቆ የማያይ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት የዕድሜ ልክ ሳይሆን በጊዜ እንደተገደበ የኮንትራት ግንኙነት የሚያይ ሰው ነው።**

አርቆ የማያስብ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ሊያልፍበት የሚገባው የአጭር ጊዜ ግንኙነት አድርጎ ያያል። ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ለሦስት ዓመት ኮርስ በዩኒቨርስቲ ቆይታው የገጠመውን ሌክቸረር በትዕግሥት ማለፍ ግድ ከሆነበት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ አድርጎ ይቆጥረዋል። ይህ ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ከሚኖራቸው ዘላቂና ቀጣይ ግንኙነቶች ጋር በአንፃራዊነት የሚፈረጅ ነው።

### አባት ዛፍ ነው

ከረጅም ዘመን በፊት፣ እንድ ትልቅ የማንጎ ዛፍ ይኖር ነበር። አንድ ትንሽ ልጅ ሁልጊዜ እየመጣ በዙሪያው መጫወት ይወድ ነበር። ዛፉ ላይ መውጣትና ፍሬውንም መብላት፣ ከዚያም ከጥላው በታች

ሸለብታ መውሰድ ያዘወትር ነበር። ይህ ልጅ ዛፉን ይወድ ነበር፤ ዛፉም ከእርሱ ጋር መጫወትን ያስደስተው ነበር።

ጊዜ አለፈና ትንሹ ልጅ አደገ። በዛፉ ዙሪያ ሁልጊዜ መጫወቱን አቆመ። አንድ ቀን ይህ ልጅ እያዘነ ወደ ዛፉ ተመልሶ መጣ። በዚህ ጊዜ ዛፉ ልጁን "ና ከእኔ ጋር ተጫወት፣" አለው።

ልጁ ግን፣ "እኔ አሁን ሕፃን ልጅ አይደለሁም፤ በዛፎች ዙሪያ መጫወቱን ካቆምሁ ቆይቻለሁ፣" በማለት መለሰለት። አሁን ግን "አሻንጉሊቶች እፈልጋለሁ። እንድገዛቸውም ገንዘብ እፈልጋለሁ" አለ።

ዛፉም፣ "አዝናለሁ፣ እኔ ገንዘብ የለኝም . . . ሆኖም ግን ፍሬዎቼን ለቅመህ መሸጥ ትችላለህ። ከዚያም ገንዘብ ይኖርሃል" አለው። ልጁም በጣም ተደሰተ። በዛፉ ላይ የነበሩትን ፍሬዎች ሁሉ ሸምጥጦ ከለቀመ በኋላ ደስ እያለው ሄደ። ያ ልጅ የማንጎ ፍሬዎችን ከለቀመ በኋላ አልተመለሰም። በዚህ ጊዜ ዛፉ ብቸኝነትና ሐዘን ተሰማው።

አንድ ቀን ግን ልጁ ሲመለስ ዛፉ በጣም ተደሰተ። ከዚያም፣"ናና ከእኔ ጋር ተጫወት፣" አለው። "ለመጫወት ጊዜ የለኝም። ለቤተሰቤ መሥራት አለብኝ። መጠለያ የሚሆን ቤት ያስፈልገናል። ልትረዳኝ ትችላለህ?" ሲል ጠየቀው።

"አዝናለሁ ቤት የለኝም። ነገር ግን፣ ቅርንጫፎቼን ቆራርጠህ ቤት መሥራት ትችላለህ።" ከዚያም ያ ልጅ ቅርንጫፎቹን ሁሉ ቆራርጦ ደስ እያለው ወደ ቤቱ ተመለሰ። ዛፉም ልጁ ሲደሰት ማየት አስደሰተው። ነገር ግን አሁንም ልጁ ተመልሶ ሊጠይቀው አልመጣም።

በዚህ ጊዜ ዛፉ ብቸኝነትና ሐዘን ተሰማው። አንድ ሞቃታማ የበጋ ቀን፣ ልጁ ተመልሶ በመምጣቱ ዛፉ በጣም ደስ አለው። ከዚያም፣ "ናና ከእኔ ጋር ተጫወት!" አለው።





ነገር ግን ልጁ፣ "አዝናለሁ፣ አሁን ትልቅ እየሆንሁ ነኝ። በውኃ ላይ በመንሳፈፍ ራሴን ለማዝናናት እፈልጋለሁ። ጀልባ ልትሰጠኝ ትችላለህ?" አለው።

ደጉ ሽማግሌ ዛፍም እንዲህ አለ፣ "ጀልባ ለመሥራት ግንዴን መጠቀም ትችላለህ። ወደ ሩቅ አካባቢ እየተንሳፈፍህ በመሄድም ልትደሰት ትችላለህ"አለው። ከዚያም ልጁ በዛፉ ግንድ ጀልባ ለመሥራት ቆረጠ። በመጨረሻም በጀልባ ተንሳፎ ሄደ፣ ከዚያም ለብዙ ዓመታት አልተመለሰም።

ከዓመታት በኋላ ልጁ እንደገና ወደ ዛፉ ተመልሶ መጣ።

"አዝናለሁ፣ ልጄ፣ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲያ ለአንተ የሚሆን ምንም ነገር የለኝም። ማንጎ ከእንግዲህ ወዲያ አይኖርህም . . ." በማለት ዛፉ መለሰለት።

"እኔም ብሆን የምገምጥባቸው ጥርሶች የሉኝም፣" በማለት ልጁም መለሰ።

ከዚያም ዛፉ እንዲህ አለ፣ "ወጥተህ የምትጫወትበት ግንድ የለኝም።"

ልጁም "እኔም አሁን ያን ለማድረግ በጣም አርጅቻለሁ" በማለት መለሰ።

ከዚያም ዛፉ ዕንባውን እያፈሰሰ፣ "እንግዲያውስ ምንም ነገር ልሰጥህ አልችልም . . . የቀሩኝ ነገሮች ቢኖሩ እየሞቱ ያሉ ሥሮቼ ናቸው" አለ።

ልጁም፣ "ለማረፊያ የሚሆን ስፍራ ካልሆነ በቀር አሁን ብዙ ነገር አያስፈልገኝም። ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ ድካም ተጫጭኖኛል" አለ።

ዛፉም፣ "የአሮጌ ዛፍ ሥሮች ለማረፍና ለመደገፍ እጅግ ምቹዎች ናቸው"ብሎ መለሰለት። ልጁም ቁጭ አለ፣ ዛፉም በጣም ደስ ብሎት በዕንባው መካከል ፈገግ አለ።

ዛፉ አባት ነው። ልጆች ሆነን እያለን ከእርሱ ጋር መጫወት እንወድ ነበር። ባደግን ጊዜ ግን የሆነ ነገር ለመፈለግ ወይም ችግር ውስጥ ስንገባ ብቻ ካልሆነ በቀር ትተን ከሄድንበት አንመለስም። አባቶች ምንም የሚሰጡት ነገር የላቸውም ብለው ለሚያስቡ ልክን ለማያውቁ ልጆች በመላው የሕይወት ዘመን፣ በሚለዋወጡ የሕይወት ምዕራፎች ሁሉ አባቶች ሚና አላቸው። ልክን ያልተረዱና አርቀው የማያዩ ልጆች፣ "አባቴ ዘመን አልፎበታል። እርሱ ከዘመኑ ጋር አብሮ አይሄድም" ይላሉ። ነገር ግን ጊዜ፣ የአየር ጠባይ፣ የሕይወት ጭብጦችና እውነታዎች እንደነዚህ ላሉ ሰዎች ሁሉ የሚገልጡት፣ አባት ለዘላለም አባት እንደሆነ ነው።

2. አርቆ የማያስብ ልጅ አባቱን ዘመን ያለፈበት ሰው አድርጎ ይመለከተዋል።

ብዙ አባቶች የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ እንዳለው ምግብ፣ ወይም ጊዜው እንዳለፈበት፣ ወይም ተዛማጅነት እንደሌለው ነገር ተደርገው ይታያሉ። ነገር ግን አባት ምንም ጊዜም ፈጽሞ ተዛማጅነቱን አያጣም። እንዲያውም ጊዜ እያለፈ በሄደ መጠን አባቶች ይበልጥ ተዛማጅነታቸው እየጨመረ ይሄዳል። አእምሮህ ክፍት ከሆነና ትሑት መንፈስ ካለህ አባት ጊዜው ያለፈበትና ተዛማጅነቱ ያበቃ አለመሆኑን ትረዳለህ።

> ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፣ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው።
>
> ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡22-23

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገሩ ብዙዎቹ በረከቶች በአባቶች አማካኝነት በመጨረሻው ዕድሜያቸው የተሰጡ ነበሩ። ባረጁ ተሰናባች አባቶች የተነገሩ ቃሎች የተለያዩ ትውልደ-ሕዝቦችን ነክተዋል። ይስሐቅ በዕድሜው መጨረሻ ላይ ስለ ልጆቹ ትንቢት ተናገሯል። በግልጽ እንደሚታየው ይስሐቅ ከልጆቹ ሕይወት ጋር





ተዛማጅነቱን ያጣ ሰው አልነበረም። ተዛማጅነቱ ያለፈበት ቢሆን ኖሮ የተናገረው ትንቢት ባልተፈጸመ ነበር።

3. አርቆ የማያይ ልጅ ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመለከተው ከሚያገኛቸው የተወሰኑ "ድርሻዎች" አኳያ ነው።

በእርግጥ አርቆ የማያይ ልጅ ከአባቱ ስለሚያገኛቸው ነገሮች ያለው ግንዛቤ ውስን ነው። ኮብላዩ ልጅ ከአባቱ የሄደው የሚገባውን "ድርሻውን"ጠይቆ ከወሰደ በኋላ ነበር።

አንዳንድ ልጆች ከአባታቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከገንዘብ አኳያ ወይም ከሚቀበሉት ነገር ይመዝኑታል። ከዚህም የተነሣ ከአባታቸው በሚገኝ እውነተኛ በረከት ሳይባረኩ ይቀራሉ። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ልጆች ወላጆቻቸውን የትምህርት ቤት ክፍያዎቻቸውን የሚከፍሉ ሰዎች አድርገው ያዩአቸዋል። ከትምህርት ቤት ክፍያ ውጭ ከአባታቸው ምንም አይፈልጉም ወይም አይጠብቁም። በዚህ ታሪክ ውስጥ እንዳለው ልጅ ወላጆቻቸውን ውርስ እንደሚሰጡ ሰዎች አድርገው የሚመለከቱ ሌሎች ደግሞ አሉ። ውርስ ከአባታቸው ሲቀበሉ የሚችሉት ብቸኛና ዋጋ ያለው ነገር አድርገው በማየት ፍላጎታቸው ለዚያ ብቻ ይሆናል። አንዳንድ ልጆች ያላቸውን መውረስ እንዲችሉ ወላጆቻቸው እንዲሞቱላቸው እንኳ ይመኛሉ።

ከዚህ ዓይነቱ ቅርብ-አደር አመለካከታቸው የተነሣ አባት በልጁ ሕይወት ውስጥ የሚያመጣውን፣ ብዙም የማይታይ ሆኖም ግን ይበልጥ ታላቅ የሆነውን ነገር ያጣሉ።

4. አርቆ የማያይ ልጅ አባት በመኖሩና በበጎ ተጽእኖው አማካኝነት የሚያበረክተውን የማይታየውን፣ የማይጨበጠውን ድርሻ አይመለከትም።

አባት ወደ ልጁ ሕይወት የሚያመጣቸው ብዙ የማይታዩና የማይጨበጡ ነገሮች አሉ። የአባትህ ሚና የትምህርት ቤት

ክፍያዎችን መክፈል ነው ብለህ ስታስብ የቱን ያህል ቅርብ ተመልካች መሆን እንደምትችል በገባህ!

ያ ከብላዩ ልጅ የአባቱን ጠቀሜታ በውርስ ድርሻ ብቻ ሲወስን የቱን ያህል ቅርብ ተመልካች ነበር! በዚህ በውርስ ድርሻው ምን ነበር ያደረገው? በውርስ ድርሻው በለጸገን? በውርስ ድርሻው ስኬታማ መሆን ቻለን? ያን የውርስ ድርሻ በመቀበሉ ሕይወቱ ተለውጦአልን?

በእርግጥ አይደለም! ምንም እንኳ ሙሉውን የውርስ ድርሻውን ይዞ ቢሄድም፣ነገር ግን ይበልጥ ድሃና ሁሉን ያጣ ሆነ፡፡ በግልጽ አባቱ የነበረውና እርሱም ያልተቀበላቸው የተወሰኑ ያልታዩና ያልተጨበጡ ነገሮች ነበሩ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የውርስ ድርሻውን የያዘ ቢሆንም አባቱ ሊሰጠው የሚገባውን ጥበብና ብስለት አልተቀበለም ነበር፡፡ የአባት ጥበብ፣ አርቆ ማስተዋልና ልቡና ሳይኖር ገንዘብ ብዙ ጊዜ ምንም ውጤት አያስገኝም፡፡

አባት የትምህርት ቤት ክፍያዎችን የሚከፍል ብቻ አይደለም፡፡ አባት ጽናትን፣ ጥበብን፣ አቅጣጫን፣ በጎ ተጽእኖን፣ አመራርን፣ ዋስትናን፣ ደህንነትንና ሑልቁ መሳፍርት የማይደዳሰሱ በረከቶችን ይሰጣል፡፡

5. አርቆ የማያይ ልጅ ከአባቱ ማግኘት የሚችለውን ሁሉ እንደተቀበለ በችኮላ የሚያስብ ሰው ነው፡፡

አርቆ የማያይ ልጅ ገና ጊዜው ሳይደርስ ከእትብት ራሱን የሚያላቅቅ ልጅ ነው፡፡ አባቱ ሊሰጠው የሚችለውን ነገር ሁሉ እንደተቀበለ አድርጎ ለመደምደም ፈጣን ነው፡፡

አባቶቻቸው ያካበቷቸውን ትምህርቶች ሁሉ እንደተቀበሉ የሚሰማቸው ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ በውስጣቸው፣ "እርሱ የሚያስተምረውን አውቃለሁ፡፡ ምን እንደሚናገር አውቃለሁ፡፡ የሚያደርገውንም አውቃለሁ፡፡" የሚሉ ብዙ ሰዎች ገጥመውኛል፡፡





"እንዴት አወቅህ?" ብለህ ልትጠይቀኝ ትችላለህ፡፡ አንተንና ስለ አንተ ሁሉን ነገር እናውቃለን ከሚሉ ሰዎች ጋር ስትሆን አንድን ነገር መገመት በዓለም ቀላሉ ነገር ነው፡፡

ሰይጣን ለኢየሱስ ይህንኑ ማለቱን አስታውስ፣ ". . . ማን እንደሆንህ አውቄአለሁ" (ሉቃስ 4:34)፡፡ ርኩሳን መናፍስት በልጆች ላይ ተለጥፈው አባቶቻቸውን እንዲተዉ የሚያነሣሡት ወይም ሥርዓት በጎደለው መንገድ ቤትን ትተው እንዲሄዱ የሚያደርጉበት በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ነው፡፡

ስለ እኔ ሁሉን ነገር እንደሚያውቁ የሚያስቡ መጋቢዎችን ብዙ ጊዜ ልብ እላለሁ፡፡ ተቀብለናል ብለው የሚያስቡትን ድርሻ ለማባከንና መና ለመቅረት ብቻ ከእኔ ይዘው ሲሄዱ በውስጤ እስቃለሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አባት የተወሰነውን ድርሻ ይሰጥና ነገር ግን በመጨረሻ ለመስጠት የሚያስበውን ያስቀራል፡፡ ይስሐቅ ቀደም ባለው ዕድሜ ዘመኑ ለመስጠት ያልተጨነቀበትን በዕድሜው መጨረሻ ላይ ለልጆቹ ሰጥቷል፡፡ አባትህ ካለው ማናቸውም እውቀትና ጥበብ ጋር ሄጃለሁ ብለህ ስታስብ ምን ያህል ጨቅላና አእምሮ-ጠባብ ነህ፡፡

## የካራቴ አዋቂ

አንድ ጊዜ የሁሉም ክፍለ-ግዛቶች አሸናፊ የነበረ አንድ እውቅ የካራቴ ባለ ድል ነበር፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምቶችን፣ እርግጫዎችን፣ የጉልበትና የክርን ድቀሳዎችን በመጠቀም የታወቀ ሰው ነበር፡፡ ደግሞም እንደ ጩቤ አጠቃቀም በመሳሰሉ አንድ መቶ የክፍት እጅ ብልሃቶች የታወቀም ነበር፡፡ በተጨማሪም አንድ መቶ የሚሆኑ ትግሎችን፣ ማፈግፈጎችንና ግፍተራዎችን ያውቅ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ የድል ማድረጊያ እርምጃው የሆኑ አስር የደካማ ብልት ምቶች ነበሩት፡፡ እነዚህ አንድ ላይ ተዳምረው ሦስት መቶ አስር ቁልፍ የካራቴ ማጥቂያ እርምጃዎቹ ነበሩ፡፡

ሦስት መቶ ዘጠኝ ዘዴዎችን ያስተማረው አንድ በልዩ ሁኔታ የሚወደው ተማሪ ነበረው። ለምን እንደሆነ ባይታወቅም የመጨረሻውን ቁልፍ የማጥቂያ ዘዴ ፈጽሞ ሳያስተምረው አለፈ።

ወራት እንዳለፉ አለቃውንም እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ማሸነፍ እንደሚችል በኩራት እስኪናገር ድረስ ተማሪው በካራቴ እጅግ በጣም ጥሩ ውጤት ማሳየት ጀመረ። በእርግጥ አለቃውን ለማሳፈር የማይፈልገው ለዕድሜው ካለው አክብሮትና ስለሰጠው ትምህርት ከሚሰማው ውስታ የተነሣ እንደሆነም ተናገረ።

በጊዜ ሂደት አለቃው ስለ ተማሪው ጉራ ሰምቶ ለዚህ ደቀመዝሙሩ አንድ ትምህርት ለማስተማር ወሰነ። ከተማሪው ጋር ግጥሚያ ለማድረግ ራሱን አቀረበ። ከዚያም አለቃውን ሊያሸንፍ የሚችል ብቸኛውን ወጣት ለማየት ሕዝብ ተሰበሰበ።

የጀምር ደወል ሲሰማ ደቀመዝሙሩ ወደ አለቃው ተንደርድሮ ሲሮጥ ያልተለመደ ሦስት መቶ አስረኛ የካራቴ ምት ተቀበለው። አለቅዬው የቀድሞ ተማሪውን ከራሱ በላይ አንሣና ከአድማጮች በሚስተጋባው ጩኸት መካከል በደረቱ ዘረረው።

በኋላም፣ እንዲህ ያለውን ጠንካራ ወጣት እንዴት ማሸነፍ እንደቻለ ሲጠየቅ፣ እንዲህ ላለ ቀን ሦስት መቶ አስረኛውን ብልሃት ለራሱ እንዳቆየ ተናገረ።

በእርግጥ በመጨረሻ መማር የሚችሉት ብዙ ነገር መቅረቱን ተገንዝበው እስከሚደነቁ ድረስ መማር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሚጠው እንደተማሩ የሚያስቡ ብዙ ልጆችና ደቀመዝሙሮች አሉ።



*ምዕራፍ 10*

# አባቶችን በማክበር የሚገኙ ሦስት ሽልማቶች

ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።

ኤፌሶን 6፡1-3

1. አባቶችን በማክበር የሚገኝ የመጀመሪያው ሽልማት፡ መልካም እንዲሆንልህ

1. መልካም ሲሆንልህ፣ ስኬታማ ትሆናለህ።
2. መልካም ሲሆንልህ፣ ታሸንፋለህ።
3. መልካም ሲሆንልህ፣ ትለማለህ።
4. መልካም ሲሆንልህ፣ ታብባለህ።
5. መልካም ሲሆንልህ፣ ትበዛለህ።
6. መልካም ሲሆንልህ፣ ትታደሳለህ።
7. መልካም ሲሆንልህ፣ ትዘልቃለህ።
8. መልካም ሲሆንልህ፣ ትበለጽጋለህ።
9. መልካም ሲሆንልህ፣ ታድጋለህ።
10. መልካም ሲሆንልህ፣ ትጨምራለህ።
11. መልካም ሲሆንልህ፣ ታሸንፋለህ።

ሦስት መቶ ዘጠኝ ዘዴዎችን ያስተማረው አንድ በልዩ ሁኔታ የሚወደው ተማሪ ነበረው። ለምን እንደሆነ ባይታወቅም የመጨረሻውን ቁልፍ የማጥቂያ ዘዴ ፈጽሞ ሳያስተምረው አለፈ።

ወራት እንዳለፉ አለቃውንም እንኳ ሳይቀር ሁሉንም ማሸነፍ እንደሚችል በኩራት እስኪናገር ድረስ ተማሪው በካራቴ እጅግ በጣም ጥሩ ውጤት ማሳየት ጀመረ። በእርግጥ አለቃውን ለማሳፈር የማይፈልገው ለዕድሜው ካለው አክብሮትና ስለሰጠው ትምህርት ከሚሰማው ውለታ የተነሣ እንደሆነም ተናገረ።

በጊዜ ሂደት አለቃው ስለ ተማሪው ጉራ ሰምቶ ለዚህ ደቀመዝሙሩ አንድ ትምህርት ለማስተማር ወሰነ። ከተማሪው ጋር ግጥሚያ ለማድረግ ራሱን አቀረበ። ከዚያም አለቃውን ሊያሸንፍ የሚችል ብቸኛውን ወጣት ለማየት ሕዝብ ተሰበሰበ።

የጀምር ደወል ሲሰማ ደቀመዝሙሩ ወደ አለቃው ተንደርድሮ ሲሮጥ ያልተለመደ ሦስት መቶ አስረኛ የካራቴ ምት ተቀበለው። አለቅዬው የቀድሞ ተማሪውን ከራሱ በላይ አንሣና ከአድማጮች በሚስተጋባው ጩኸት መካከል በደረቱ ዘረረው።

በኋላም፣ እንዲህ ያለውን ጠንካራ ወጣት እንዴት ማሸነፍ እንደቻለ ሲጠየቅ፣ እንዲህ ላለ ቀን ሦስት መቶ አስረኛውን ብልሃት ለራሱ እንዳቆየ ተናገረ።

በእርግጥ በመጨረሻ መማር የሚችሉት ብዙ ነገር መቅረቱን ተገንዝበው እስከሚደነቁ ድረስ መማር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟጠው እንደተማሩ የሚያስቡ ብዙ ልጆችና ደቀመዝሙሮች አሉ።



## ምዕራፍ 10

# አባቶችን በማክበር የሚገኙ ሦስት ሽልማቶች

ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፣ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።

ኤፌሶን 6፡1-3

1. አባቶችን በማክበር የሚገኝ የመጀመሪያው ሽልማት፡ መልካም እንዲሆንልህ

1. መልካም ሲሆንልህ፣ ስኬታማ ትሆናለህ።
2. መልካም ሲሆንልህ፣ ታሸንፋለህ።
3. መልካም ሲሆንልህ፣ ትለማለህ።
4. መልካም ሲሆንልህ፣ ታብባለህ።
5. መልካም ሲሆንልህ፣ ትበዛለህ።
6. መልካም ሲሆንልህ፣ ትታደሳለህ።
7. መልካም ሲሆንልህ፣ ትዘልቃለህ።
8. መልካም ሲሆንልህ፣ ትበለጽጋለህ።
9. መልካም ሲሆንልህ፣ ታድጋለህ።
10. መልካም ሲሆንልህ፣ ትጨምራለህ።
11. መልካም ሲሆንልህ፣ ታሸንፋለህ።

12. መልካም ሲሆንልህ፣ ትቀድማለህ።

13. መልካም ሲሆንልህ፣ የበለጠ ታደርጋለህ።

14. መልካም ሲሆንልህ፣ ፍሬ ታፈራለህ።

15. መልካም ሲሆንልህ፣ ትሰፋለህ።

16.

መልካም ሲሆንልህ ከከፍተኛ በረከቶች ሁሉ የላቀውን አገኘህ ማለት ነው። ማን ነው መልካም እንዲሆንለት የማይወድ? ይሁንና፣ ለአባትህ የማትታዘዝ ከሆንህ ፈጽሞ መልካም አይሆንልህም!

ለልጆች የሚሆን ከሁሉም የላቀው በረከት ተደብቆ የተቀመጠውለአባቶቻቸው ባላቸው ታዛዥነት ውስጥ ነው። ብዙ ልጆች ባሉባቸው ሰፊ ቤተሰቦች የታዘብሁት አንድ ነገር አለ።

ለወላጆቻቸው ታዛዥ የሆኑ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች፣ ከዓመፀኞቹ፣ ከግለኞቹና ከተቃዋሚዎቹ ይለያሉ። ይህ ራስህ መድረስ የምትችለው እውነት ነው።

አንዲት መጋቢ ይህን ክስተት እንዴት እንደደረሰችበት ነገረችኝ። ከአባቷ ልጆች አንዳንዶቹ እንዴት የአባታቸውን ምክር ያለማቋረጥ እንደተቃወሙም ገለጸችልኝ። ከዚያም፣"ታዲያ ዛሬ ነገር ለእነርሱ ቀላል አልሆላቸውም" በማለት ተመሰጠች። "ጋብቻ ቀላል አልሆነላቸውም። በገንዘብ ረገድም በጣም ይቸገራሉ።"

በመቀጠልም፣ "በታዘዝነውና ባመፁት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አያለሁ" አጫወተችኝ።





## ልዩነቱ ግልጽ ነው

ሌላኛው መጋቢ ደግሞ፣ "እኔ ወንድሞችና እኅቶች ያሉበት ትልቅ ቤተሰብ አለኝ፤ በመካከላችን ያለው ልዩነት ግልጽ ነው" በማለት ነገረኝ።

አባት እንዴት ከሴት ልጆቹ በአንዲቱ ክብካቤ ይደረግለት እንደነበርም ገለጸልኝ።

እንዲህም አለኝ፣ "ይህች እኅቴ ሁልጊዜ አባቴን ትንከባከብ ነበር። እርሱ የሚፈልገውን ሁሉ ታደርግ ነበርና እርሱም በእርሷ ደስ ይለው ነበር።"

*"በእርግጥ"፣ አለና ቀጠለ፣ "አባቴ የሞተው በእርሷ እጅ ነው። እርሱ በሚሞትበት ጊዜ ታገለግለው ነበር። በሞቱ ሰዓት እናቴ እንኳ አልነበረችም፣ እርሷ ግን እዚያው ነበረች።"*

ዛሬ ሕይወቷ ከአንዳንድ ወንድሞቿና እኅቶቿ የተለየ ነው። ሌሎች ወንድሞቹንና እኅቶቹን ስለመታው የካንሰርና የድህነት አሰቃቂ ሁኔታ ማብራራት ጀመረ። እየተመሰጠ፣ "በእርግጥ ወላጆቻቸውን በሚወዱና በሚያከብሩ ልጆችና እነዚህን በማያደርጉ ልጆች መካከል ልዩነት ይታያል።"

አንድ ቀን አንድ አባት ከሁለት ወንድ ልጆቹ ጋር ገበያ ሄደ። በገበያው አዳራሽ እየተዘዋወሩ ልብሶችን በሚገዙበት ወቅት፣ አባት ለልጆቹ፣ "ይህን ሱሪ ግዙ፣ ይስማማችኋል፣ ቆንጆ ነው" አለ። ነገር ግን አባት በሰጠው አስተያየት ላይ ልጆች ምላሽ የሰጡት በተለያየ መንገድ ነበር።

አንደኛው ሁልጊዜም የተለየ አስተያየት የነበረው ነው። አባቱ የወደደውን እርሱ አይወድም። እንዲያውም የሆኑ ነገሮችን ባለማግኙ የሚያጉረመርምና የሚበሳጭ ነበር።

ይሁንና፣ የሌላኛው ልጅ ምላሽ በጣም የተለየ ነበር። እንዲህ ይል ነበር፣ "አንተ የምትመርጥልኝ ሁሉ ጥሩ ነው። አንተ ለእኔ

*የምትወደውን እኔም ለራሴ እውደዋለሁ። አንተ ለእኔ የምትፈልገውን እኔም ለራሴ እፈልገዋለሁ።"*

አየህ እነዚህ ሁለት አመለካከቶች ያድጉና የተለየ ውጤት ያስከትላሉ። መልካም ሲሆንልህ ከሁሉም የላቀ በረከት ባለቤት ትሆናለህ። አባቶቻቸውን የሚያምኑና የሚታዘዙ ሴት ልጆች መልካም ይሆንላቸዋል! አባቶቻቸውን የሚታዘዙ ወንዶች ልጆች መልካም ይሆንላቸዋል። ይህ መርህ ለሁሉም ዓይነት አባቶች፣ የሥጋ ይሁኑ የመንፈስ ተግባራዊነት አለው።

አባት ለልጁ የሚፈልገውን የምትፈልግ ልጅ ሁን። አባት ለልጁ የሚወደውን የምትወድ ልጅ ሁን። ክርስትና በዚህ መሠረት ላይ የተገነባ ነው፡ ፈቃድህን ለአባትህ ፈቃድ ማስገዛት ላይ። ከራስህ ፈቃድ ይልቅ፣ *የአባትን ፈቃድ በመቀበል* መርህ ላይ።

የራስህን ፈቃድ አድራጊ አትሁን። ለአባትህ ፈቃድ ተገዛ። "አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" ማለት ቀላልና አስተማማኝ ነው። ኢየሱስን እንከተል፤ እርሱ ለእኛ ከሁሉም የላቀ ምሳሌ ነው።

## 2. አባቶችን በማክበር የሚገኝ ሁለተኛ ሽልማት።

1. አባትህን ስታከብር ሕይወትህን የሚያሳጥሩ በሽታዎችን ታሸንፋለህ።
2. አባትህን ስታከብር ብዙ ቀውሶችን ታልፋለህ።
3. አባትህን ስታከብር አደጋም እያለ ትዘልቃለህ።
4. አባትህን ስታከብር ብዙ ችግሮችን ትቋቋማለህ።
5. አባትህን ስታከብር ብዙ ዘመን ትኖራለህ።
6. አባትህን ስታከብር ሰዎች ሞትህን ሲተነብዩ በሕይወት ትኖራለህ።
7. አባትህን ስታከብር ታሪክን ለመዘከር ትበቃለህ።
8. አባትህን ስታከብር በአገልግሎት ትለማለህ።





9. አባትህን ስታከብር ዕድሜህን ታስረዝማለህ።
10. አባትህን ስታከብር ሳትስምጥ ተንሳፈህ ትኖራለህ።
11. አባትህን ስታከብር ትመለሳለህ።
12. አባትህን ስታከብር ከሌሎች ሁሉ የበለጠ ትቆያለህ።
13. አባትህን ስታከብር ከሌሎች ሁሉ የበለጠ ትኖራለህ።
14. አባትህን ስታከብር ከሌሎች የበለጠ ዕድሜ ትኖራለህ።
15. አባትህን ስታከብር በችግር ትጸናለህ።
16. አባትህን ስታከብር ትጠነክራለህ።
17. አባትህን ስታከብር ትዘልቃለህ።
18. አባትህን ስታከብር እስከ መጨረሻ ትጓዛለህ።
19. አባትህን ስታከብር ፈጽሞ 'ተስፋ አትቁርጥም'።
20. አባትህን ስታከብር በጊዜ ያልተገደበህ ትሆናለህ።

ሕይወትህን ከምታሳጥርባቸው መንገዶች አንዱ አባትህንና እናትህን አለማክበር ነው። ዙሪያ ገባህን እይና ይህ በተግባር እውነት እንደሆነ ትረዳለህ።

*በአገልግሎትም ቢሆን ዘለቄታህ ከአባቶችህ ጋር ባለህ ግንኙነቶች ላይ የሚመሠረት ነው።* ዘለቄታ ሲባል በአገልግሎት ውስጥ ምን ያህል እንደምትቆይ ማለት ነው። ሁልጊዜም ቢሆን ከአንተ የሚቀድሙ ሰዎችን ታገኛለህ። እነዚህን ሰዎች እንደ አባት ማክበር አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳ የተለየ አገልግሎት ቢኖርህም አባቶችን ስለ ማንነታቸው ማክበር ይገባሃል።

ዘለቄታ ያላቸው አገልግሎቶች ምሳሌዎች፣ ሁለቱ የኢየሱስና የዳዊት አገልግሎቶች ናቸው። የኢየሱስ አገልግሎት በሺዎች የሚቆጠሩ ዘመናትን ያካለለ ሲሆን አሁንም ቢሆን እየተጠናከረ ያለ ነው። የንጉሥ ዳዊት አገልገሎት አሁንም ቢሆን በጻፋቸው መዝሙሮቹና በመራው ሕይወቱ በኩል ለሰዎች የሚሰማ ነው።

ለመቀጠልና በዓመታት ሁሉ ለመዝለቅ ከፈለግህ ይህን መርህ አሁን ተማር!

3. አባቶችን ስለ ማክበር ሦስተኛው ሽልማት፡ ርስት ማግኘት ነው።

ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን፣ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን . . . ታውቁ ዘንድ ነው፤

ኤፌሶን 1፡18

መንፈሳዊ ርስት በመባል የሚታወቅ ነገር አለ። "መንፈሳዊ ርስት" ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፍ ነገር ነው።

የእግዚአብሔርን ሰው እንደ *አባት* ስትቀበል ብቻ የርስትን ጥቅም ትቀበላለህ። ርስት የሚተላለፈው *ከአባቶች ወደ ወንድና ሴት ልጆች* ብቻ ነው።

ኤልሳዕ ሳፋጥ የሚባል ምድራዊ አባት እንደነበረው ታስታውሳለህ።

. . . የሳፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ . . .

2 ነገሥት 3፡11

ኤልሳዕም አይቶ፣ አባቴ አባቴ ሆይ፣ . . . ብሎ ጮኸ።

2 ነገሥት 2፡12

*የአንተ የሆነውን የእግዚአብሔር ሰው እንደ አባት መቀበል ያለብህ ለምንድን ነው? ምክንያቱ አባቶች ለልጆች ርስትን ስለሚያስቀሩ ነው።* ሰዎች ብዙ ጊዜ ርስትን ለአሽከሮች፣ ለሠራተኞች፣ ለጓደኞችና ለባልደረቦች አያስቀሩም። ርስት ለልጆች ነው!

ርስት ያለው ሰው ርስት ከሌለው ሰው በጣም ይለያል። አባት ያለው ሰው ለሕይወቱ አቅጣጫንና ምሪትን ያገኛል። አባት የሌለው ሰው ሕይወቱ በትግሎች የተሞላ ነው።

ዩኒቨርስቲ ውስጥ እያለሁ ምንም *ሥራ* አልሠራም ነበር። የሕክምና *ዶክተር* እስከምሆን ድረስ አባቴ ሁሉን ነገር ያቀርብልኝ ነበር።





በየወሩ የሚሰጠኝ ገንዘብ ዶክተር ከሆንሁ በኋላ ከማገኘው ደመወዝ የበለጠ ነበር። በአምስተኛ ዓመት የሕክምና ትምህርት ላይ እያለሁ አባቴ አዲስ መኪና ገዛልኝ። እኔ በእርግጥ የሚንከባከበኝ አባት ስለነበረኝ በጣም የተባረክሁ ነበርሁ። *የተማሪነት ሕይወቴ "ከትግል ነፃ" ነበር፣ ምክንያቱም አባት ስለነበረኝ!* ይሁንና ይህ የብዙ ሰዎች ታሪክ አይደለም።

ለሕይወታቸው ምሪትን ያልተቀበሉ ቁጥራቸው ብዙ የሆነ ሰዎችን አግኝቼ አውቃለሁ። የሚመራቸው አባት ስላልነበራቸው ችሎታቸውን የትም ጥለው አልባሌ ሰዎች ሆነው ቀርተዋል። አባታቸውን እንኳ የማያውቁ ሰዎችን አውቃለሁ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆች እጅግ የባሰ ነው! ወላጅ አልባ ልጆች በትግሎች የተጨናነቁ ናቸው። የወላጅ አልባ ልጅ የወደፊት ሕይወት እርግጠኝነት ይጎድለዋል። በአገልግሎትም ቢሆን እንዲሁ ነው። በትክክለኛው መንገድ የሚመራህ ሰው ከሌለህ፣ አገልግሎትህ በትግሎች የተሞላ ይሆናል። እኔ በአገልግሎት የተለያዩ አባቶች የነበሩኝ ቢሆንም፣ ወደ መጋቢነት የማደርገውን እድገት በተመለከተ አባት አልባ የነበርሁባቸው ጊዜያት ነበሩ።

በርቀት የሚገኙ የአገልግሎት አባቶች ነበሩኝ። በቅርብ የሚገኙ አባቶች ስላልነበሩኝ በተለያዩ ትግሎች ውስጥ ማለፍ ግድ ሆኖብኛል። በአገልግሎት የገጠሙኝ ብዙዎቹ ትግሎችና ጭንቀቶች ምክንያታቸው የሚረዳኝ አንድም ሰው አለመኖሩ ነበር።

በእርግጥ ቤተክርስቲያኔን በምጀምርበት ወቅት ለእኔ አባት መሆን የሚገባቸው ሰዎች ይብስ የወጣላቸው ጠላቶች ሆኑ። ዓለማዬን ተቃወሙና በእኔ ላይ ተነሡብኝ።

*ርስት በተፈጥሮ ከአባቶች ወደ ልጆች የሚተላለፍ ነው።* በአገልግሎትም *መንፈሳዊ* ርስት *በቀጥታ* ከአባቶች ወደ ልጆች ይተላለፋል። አባቴ በሞተ ጊዜ የእርሱ ኑዛዜ በፍርድ ቤት ተነበበ።

ንብረቱን ለልጆቹ ትቶ ሞተ። ብዙ ሠራተኞችና ጓደኞች የነበሩት ቢሆንም እንኳ ለአንዳቸውም አልተናዘዘም-ሁሉም ነገር ለልጆች ነበር። ውድ ወዳጄ፣ ይህ የሕይወት እውነታ ነው። ርስት ሁልጊዜም ቢሆን የሚሰጠው ለልጆች እንጂ ለባልደረቦች ወይም ለጓደኞች አይደለም።

መንፈሳዊ ርስት በመባል የሚታወቅ ነገርም አለ። ይህ የቅባትና የስጦታዎች መንፈሳዊ ርስት በቀጥታ ከአባቶች ወደ ልጆች ይተላለፋል። ከአባት ወደ አቻዎች፣ ወደ ባልደረቦችና ወደ ጓደኞች አይተላለፍም። እንዲያውም ከአባት ወደ አገልጋዮቹ እንኳ አይተላለፍም። የሚተላለፈው *ከአባቶች ወደ ልጆች ነው።*

## እንደምን ነህ "አለቃ"

"አለቃ" እያለ መጥራት የሚወድ አንድ ረዳት መጋቢ ነበረኝ። ለምን እንደሆነ አላውቅም፣"አለቃ"እያለ ሲጠራኝ ሁልጊዜ አይመቸኝም። አየህ አንድ ሰው "አለቃ"ብሎ ሲጠራህ ራሱን እንደተቀጠረ ሰው አድርጎ የሚያይ ይመስላል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይህ መጋቢ በማያስደስት ሁኔታ ከእኛ ተለየ። ለምን ደስ አይለኝ እንደነበር የተረዳሁት ከዚያ በኋላ ነበር። አሽከር ወይም ሠራተኛ ሁልጊዜ አብሮ አይቆይም። የሚቆየው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሲሆን ሲመቸው ይለቃል።

> ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል።
>
> የሐንስ 8:35

የአባትና ልጅ ግንኙነት የሚሆንልህ ከእግዚአብሔር ሰው ጋር ግንኙነት ካለህ፣ ከእርሱ ዘንድ መንፈሳዊ ቅብዓት ያለብዙ ድካም እንዲፈስልህ ልትጠብቅ ትችላለህ።



*ምዕራፍ 11*

# ሰባት የአባት ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሎች

## 1. የአባት መረማመጃ ድንጋይ የመሆን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

> ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምን አነሆ፣ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፤
>
> ሉቃስ 2:34

አባት በመኖሩ ብቻ ልጆቹ ወደ ከፍታ እንዲደርሱ ያደርጋል። ከላይ የተሰጠው ክፍል የክርስቶስ መገኘት እንዴት መነሣትንና መውደቅንም ለብዙ የተለያዩ ሰዎች እንደፈጠረ ይናገራል። አባት የልጆቹን መነሣትና ማደግ ለማምጣት በልዕለ-ተፈጥሮአዊ መንገድ የተቀመጠ ነው።

አባቶች ለልጆቻቸው በረከት ለመሆን የግድ በረከትን መናገር የለባቸውም። ማድረግ ያለባቸው ነገር ቢኖር መኖር ብቻ ነው፣ በዚህም ልጆቻቸው ይባረካሉ። አብዛኞቹ አባቶች ለልጆቻቸው ምንም የተለየ ነገር አይናገሩም። የአባት መኖር ብቻ በራሱ ልጁ እንዲባረክ ያደርጋል።

ሰዎች አባታቸው ለሞቱባቸው ልጆች የሚያዝኑት ለዚህ ነው። ችግራቸው የተነገሩ በረከቶች ወይም እርግማኖች መኖራቸው አይደለም። የአባት መገኘት መቋረጡ ችግር ነው። የእርሱ መገኘት በልጆቹ ላይ ሊገለጽ የማይችል መጠን ያለው ውጤት ያስከትላል።

## 2. የእንቅፋት ድንጋይ ለመሆን አባት ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

አባት በልጆቹ ላይ ችግሮች እንዲፈጠሩ እርግማን መናገር አያስፈልገውም። የአባት መኖር የልጁን ውድቀት ሊያስከትል ይችላል። አባቶች ፍጹም ስላይደሉ እነርሱን መቃወምና ክብርን መንፈግ ቀላል ነው። አባቶች ለልጆቻቸው ብዙ የተለዩና ጊዜ ያለፈባቸው መስለው ሊታዩ ይችላሉ።

> ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና፣
>
> የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ አለው።
>
> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ሄዳችሁ ያያችሁትን፣ የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤
>
> ዕውሮች ያያሉ፣ አንካሶችም ይሄዳሉ፣ ለምጻሞችም ይነጻሉ፣ ደንቆሮችም ይሰማሉ፣ ሙታንም ይነሣሉ፣ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው።
>
> ማቴዎስ 11:2-6

ኢየሱስ በእርሱ የማይሰናከሉ ሰዎች የተባረኩ እንደነበሩ ተናገረ። ምንም እንኳ መልካም ነገር እያደረገ ቢሆንም በእርሱ የሚሰናከሉ ሰዎች እንደሚኖሩ ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ሰዎችን ለማሰናከል ብዙ ድካም አይጠይቅም! ሰዎች በሁሉም ነገር ማለት እስከሚያስደፍር ድረስ ይሰናከላሉ! ቁጡ ልጆች በቀላሉ በተሳሳተ አቅጣጫ በመሆን በአባቶቻቸው ላይ በመራርነት ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። አባቶችን በማዋረድ ወጥመድ ውስጥ የሚገቡ ልጆች ጽኑ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እርግማን ያገኛቸዋል!

ነገር ግን ይህ እንዴት ይሆናል? ይህስ እርግማን የሚተላለፈው መቼ ነው? አንድ ማወቅ የሚገባህ ነገር ቢኖር አባቶች እርግማንን ራሳቸው መናገር እንደማያስፈልጋቸው ነው። አባት እርግማን አስተላልፎ ይሁን አይሁን አትጨነቅ። የእግዚአብሔር ቃል አባታቸውን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለሚያዋርዱ ወንዶች





ልጆች ብዙ የተጻፉ እርግማኖች አሉት። በዚህ ዓይነት መንገድ፣ ምንም ዓይነት እርግማን በተግባር በልጆቻቸው ላይ ያልተናገሩ አባቶች እርግማን እንዲመጣ ሊያደርጉ ይችላሉ።

## 3. አባት እርግማንን ለማስተላለፍ ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

አባቶች ለመባረክም ሆነ ለመርገም ኃይል አላቸው። በጌታ የተሰጠ የሥልጣን መንበር አላቸው። አባት በልጅ ላይ በረከትን ሲናገር ከፍተኛ የሆነ ኃይል ይለቀቃል።

በምድር ላይ መለኮታዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ሦስት አይነት የሰዎች ቡድኖች አሉ። በቤተሰብ አካባቢ፣ አባት ይህ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በአገር ደረጃ፣ መንግሥት ይህ ሥልጣን ተሰጥቶታል፣ በቤተክርስቲያን ደግሞ መጋቢው ይህ ሥልጣን አለው።

> ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።
>
> ሮሜ 13:1-2

ከእነዚህ ሥልጣናት ከማናቸውም ጋር ያለህ ግንኙነት በምድር ላይ ለመኖርህ ቁልፍ አስተዋጽኦ አለው። በእግዚአብሔር ለአንተ የተመደበ ማናቸውም ዓይነት አባት በሕይወትህ ላይ ሥልጣን አለው።

> ትዕግሥት ታላቁን ኃጢአት ጸጥ ያደርጋልና የገዢ ቁጣ የተነሣብህ እንደሆነ ስፍራህን አትልቀቅ።
>
> መክብብ 10:4

አንድ ቀን፣ ከጥቂት መጋቢዎች ጋር በአንድ አዳራሽ ውስጥ ሆኜ እጫወት ነበር። አንደኛው መጋቢ እሮሮውን ሲያሰማ ሰማሁት። የልጁን ሕይወት ለማትረፍ ያለውን ገንዘብ ሁሉ ቢያጠፋም አሁን

ልጁ በጣዕር ላይ መሆኑን ተናገረ። በጊዜው ይህ ሰው ተስፋ የቆረጠና የተጨነቀ ነበር። በገዛ አንደበቱ፣ ልጁን ለዚህ ችግር የዳረገው ምን እንደሆነ ሲናገር ሰማሁት።

ልጁ በእርሱ ሕይወት ላይ አባቱ ከነበረው ሥልጣን ጋር አለመስማማት ነበረበት።በዚህ ጊዜ አባትየው ከዚህ ሥልጣኑ ልጁ ርቆ በመሄዱ፣"የእኔ ከለላ ከአንተ ተወግዷል" ብሎ አወጀበት።

"የእኔ ችግር መነሻው ሁሉ ይህ ነው" በማለት ተናገረ።

አየህ መንፈሳዊ ሰዎች መንፈሳዊ መርሆችን ይረዳሉ። ከሥልጣናዊ አካል ከእርግማን ይልቅ በረከቶችን ለመቀበል ተጣጣር።

## ቀሳፊ እርግማኖች

የአባት እርግማን ቀሳፊ ነው! አባት ሥልጣናዊ አካል ስለሆነ ቃሎቹ ሰማያዊ ድጋፍ አላቸው።

በእርግጥ አባትነት መንፈሳዊ ይዞታ ነው። ከዚህ ይዞታ የሚወጡ ቃሎች ኃይል ስላላቸው ቀላል ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ በእርግማኖችና በበረከቶች ምሳሌዎች የተሞላ ነው።

## የካም እርግማን

ኖኅ እንደ አዳም ዓይነት ሰው ነበር። ይህም ማለት በምድር ላይ ብቻውን የቀረ ሰው ሲሆን በልጆቹ አማካኝነት ምድርን እንደገና በሰው መሙላት ነበረበት። ኖኅ መርከብ ሠርቶ የጥፋቱን ውኃ አምልጧል። ከጥፋት ውኃ በኂላ በምድር ላይ በሕይወት የቀሩት እርሱና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ።

ይሁንና፣ አንድ ቀን ከጥፋት ውኃ በላይ የታሪክን አቅጣጫ ያስቀየረ አንድ ነገር ተከሰተ። ይህ ቀን ኖኅ ከልክ በላይ ጠጥቶ በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን የሆነበት ቀን ነበር። ከልጆቹ አንዱ፣ ጥቁር መልክ የነበረው ካም፣ የአባቱን ራቁትነት በማጋለጥ ስለ ሁኔታው ለሌሎች





ተናገረ። ይሁን እንጂ፣ ሌሎቹ ሁለቱ ልጆቹ የአባታቸውን ራቁትነት ሸፈኑ።

ኖኅ በነቃ ጊዜ፣ ለዘላለም እጅግ ከጸኑ ተግሣጾች አንዱ የሆነውን አስተላለፈ። በልጁ ላይ "የባርያዎች ባርያነትን" እርግማን አስተላለፈ። ጥቁር መልክ ባለው ልጁ ላይ የተላለፈው ይህ ተግሣጽ፣ እስከ ዛሬ ድረስ የሚታይ ውጤትን አስከተለ።

በመላው ዓለም ላይ፣ ጥቁር ሕዝቦች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ሰዎች ይቆጠራሉ። በኢራቅ አገር የተጨቆኑ ሰዎችን ነፃ ለማውጣት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች ፈስሰዋል። ነገር ግን የታረዱ የላይቤሪያና የሴራሊዮን ወንድና ሴት ልጆችን ለመርዳት ምንም ተነሣሽነት አልታየም።

ሳዳም ሁሴንን ወይም ሁለቱን ልጆቹን ለማስያዝ የሚያበቃ መረጃ ለሰጠ ሰው *የሃያ ሚሊዮን ዶላር* ሽልማት ቀርቦ ነበር።

ነገር ግን በአፍሪካ፣ አፍሪካዊውን አሸባሪ ሞሐመድ ፋራ አይዲድን ለመያዝ ለሚችል የቀረበው ገንዘብ *ሃያ ሺህ ዶላር* ብቻ ነበር።

ጥቁር ሕዝቦች በሁሉም ዓለም በአስፈሪው የኖኅ ተግሣጽና እርግማን ምንክንያት እየተሠቃዩ ናቸው።

በጥቁር ሕዝቦች የተያዘው ክፍለ-አህጉር በአጠቃላይ በአልባሌ ሕዝቦች የተያዘ ዝቅተኛ ቦታ ተደርጎ ይቆጠራል። እንዲህም ሆኖ ግን ከፍተኛ የማዕድናት ሀብትን ያመቀ ክፍለ-አህጉር ነው። ከከፍተኞች የወርቅ ሀብቶች አንዳንዶቹ እንደ ታንዛኒያ፣ ጋናና ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገሮች ይገኛሉ።

በእያንዳንዱ ክፍለ-አህጉር እንኳ፣ በጥቁር ሕዝቦች የተያዙ ክፍሎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ አካባቢዎች ይታያሉ። በሰሜን ወይም በደቡብ አሜሪካ፣ በአውስትራሊያ ወይም በአውሮፓ የጥቁር ሕዝቦች ገጽታ አንድ ነው። ይኸውም፣የባሪያ ወይም የባሪያ ባሪያ ገጽታ ነው።

እንዲህ ያለ ሁኔታ በመላው ዓለም እንዴት ሊከሰት ቻለ? ጥቁር ሕዝቦች እንደ ነጭ ሕዝቦች እኩል የአእምሮ ችሎታ እንዳላቸው ተረጋግጧል። የተበላሸችው የአሜሪካ የጠፈር መንኮራኩር በውስጧ ጥቁር የጠፈር ሊቅ እንደነበረባት ታውቋል። ጥቁር ሕዝቦች እንደ ነጮቹ በትምህርት እኩል ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕሬዝደንት፣ ታዋቂው የጎልፍ ተጫዋች፣ ከፍተኛዋ ሀብታም ሴት፣ ቁንጮ የቅርጫት ኳስ ተጫዋች፣ እጅግ ፈጣን ወንድና ሴት ሯጮች፣ በዓለም እጅግ ታዋቂ ቦክሰኞች ጥቁር ሰዎች ናቸው። የፖፕ ሙዚቃ ንጉሥና ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ የክርስቲያናዊ ሙዚቃ ድምፃዊ ጥቁሮች ናቸው።

እንዲህም ሆኖ እርግማኑና ተግሣጹ ጥቁር ሕዝቦች ላይ ጥቁር ደመናን እንዳጠላ ነው። በልጁ ላይ የተነገሩ የአባት ቃሎች፣ የማያወላዳ የባርነት ኡደትን በመላው ምእተ ዓመታት መካከል እያስተጋቡ ናቸው።

## ከአባቶች ጋር ያለህን ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ያዝ

ከአባቶች ጋር ያሉህን ግንኙነቶች በአግባብና በጥንቃቄ መያዝ በዓለም እጅግ ብልህነት ከሚሰኙ ነገሮች አንዱ ነው።

ወጣቶች ፍቅር ሲይዛቸው፣ ብዙ ጊዜ ወላጆቻቸውን ማክበርንና መታዘዝን ይዘነጋሉ።

ከጥቂት ጊዜያት በፊት፣ ይህን መርህ ሙሉ በሙሉ አልተረዳሁም ነበር። ነገር ግን ሁለት ወጣት ሴቶች ከወላጆቻቸው ፍላጎት ውጭ ካገቡ በኋላ ገና በአፍላ ዕድሜያቸው ሲቀጩ አይቼ ነገሩን አጤንሁት።

አንድ ባል የሚስቱ ቤተሰብ እርሱን ማግባቷን እንዴት አምርሮ እንደተቃወመ ነገረኝ። ነገር ግን እርሱ ከወላጆቹ ፍላጎት ውጭ ጥሶ ሄዶ አገባት። በኋላም ይህች ወጣት ሴት የተለየ ዓይነት ሽባነት





መጣባት። በመጨረሻም በምትሞትበት ጊዜ ትንንሽ ልጆችን በባለቤቷ እጅ አስታቅፋ ሞተች።

## ከአባት ፍላጎት ውጭ ማግባት

በተኛችበት የሆስፒታል አልጋ በሞት ጣዕር ውስጥ ከነበረች አንድ የሃያ አምስት ወጣት ሴት አጠገብ ቁጭ ብዬ የነበርሁበት ጊዜ ትዝ ይለኛል። ይህች ልጅ አባቷ ማግባቷን ይቃወም ነበር፣ እርሷ ግን በጉዳዩ ቀጥላበት ያለ አባቷ እውቅና አገባች።

ከሕክምና ተሞክሮዬ የተነሣ፣ አንድ ሰው የሚሞትበትን ጊዜ አውቃለሁ። ፊታቸውን በማየት ብቻ መናገር እችላለሁ። በአልጋዋ ላይ ተቀምጬ እያለሁ በጣም ደነገጥሁ። እጇን በጉልበቴ ላይ አስቀምጣ "ቢሾፕ፣ ፈራህ?" አለችኝ፤ ያሳዝናል እኔ ግን ዋሸሁ። ለካስ ሳላውቀው ፈርቼ ነበር። ነገር ግን አልፈራሁም ብዬ ተናገርሁ፡
፡

ከዚያም፣ "አትፍራ፣ እኔ አልሞትም" አለችኝ። ነገር ግን እየሞተች እንደሆነ እኔ አውቅ ነበር። እጄን በራሷ ላይ አስቀምጬ ስዳስስ፣ የተሰራጨ ካንሰር የሚያመለክቱ በጭንቅላቷ ውስጥ በርከት ያሉ እብጠቶችን አገኘሁ። በጣም ከባድና በውል የማይታወቅ በሁሉም ስፍራ የተሰራጨ ካንሰር ነበረባት። ይህ በሽታ በጣም የተለየ ከመሆኑ የተነሣ የታወቀው ከሞተች በኋላ በአካሏ ላይ በተደረገ ምርመራ ነበር።

የሞተችው ፈጽሞ በማልረሳው፣በሚያስፈራና በሚዘገንን ሁኔታ ነበር። በዚሁ ሁሉ ረጅም ሥቃይዋ በአእምሮዬ ውስጥ የሚመላለሰው እንዴት ከአባቷ ፈቃድ ውጭ እንደሄደች ነበር። እውነቱን እንናገርና የአባት እርግማን በማናቸውም መንገድ ሊወገድ ይገባዋል። እግዚአብሔር የሰጣችሁን አባቶች ታዘዙ፣ በሰላምም አብራችሁ ተጓዙ። እነርሱ የተሰጧችሁ መልካም እንዲሆንላችሁ ነው።

ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤

ሮሜ 13፡1-3

በአባትዋ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል።

ምሳሌ 30፡17

## 4. አባት በረከትን ለማወጅ የተሰጠው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

ይስሐቅ ሸምግሎ ዓይኖቹ ከማየት በፈዘዙ ጊዜ . . . አባቱ ይስሐቅም፡- ልጄ ሆይ (ያዕቆብ) . . . እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል ከምድርም ስብ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ። አሕዛብ ይገዙልህ፣ ሕዝብም ይስገዱልህ፣ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፣ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን የሚባርክህም ብሩክ ይሁን።

ዘፍጥረት 27፡1፣ 26፣ 28፣ 29

ከዚህም ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ፣ እነሆ አባትህ ታምሞአል ብለው ለዮሴፍ ነገሩት . . . በዚያም ቀን እንዲህ ብሎ ባረካቸው።

ዘፍጥረት 48፡1፣20

ተፈጥሮአዊ ሰዎች አካላዊ ድካምን እንደ መንፈሳዊ ድካም አድርገው መውሰዳቸው የሚያሳዝን ነው። እርጅና፣ በሽታና ችግሮች የአንድን ሰው መንፈሳዊ ሥልጣን የሚቀንሱ ይመስላቸዋል። ይህ ከፍተኛ ከሚባሉ ስሕተቶች አንዱ ነው።

ይስሐቅ *ሽማግሌ ሰው ነበር*። በሁለት ልጆቹ በያዕቆብና በዔሳው መካከል የነበረውን ልዩነት ማየት የሚችል አልነበረም። ይስሐቅ በያዕቆብ ተታሏል፣ በመታለሉም በያዕቆብ ላይ የተናገረው በረከት ተግባራዊ ሊሆን ችሏል።





አለውም፡- አንተ ልጄ ዔሳው ነህን? እርሱም (ያዕቆብ)፡- እኔ ነኝ አለ። ወደ እርሱም ቀረበ፣ ሳመውም . . . ባረከውም፣ እንዲህም አለ፡- . . . እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል፣ ከምድርም ስብ፣ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ፡ አሕዛብ ይገዙልህ፣ ሕዝብም ይስገዱልህ፡ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፣ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፡ የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን፣ የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን።

ዘፍጥረት 27፡24፣ 27-29

በአባትህ ዓይኖች መፍዘዝና በአካሉ ድካም አትታለል። እርሱ አሁንም ቢሆን አባት ነው፣ የዚህ ምዕራፍ ዋነኛ ትምህርትም ይህ ነው። ዓይነ ስውር አባት ተግባራዊ የሚሆን በረከትን መናገር ከቻለ፣ የአባቶችን ቃሎች መፍራት ይገባናል።

ሰዎች ብዙ ጊዜ አባቶችን በመቃወም ሲናገሩ እንሰማለን። አባቶቻቸውን ለእነርሱ ክብካቤ ያላደረጉ ኃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች አድርገው ይወቅሷቸዋል። ከአባቶቻቸው ጋር ምንም ነገር እንዲኖራቸውም አይፈልጉም። አንዳንድ ጊዜ በወጣትነት ጤናማ አቋማችን፣ አባቶችን አስተዋጽኦቸው እዚህ ግባ የማይባል፣ አርቀው የማያዩ፣ መስመር-ለቀቅ ሰዎች አድርገን እናስብ ይሆናል።

አንዳንድ ወጣቶች የእናቶቻቸውን መበደል ምክንያት አድርገው በአባቶቻቸው ላይ ተቃውሞአቸውን ሲያፋፍሙ ያሳዝናል። ይህ ትልቅ ዋጋ የሚያስከፍላቸው ጠንቀኛ ስሕተት ነው። አንዳንዶች የመካንነትን ዋጋ ይከፍላሉ። አንዳንዶች ደግሞ የሞትን ዋጋ ይከፍላሉ። አዎን፣ አባት የታወረ፣ ኃላፊነት የማይሰማውና የሳተ ሊሆን ቢችልም እንኳ እንዲህም ሆኖ ግን አባት ነው።

ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች በኋለኛው ዕድሜያቸው በውጊያ የዛሉና ኃይላቸው የተሟጠጠ ይመስላሉ። ብዙ ጊዜ የተጣሉ ጀግኖች፣ ጥንታዊ ሰዎችና የተረሱ መንፈሳዊያን ተደርገው ይታሰባሉ! ማንም ሰው ከእነርሱ ጋር ምንም ነገር እንዲኖረው አይፈልግም። ነገር ግን የወለዱህና ዛሬ ያለህን ውርስ-ቅርስ ሁሉ ያጎናጸፉህ እነዚህ “የታወሩና የተታለሉ” ሰዎች ናቸው።

ካም የሰከረውን የአባቱን ራቁትነት ባጋለጠ ጊዜ፣ የረሳው አንድ ነገር ነበር። አባቱ መርከብ ባይሠራ ኖሮ፣ በውኃ ይበላ ነበር። ከተቀረው ዓለም ጋር በሰመጠ ነበር። አካሉ በተለያዩ የባሕር ዓሦች በተበላ ነበር!

ያልተረዳው ነገር ቢኖር በአባቱ ብቸኛ የእምነት ተግባር ዓለም ሁሉ መዳኑን ነው። እግዚአብሔር ያንን የእምነት እርምጃውን እንደመዘገበውና እንደ ጽድቅ እንደቆጠረለት አልገባውም። *ካም እግዚአብሔር ያከበረውን ሰው አዋረደ።*

እግዚአብሔር ያከበራቸውን ከሚያዋርዱ ጭፍራዎች መካከል አያድርገን!

## 5. ልጆቹን ለመጋረድ አባት ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

በላባዎቹ ይጋርድሃል፣ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፡ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል።

መዝሙር 91፡4

## ኢየሱስና አባቱ

ኢየሱስ የአባቱን ኃይል ያውቅ ነበር። በመስቀል ላይ የተናገረው የመጨረሻ ቃሉ ራሱን በአባት እጅ አደራ የመስጠት ነበር። *"አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ።"በእነዚያ ቃሎች* ነፍሱን ከሞት መንጋጋ ፈልቅቆ በማውጣት በአባቱ እጅ አኖረ።

የሞት ጣዕር እርሱን ከብበውት እያሉ እንኳን አባቱን ተማመነ። እርሱን ለማስጣል ኃይል ያለው ማን እንደሆነ ያውቅ ነበር። ኢየሱስ ያከበረው ያ የአባት ኃይል ነው። ስለዚህ በምድር ላይ ሳለ ኢየሱስ የተናገራቸው የመጨረሻ ቃሎች እንዲህ ያለ እውነትን መፈንጠቃቸው የሚያስደንቅ አይደለም።

*ልጅዋ እንደ ተነጠቀባት ድብ እገጥማቸዋለሁ፣ የልባቸውንም ስብ እቀድዳለሁ፣ በዚያም እንደ አንበሳ እበላቸዋለሁ፡ የምድረ በዳም አውሬ ይነጣጠቃቸዋል።*

ሆሴዕ 13፡8





ወላጆች በልዕለ-ተፈጥሮአዊ መንገድ ልጆቻቸውን ለመጠበቅ ኃይል የለበሱ ናቸው።

ማናቸውም እንስሳት ለልጆቻቸው ሲሉ ሕይወታቸውን አሳልፈው ለአደጋ እንደሚሰጡ የታወቀ ነው። ልጅን ለአደጋ የሚያጋልጥ ማናቸውንም ዓይነት ጠላት ለመዋጋት ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ጥንካሬ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ችሎታ ነው።

እግዚአብሔር አባትን ሲሰጥህ፣ ጠላቶችህን ልጇ እንደተነጠቀባት ድብ በደጅ ይገጥማቸዋል።

ከአባትህ ሌላ ለአንተ ደህንነት ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት መለኮታዊ ኃይል የተሰጠው ማንም የለም። አባቶች ለልጆቻቸው ሕይወት እንዲዋጉ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል የተሰጣቸው ናቸው።

## 6. ትክክል የሆነውን ለማወቅ አባት ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

ልጆች ሆይ፣ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና።

ኤፌሶን 6፡1

ብዙ ጊዜ ማድረግ የሚገባንን ነገር ለማወቅ እንፈልጋለን። *በዚህኛው ወይስ በዚያኛው መንገድ ልሂድ?ትክክል* እና *ስሕተቱ* የቱ ነው? ብዙ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸው ሊያደርጉት የሚገባ ከሁሉም የላቀው የቱ እንደሆነ ያውቃሉ። አብዛኞቹ ወላጆች ለልጆቻቸው በልባቸው ያላቸው ፍላጎት ከሁሉም የላቀውን እንዲያገኙ ነው። የሚናገሩት ብዙ ጊዜ ትክክል የሚሆነው ለዚህ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወላጆችን መታዘዝ መደረግ የሚገባ ትክክለኛ ነገር መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ከአሁን በኋላ ትክክለኛው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ስትፈልግ፣ በወላጆችህ የተሰጡህን መመሪያዎች አስብ።

መንፈሳዊ አባቶችም ለመንፈሳዊ ልጆቻቸው ትክክለኛው ምን እንደሆነ የማወቅ ኃይል አላቸው። ብዙ ጊዜ አባት የሚናገረው ነገር

ትክክል ነው። ነገሮች የቀለሉ ሲሆኑ የሚችሉት የቱን ያህል ነው? አባቶችን መታዘዝ ሲደረግ የተገባ ትክክለኛ ነገር ነው!

## 7. ልጆቹን ለመመገብ አባት ያለው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

ልጅ በሚወለድበት ጊዜ እናት ለሕፃኑ ምግብ የሚሆን ወተት የማመንጨት ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ተሰጥቷታል። ከማርገዟ አስቀድሞ የእናት ጡቶች የስብ ክምችት ብቻ ናቸው። ምንም ወተት የላቸውም። ወተት አመንጭ ዕጢዎች ሕፃን የሚመጣ መሆኑን በማወቅ ማደግ መጀመራቸው ረቂቅ ጥበብ ነው። በዚሁ መንገድ እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑ አባቶችና እናቶች የእርሱ የሆኑ ልጆችን የሚመግቡበትን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሎች ያስታጥቃቸዋል።

በእግዚአብሔር የተቀባ መጋቢ ለመንጎቹ አባት ለመሆንና የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ምግብ ሁሉ ለመስጠት በልዕለ-ተፈጥሮአዊ መንገድ በኃይል የታጠቀ ሰው ነው።

አንድ ሰው በአንድ ጉባኤ ፊት ለመቆምና ለዚያው ጉባኤ ለሰላሳ ዓመታት ለመስበክ መቻሉ የሚያስደንቅ ነው። መጋቢው መልእክቶቹን ሁሉ የሚያገኘው ከየት ነው ብለህ መጠየቅህ አይቀሬ ነው። ሕዝቡስ አይሰለቸውምን ብለህ ልትጠይቅ ትችላለህ። እንዲህም ሆኖ አብዛኛው ምእመን ሌሎችን ሰባኪዎች የማይረዱ እስኪመስል ድረስ ከዚህ እረኛ ጋር የተቆራኙ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ልጆቹን እንዲመግብ ለአባት ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ችሎታን ይሰጣል።



*ምዕራፍ 12*

# አባቶች እንዴት ለብዙዎች መነሣትና መውደቅ ምክንያት እንደሚሆኑ

. . . ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው . . . ተሾሞአል . . .

ሉቃስ 2:34

ይህ በብዙ ሰዎች ላይ የሚያስከትለውን ውጤትአስመልክቶ ለጌታችንና ለንጉሣችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ጥንታዊ ትንቢት ነው። በእርሱ ብዙዎች ይነሣሉ፣ በእርሱም ብዙዎች ይወድቃሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛችን፣ ጌታችን፣ አዳኛችንና ንጉሣችን ው። አንዳንድ ሰዎች እንዲወድቁ፣ አንዳንዶች ደግሞ እንዲነሡ ያደርጋል፡ ፡ ኢየሱስ ሰዎች መልካም እንዲያደርጉ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እንዲወድቁና ለእርሱ በተሳሳተ መንገድ ምላሽ የሰጡትም እንዲጠፉ አድርጓል።

አባቶች በልጆቻቸው ላይ በሁለት መንገዶች ተጽእኖ ሊያደርጉ ይችላሉ። አባቶች ልጆቻቸውን በመባረክ እንዲነሡ ሊያደርጉና ወይም በመርገም እንዲወድቁ ሊያደርጉ ይችላሉ።

አባትና እርሱ የሚወክለው ሁሉ ከልጆቹ በኩል የተወሰኑ ምላሾችን ሊቀሰቅስ ይችላል። እነዚህ ምላሾች ከልጅ ወደ ልጅ የተለያዩ ሲሆኑ፣የአንዱን ልጅ መነሣት ወይም የሌላኛውን ልጅ መውደቅ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ልጅ ለአባት በተሳሳተ መንገድ ምላሽ ሲያደርግ እንደ እርሱ ባሉ ልጆች ላይ የተላለፈው ጥንታዊ እርግማን በሕይወቱ አውዳሚ ውጤት እንዲያስከትልበት ያደርጋል። ለአባቶቻቸው አግባብ ያለውን ምላሽ የማይሰጡ ሰዎች ምን እንደሚደርስባቸው ለማየት፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ረጅም ዘመን መኖር አያስፈልግህም።

በአባቶች አማካኝነት ሊመጡ የሚችሉ በረከቶችንና አደጋዎችን ማብራራት የዚህ መጽሐፍ ፍላጎት ነው:: ብዙ ሰዎች አባቶች ያሏቸውን ኃይልና ሥልጣን አይገነዘቡም:: አባት አንተን ወደ ሕልውና የሚያመጣ ሰው ነው:: በሕይወትህ ላይ ኃይልና ሥልጣን እንዲኖረው የሚያደርገው ይህ ነው::

ወረድ ብለው የተመለከቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት አንድም እንዴት እንደተነሡ አልያም እንዴት እንደወደቁ የሚናገሩ ናቸው::

## 1. አባቶች ልባቸው ከልጆቻቸው ሲርቅ ምድር በእርግማን እንድትመታ ያደርጋሉ::

መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል::

ሚልክያስ 4:6

## 2. አባቶች የልጆቻቸው ልብ ከእነርሱ ሲርቅ ምድር በእርግማን እንድትመታ ያደርጋሉ::

መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል::

ሚልክያስ 4:6

## 3. ኖኅ ልጁን ሴምን በልዩ መንገድ በመባረክ እንዲነሣ አደረገው::

እንዲህም አለ፡- የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፣ ከነዓንም ለእነርሱ ባሪያ ይሁን::

ዘፍጥረት 9:26

## 4. ኖኅ ልጁ ያፌት እንደሚሰፋ በመናገር እንዲነሣ አደረገው::





እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ፣ በሴምም ድንኳን ይደር፤ ከነዓንም ለእነርሱ ባሪያ ይሁን::

ዘፍጥረት 9:27

## 5. ይስሐቅ ያዕቆብን የባረኩትን ሁሉ በመባረክና የረገሙትን ሁሉ በመርገም ልጁ ያዕቆብ እንዲነሣ አደረገ::

እግዚአብሔርም ከሰማይ ጠል፣ ከምድርም ስብ፣ የእህልንም የወይንንም ብዛት ይስጥህ::

አሕዛብ ይገዙልህ፣ ሕዝብም ይስገዱልህ፡ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፣ የእናትህም ልጆች ይስገዱልህ፣ የሚረግምህ እርሱ ርጉም *ይሁን* የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን::

ዘፍጥረት 27:28-29

ይስሐቅም ያዕቆብን ጠራው፣ ባረከውም፣ . . .

ሁሉን የሚችል አምላክም ለብዙ ሕዝብ ጉባኤ እንድትሆን ይባርክህ፣ ያፍራህ፣ ያብዛህ፤

ስደተኛ ሆነህ የተቀመጥህባትን እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሰጣትን ምድር ትወርስ ዘንድ የአብርሃምን በረከት ለአንተ ይስጥህ፣ ለዘርህም እንዲሁ እንደ አንተ::

ዘፍጥረት 28:1-4

## 6. ያዕቆብ በይሁዳ ሕይወት ላይ ብዙ በረከቶችን በመናገር ልጁ ይሁዳ እንዲነሣ አደረገ::

ይሁዳ፣ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል፡ እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፤ የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ::

ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው፡ ልጄ ሆይ፣ ከአደንህ ወጣህ፡ እንደ አንበሰ አሸመቀ፣ እንደ ሴት አንበሳም አደባ፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል?

በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፣ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፣ ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፤ የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ *ይሆናል::*

ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል፣ የአህያይቱንም ግልገል በወይን አረግ፤ ልብሱን በወይን ያጥባል፣ መጎናጸፊያውንም በወይን ደም::

ዓይኑም ከወይን ይቀላል፣ ጥርሱም ከወተት ነጭ *ይሆናል::*

ዘፍጥረት 49:8-12

## 7. ያዕቆብ የልጁን የዛብሎንን ወሰን በማስፋት አነሣው::

ዛብሎን በባሕር ዳር ይቀመጣል እርሱም ለመርከቦች ወደብ ይሆናል፤ ዳርቻውም እስከ ሲዶና ድረስ ነው::

ዘፍጥረት 49:13

## 8. ያዕቆብ ልጁ ጋድ በመጨረሻ እንደሚያሸንፍ ትንቢት በመናገር እንዲነሣ አደረገ::

ጋድን ዘማቾች ይዘምቱበታል፡ እርሱ ግን ተከታትሎ ይዘምትባቸዋል::

ዘፍጥረት 49:19

## 9. ያዕቆብ በልጁ በአሴር ላይ የበረከት ቃሎችን በመናገር እንዲነሣ አደረገ::

የአሴር እንጀራው ወፍራም ነው፣ ለነገሥታቱም ደስ የሚያሰኝ መብልን ይሰጣል::

ዘፍጥረት 49:20

## 10. ያዕቆብ በመባረክና እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና ከወንድሞቹ በላይ አንድ ድርሻ እንደሚሰጠው በመተንበይ ልጁ ዮሴፍ እንዲነሣ አደረገ::

እስራኤልም ዮሴፍን፣ እነሆ እኔ እሞታሁ እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ይሆናል፣ ወደ አባቶቻችሁም ምድር ይመልሳችኋል::

እኔም ከአሞራውያን በሰይፌና በቀስቴ የወሰድሁትን ለአንተ ከወንድሞችህ አንድ እጅ አብልጬ ሰጠሁህ አለው::

ዘፍጥረት 48:21-22

በአባትህ አምላክ እርሱም የሚረዳህ፣ ሁሉንም በሚችል አምላክ እርሱም የሚባርክህ፣ በሰማይ በረከት ከላይ በሚገኝ፣ በጥልቅም በረከት ከታች በሚሠራጭ፣ በጡትና በማኅፀን በረከት፡





የአባትህ በረከቶች ጽኑዓን ከሆኑ ከተራሮች በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው፡ ዘላለማውያን ከሆኑ ከኮረፍቶችም በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው፡ እነርሱም በዮሴፍ ራስ ላይ ይሆናሉ፣ በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነው ራስ አናት ላይ::

ዘፍጥረት 49:25-26

## 11. ያዕቆብ ብዝበዛን እንደሚካፈል በማወጅ ልጁ ብንያም እንዲነሣ አደረገ::

ብንያም ነጣቂ ተኩላ ነው፡ የበዘበዘውን በጥዋት ይበላል፣ የማረከውንም በማታ ይካፈላል::

ዘፍጥረት 49:27

## 12. ያዕቆብ የልጅ ልጆቹን ምናሴንና ኤፍሬምን በራሱ ስም በመሰየም እንዲነሡ አደረገ::

ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፣ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ፣ ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅም ስም በእነርሱ ይጠራ፣ በምድርም መካከል ይብዙ::

ዘፍጥረት 48:16

## 13. ያዕቆብ የልጅ ልጁ ኤፍሬም በታላቅ ወንድሙ ላይ እንዲነሣ አደረገ::

አባቱም እንቢ አለ እንዲህ ሲል:- አወቅሁ ልጄ ሆይ፣ አወቅሁ ይህም ደግሞ ሕዝብ ይሆናል ታላቅም ይሆናል፡ ነገር ግን ታናሽ ወንድሙ ከእርሱ ይበልጣል፣ ዘሩም የአሕዛብ ሙላት ይሆናል::

በዚያም ቀን እንዲህ ብሎ ባረካቸው፣ በእናንተ እስራኤል እንዲህ ብሎ ይባርካል፣ እግዚአብሔር እንደ ኤፍሬምና እንደ ምናሴ ያድርግህ:: ኤፍሬምንም ከምናሴ ፊት አደረገው::

ዘፍጥረት 48:19-20

## 14. የሚንቋቸውን ልጆች ዓይኖች ቁራዎችና አሞራዎች ጎጥጉጠው እንዲያወጡ በማድረግ አባቶች ልጆች እንዲወድቁ ያደርጋሉ::

በአባትዋ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል፣ አሞራዎችም ይበሉአታል::

ምሳሌ 30:17

## 15. ኖኅ የባሪያዎች ባሪያ እንዲሆን በመርገም ልጁ ከነዓን እንዲወድቅ አደረገ::

ኖኅም ከወይን ጠጁ ሰካር ነቃ፣ ታናሹ ልጁ ያደረገበትንም አወቀ:: እንዲህም አለ:- ከነዓን ርጉም ይሁን፣ ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይሁን::

ዘፍጥረት 9:24-25

## 16. ያዕቆብ እንደማይሳካለት በመናገር ልጁ ሮቤል እንዲወድቅ አደረገ::

ሮቤል፣ አንተ በኵር ልጄና ኃይሌ፣ የጉብዝናዬም መጀመሪያ ነህ፣ የክብር አለቃና የኃይል አለቃ:

እንደ ውኃ የምትዋልል ነህ፣ አለቅነት ለአንተ አይሁን፤ ወደ አባትህ መኝታ ወጥተሃልና አረከስኸውም፡ ወደ አልጋዬም ወጣ::

ዘፍጥረት 49:3-4

## 17. ያዕቆብ ልጆቹ ስምዖንና ሌዊ እንደሚበታተኑ በማወጅ እንዲወድቁ አደረገ::

ስምዖንና ሌዊ ወንድማማች ናቸው፤ ሰይፎቻቸው የዓመፃ መሣሪያ ናቸው:: . . . ቁጣቸው ርጉም ይሁን፣ ጽኑ ነበርና ኩርፍታቸውምብርቱ ነበርና፣ በያዕቆብ እከፋፍላቸዋለሁ፣ በእስራኤልም እበታትናቸዋለሁ::

ዘፍጥረት 49:5፣7

## 18. ይስሐቅ ወንድሙን እንደሚያገለግል በማወጅ ልጁ ዔሳው እንዲወድቅ አደረገ::

አባቱ ይስሐቅም መለሰ አለውም:- እነሆ፣ መኖሪያህ ከምድር ስብ፣ ከላይ ከሚገኝ ከሰማይም ጠል ይሆናል፤

በሰይፍህም ትኖራለህ፣ ለወንድምህም ትገዛለህ፤ ነገር ግን በተቃወምኸው ጊዜ ቀንበሩን ከአንገትህ ትጥላለህ::

ዘፍጥረት 27:39-40





ይስሐቅም እንዲህ አለው፤ በረከት ከሞላበት ለምለም ምድር ርቀህ ትኖራለህ፤ የሰማይ ጠልም አታገኝም፤ በሰይፍህ ኃይል ትኖራለህ፤ የወንድምህም አገልጋይ ትሆናለህ፤ በተቃወምከው ጊዜ ግን ከእርሱ ጭቆና ትላቀቃለህ::

ዘፍጥረት 27:39-40 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

*ምዕራፍ 13*

# አራት የአባት ምልክቶች

ሁሉም የእግዚአብሔር ሰው አባት አይደለም። አባቶች ያልሆኑ መጋቢዎች፣ ሐዋርያት፣ አስተማሪዎችና ወንጌላውያን አሉ። በሌላ በኩል፣ አባቶች የሆኑ መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች፣ ወንጌላውያንና ሐዋርያትም አሉ።

ከእነዚህ ጥሪዎች ማናቸውም የአባትነትን ካባ ሊያጠልቅ ይችላል። አባትነት ላለህ ማናቸውም ጥሪ ተጨማሪ የፍቅር ደርዝ አለው።

1. አባት ወንድና ሴት ልጆችን የመውለድ ችሎታ አለው።

የአባት ዋነኛ ምልክቱ ዕድሜው አይደለም። አብዛኞቹ ሰዎች አባትነትን ከዕድሜ ጋር አንድ ማድረጋቸው አሳዛኝ ሁኔታ ነው። እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው። አብዛኞቻችን አባቶች የምንሆነው ወጣቶችና በሃያዎቹ ዕድሜያችን ሳለን ነው።

እያደግን ስንሄድ የአባትነትን ጥበብ ፍጹም እያደረግን እንሄዳለን። የአባት ዋነኛው ምልክት ልጆችን የማፍራት ችሎታው ነው። በነቢያቱ በኤልያስና በኤልሳዕ ሕይወት የታየው ሁኔታ ለዚህ እውነት ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ኤልሳዕ ከኤልያስ የበለጠ ቅብዓት የነበረው ቢሆንም፣ በአገልግሎቱ ተተኪም ሆነ ልጅ አላፈራም። ኤልሳዕ ቀደም ብሎ እግዚአብሔር የሰጠውን ብቸኛ ልጅ (ግያዝን) የረገመ ሰው ነበር። ግያዝ በአገልግሎቱ ልጅ በመሆን ፈንታ የለምጽ በሽተኛ ሆኖ ቀረ! ኤልሳዕ በእርሱ ላይ በመሳቃቸው ጥቂት ትናንሽ ልጆችንም የረገመ ሰው ነበር።

በነቢዩ ኤልሳዕ ሕይወት የመጣው ሁለት እጥፍ ቅብዓት ወደ አባትነት ሊለውጠው አልቻለም።

## 2. አባት ሰፊ የይቅርታ ልብ አለው።

ኤልያስ እንዴት በመጀመሪያው አገልጋዩ እንዴት እንደተተወ ልብ በል፣ እንዲህም ሆኖ ግን ሌላ አገልጋይ (ኤልሳዕን) አፍርቷል። የእንደገና ሞክር ልብ ነበረው።

> **እግዚአብሔርም** አለው:-ሂድ፣ . . . በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤል-ምሖምላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው።
>
> 1ነገሥት 19:15-16

ኤልሳዕ በኢያሪኮ፣ በዮርዳኖስ፣ በጌልጌላ፣ ወይም በቤቴል ለመቆየት እምቢ ባለ ጊዜ፣ ኤልያስ በኤልሳዕ ተናዶ አልረገመውም። እንዲያውም በዚህ ፋንታ ኤልሳዕ ለጠየቀው ሁለት እጥፍ ቅብዓት ቀና ልብ ነበረው።

አባቶች የማይሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ብዙ ጊዜ ንጡራዊነትና ፍጹማዊነት ያጠቃቸዋል።

እንዲህ ያለው ቅዠታዊ እምነት የእግዚአብሔር ጸጋ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ጸጋ እስከ ፍጽምና ጫፍ እስከምንደርስ ድረስ ተራራውን እንድንወጣ ይረዳናል።

እግዚአብሔር ፍጹም እስከምንሆን ድረስ መጠበቅ የሚያስፈልገው ቢሆን ኖሮ፣ ማናችንንም ለመጠቀም ከቶውንም አይችልም ነበር። ከሐዋርያት አንዳቸውም እንኳ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ብቃት ሊኖራቸው ባልቻለም ነበር።

## 3. አባት ብዙ ትዕግሥት አለው።

ብዙ ትዕግሥት ያለው ማናቸውም ሰው ብዙ ልጆች ሊኖሩት ይችላል። አባቶች ሰዎች እስኪለወጡና እስኪሻሻሉ መጠበቅ ይችላሉ። በመጨረሻ ለውጥ በሚመጣበት ሰዓትም አባት ከስፍራው አይታጣም። አባቶች ለሁሉም ዓይነት ሰዎች በልባቸው ስፍራ አላቸው። ከብዙ ውድቀቶች በኋላ፣ አንፀባራቂ ኮከብ እንደሚወለድ ማየት ይችላሉ።





የኮብላዩ ልጅ አባት ለጎስቋላው ተንከራቶ-ገብ ልጁ ከሁሉም ያማረውን ልብስና ቀለበት እንዲያመጡለት ያዘዘው ለዚህ ነው። የአባትነት ችሎታዎች የሌሉት ታላቁ ልጅ፣ በወንድሙ ተመልሶ መምጣት እንዴት እንደተበሳጨ ልብ በል!

የአባትነት ልብ በወንድና በሴት ልጆች ሊደርስ የሚችለውን የመንከራተት ዓይነቶች ሊያስተናግድ የሚችል ትልቅ የልብ ስፋት አለው። የሰማዩ አባታችን እንዲህ ዓይነቱ ልብ ባይኖረው ኖሮ ዛሬ ማናችን ልጆቹ መሆን እንችል ነበር?

## 4. አባት ልጆቹን ይመግባል።

ይህ የአባት ሚና የዕለት እንጀራችንን እንዲሰጠን አባታችንን በመጠየቅ በምንጸልየው በጌታ ጸሎት ውስጥ ይታያል። በተጨማሪም ከክፉ እንዲያድነንና እንዲረዳንም እንማጸነዋለን። እውነተኛ አባት ይመግባል፣ ይረዳልም።

ክብርንና ስጦታዎችን መቀበል የአባት ዋነኛ ተግባር አይደለም። እንዲያውም የእርሱ ተግባር ተቃራኒው ነው። ልጆቹን መመገብ የአባት ዋነኛ ተግባሩ ነው።

ዕድለኛ ከሆንህ ከልጆችህ ጥቂቶቹ ሊያስታውሱህና ሊያከብሩህ ይችላሉ። ክብርንና ስጦታዎችን መቀበል እንደ አባት ልትቀበልም ላትቀበልም የምትችለው መብት ነው።

አባቶች አቅጣጫን ማሳየት አለባቸው! አባቶች ክብካቤ ማድረግ አለባቸው! አባቶች የልጆቻቸውን ፍላጎቶች ማሟላት አለባቸው።

*ምዕራፍ 14*

# ልጅ *"አሎስ"* መሆን የሚገባው ሃያ ምክንያቶች

ልጅን የማፍራት ዓላማ እንደ አንተ ያለ ሌላ ሰው የማግኘት ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ልጆችን የሚሰጥበት ልዩ እቅድ የአንዱን ዓይነት ሌላ ሰው የማግኘት ነገር ነው።

*አሎስ* የተሰኘ ጠቃሚ የሆነ የግሪክ ቃል አለ። ትርጓሜውም *"የአንዱ ዓይነት ሌላ አካል"* ማለት ነው። ይህ *ሄትሮስ* ከተሰኘው፣ "ከተለየ ዓይነት ሌላኛው አካል" የሚል ትርጓሜ ካለው ግንባር-ገጠም ተቃራኒ ቃል ነው። ሄትሮስ የተሰኘው ቃል፣ ተመሳሳይ ነገር ግን ትንሽ ልዩ የሆነ ነገርን ለመግለጽ የሚውል ቃል ነው።

ልጆች ካሏቸው ጠንካራ ርዕየ-ቅዠት አንዱ "እኔ ዓለም ስትናፍቀኝ የነበርሁ ልዩ፣ አዲስና የመጀመሪያ የሆንሁ ሰው ነኝ" የሚል አስተሳሰብ ነው። የዚህ አስተሳሰብ ስሕተቱ "እኔ ከአባቶቼ የተሻልሁ ስለሆንሁ አባቶች ሊያደርጉት ከቻሉት በጣም የተለየ ነገር አደርጋለሁ" የሚል አስተሳሰብ ነው።

ይሁንና ዓላማችን ጌታን መውደድና እንድናደርግ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ ነው። ዓላማችን በምንም ዓይነት መንገድ ልዩና አቻ የለሽ ሰው መሆን አይደለም።

አባትህ የሚቆምለትን ሁሉ ለምን ትንቃለህ? ለምንስ እንዲህ እጅግ የተለየህና እጅግ አቻ የለሽ መሆን ትሻለህ? ከአንተ በፊት ከነበሩት ሁሉ ፍጹም የተለየህ ለመሆን እንድትፈልግ የሚያደርግህ ትዕቢታዊ ሕይወት አይደለምን? እኔ ከሌላ ከማናቸውም አገልጋይ የተለየሁ አለመሆኔን ለማየት በቅቻለሁ። እኔ ክርስቶስ ለመጨረሻ ዘመን ያቆየኝ ከማይገኝ ዝርያ የተገኘሁ አይደለሁም። እንደነዚህ ያሉ አስተሳሰቦች የሚያደርሱት ወደ ስሕተት ብቻ ነው። እኔ ከጌታ

ሰራዊት አንዱ አባል ነኝ:: ጌታን ለማገልገል ከሚሞክሩት አንዱ በመሆኔ በጣም ደስ ይለኛል::

በጌታ ቤት ውስጥ አስተማሪ ለመሆን ትፈልጋለህ? እግዚአብሔር አስተማሪዎችን ለብዙ ዓመታት ሲያሳድግ ኖሯል:: እግዚአብሔር የማስተማርን ስጦታ የሚሰጥህ ከሆነ፣ አንተም ከአንዱ ዓይነት ሌላኛው አስተማሪ ትሆናለህ:: ታላቅ ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ትፈልጋለህ? አገልግሎትህን በተሳሳተ መሠረት ላይ ተክለህ አትጀምር:: ቤተክርስቲያንህ የሚሆነው የአንዱ ዓይነት ሌላኛው አካል ብቻ ነው::

ከሁሉም ነገር ሙሉ በሙሉ የተለዩና አቻ የለሽ የመሆን ሃሳቦች፣ የሚመሩት ወደ ርዕየ-ቅዠት ብቻ ነው:: በፊትህ ቀመው ካሉት አባቶች የምትማርበት ጊዜው አሁን ነው:: እግዚአብሔር እንደ ጥንቱ ያሉ ብዙ እረኞችን ለማስነሣት ይፈልጋል:: ልምድ ካላቸው አባቶች በትሑት መንፈስ የተቀበሉና የተማሩ አባቶች!

እኔ "አሎስ" የተሰኘውን ቃል የአንዱ ዓይነት ሌላኛው ወገን የሚል ትርጉም እንዲሰጥ አድርጌ እጠቀመዋለሁ:: ልጆች ቢያንስ ከአንዱ ዓይነት ሌላኛው ወገን ለመሆን መመኘት እንደሚገባቸው አምናለሁ:: አባትህ ብዙ መልካም ነገሮች አሉት፣ ስለሆነም ቢያንስ እነዚያን መልካም ነገሮች ልትማር ምናልባትም የተሻለ ልታደርግ ትችላለህ::

## 1. በፍጥረት ውስጥ እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ፣ ልጅ አሎስ መሆን ይገባዋል::

> እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ . . .
>
> ዘፍጥረት 1:26

ጌታ ሰውን በፈጠረ ጊዜ፣ እርሱን የመሰለ ነገር ፈጠረ:: እንደ እኛ የሆነ አንድ ነገር፡ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን እንፍጠር አለ:: ሁላችንም ብንሆን የተፈጠርነው እንደ አሎስ ነው::





በእርሱ አምሳል ስለተፈጠርን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ብዙ አምሳያዎች አሉ:: እግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን የመንፈሶች አባት ነው:: ሰዎችም በአካል ውስጥ የሚኖሩ መንፈሶች ናቸው:: እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የምናውቀውን ሥላሴ ይመሠርታሉ::

ሰውም መንፈስ፣ ነፍስና አካል በመሆን አሃዱ ሥሉስ ኑባሬን ይመሠርታል:: ሰዎች በፈጣሪነትና በፈልሳፊነት ባሕርያቸው ሲራመዱ ከእግዚአብሔር ጋር አምሳልነት በግልጽ ያሳያሉ:: አሎስ፡ የአንዱ ዓይነት ሌላ ወገን!

## 2. መልካም ነገር ስለሆነ ልጅአሎስመሆንይገባዋል::

> ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃይን እንደ ወገኑ . . . አበቀለች:: . . . እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ:: . . . እግዚአብሔርም እንደ ወገኑ . . . ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ፈጠረ . . . እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ:: . . . እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፤ . . . እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ::
>
> ዘፍጥረት 1:12፣21፣25

> እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው:: እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ::
>
> ዘፍጥረት 1:27፣31

የአንዱ ዓይነት ሌላኛው ወገን መሆን መልካም ነገር ነው:: ኃያሉ አምላክ ነገሮች እንደ ወገናቸው ዝርያን እንዲያስገኙ አድርጎ ፈጠረ:: ሣር የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገንን ያበቅላል፣ ቡቃያዎች የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገንን ያስገኛሉ፣ እንዲሁም ዓሣ ነባሪዎች የአንዱን ዓይነት ሌላኛ ወገን ያስገኛሉ:: ሰውም እንኳ የሚወልደው የአንዱን ዓይነት ሌላኛ ወገን ነው::

ጌታ እግዚአብሔር የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን መልካም ነገር መሆኑን አየ! የተለየ ዓይነት ሌላ ወገንን ለመፍጠር ደፋ ቀና በማለት ፈንታ፣ መልካም የሆነውን እናድርግ::

ጥሩ ዘማሪ ለመሆን ትፈልጋለህ? የምትደርስበትን ደረጃ ዒላማ አድርግ። ልትጨብጠው የምትችለውን ነገር ተመኝ። ታላቅ ዘማሪ የሆነ ሰውን አሉስ ለመሆን ተመኝ።

3. ሁሉም ሰው የሌላ ሰው አሉስ ስለሆነ፣ ልጅ አሉስ መሆን ይገባዋል።

አንተ የአባትህ አሉስ ካልሆንህ የሌላ ሰው አሉስ ነህ ማለት ነው። ማንንም አንከተልም የሚሉ ሰዎች ያላወቁትን ሰው እየተከተሉ ናቸው። በአገልግሎት ታላቅ የሆነ ሁሉ የሌላው ሰው አሉስ ነው። ታላቅ የአምልኮ መሪ የሆነ ሁሉ በሌላ ቦታ የሚገኝ የአምልኮ መሪ አሉስ ነው። ታላቅ ወንጌላዊ የሆነ ሁሉ የሌላ ወንጌላዊ አሉስ ነው። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ታላቅ ሰው ሁሉ በሌላ ቦታ ያለ የእግዚአብሔር ሰው አሉስ ነው።

እያንዳንዱ ቅባት፣ የሌላ ቅብዓት አሉስ ነው። በጴጥሮስ፣ በያዕቆብና በዮሐንስ ላይ የመጣው ቅባት፣ በጌታቸው በኢየሱስ ላይ የነበረ ቅብዓት ነው።

በኤልሳዕ ላይ የነበረ ቅብዓት በኤልያስ ላይ የነበረ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ቅብዓት ነበር።

በቅርቡ፣ በደቡብ አፍሪካ በአንድ ሆቴል ቁርስ እየበላሁ ነበርሁ። ሙዚቃውና ሲዲው በመላው ዓለም ተደማጭነት ያለው ዝነኛ ክርስቲያን ዘማሪ መጣ። አብረን እንደተቀመጥን ከመጋቢዎቼ አንዱ፣ መጋቢ ኦኮ፣ "በሙዚቃ አገልግሎትህ መስህባዊ ተጽእኖ ያሳረፈብህ ማን ነው?"የሚል ጥያቄ ጠየቀው።

እርሱም ሲመልስ፣ "ኦ! ለእኔ ታላቅ መቀስቀሻ የሆነኝ አንድሬ ክሩች ነው" ሲል መለሰ።

እኔም ይህ ሰው ለምን እንዲህ መልካም እየሆነለት እንዳለ ወዲያውኑ ገባኝ። ምክንያቱም እርሱ ሐፍረት የማይሰማው አሉስ





ነበር! የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ለመሆን ኩራት የሚሰማው ነበር።

በማናቸውም መስክ እጅግ የሚሳካላቸው ሰዎች ሁሉ፣ የአንዱን ዓይነት በቅርበት የሚከተሉ አሉስ እንደሆኑ አይቻለሁ። ስብከት፣ ዝማሬ፣ ፈውስ፣ ወይም መጋቢነት ቢሆን መርሁ ያው ነው። እግዚአብሔር የአንዱን ዓይነት ሌላኛ ወገን እየሠራ ሲሆን ያ መልካም ነገር መሆኑን ያለማቋረጥ ይናገራል።

4. አሉስ መሆን፣ ልጅንትሑት ስለሚያደርገው መልካም ነገር ነው።

አሉስ መሆን ትሕትና ያለበት ነገር ስለሆነ መልካም ነው! ከአንተ በፊት ካሉት በትሕትና መማር መልካም ነገር ነው።

ወጣቶች ለእነርሱ መንገድ ያሳዩአቸውን ሰዎች ማክበራቸው መልካም ነው።

ልጆች ትሑት ሲሆኑ፣ የእግዚአብሔር በረከቶች ወደሚቀጥለው ትውልድ ይተላለፋሉ። አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ለዚህ ትውልድ መኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን የሆነ ለሚቀጥለው ትውልድም ይኖራል።

አንድ ታላቅ ዘማሪ ብቻ ሳይሆን የአንዱ ዓይነት ብዙዎች ይሆናሉ። እነዚያ የተሰጡ ድምፆች በሚያስፈልጉበት ስፍራ ሁሉ ቅባቱ እንዲፈስ ለመርዳት በዚያ አሉስ ይገኛል ማለት ነው።

5. አሉስ መሆን፣ ታላቅ ሰው እንዲሆን ስለሚረዳው ልጅ አሉስ መሆን ይገባዋል።

ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን ወስን፣ ታላቅ የአምልኮ መሪ ለመሆንም ወስን። የመዘምራን ቡድን መሪ ወይም ሰዎች የማይረሱት እረኛ ሁን። ይህን ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው?መልሱ ቀላል ነው፡ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ሁን።

በእግዚአብሔር ታላቅ ለመሆን የሚያስችል ቀመርን በማሰብ ውኸንብር ውስጥ አንግባ።

ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ አንሂድ። የአንዱን ዓይነት ሌላኛ ወገን ወደ ማፍራት የእግዚአብሔር ዘዴ በቀጥታ እንሂድ። አንዱ ታላቅ ከሆነ፣ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገንም ታላቅ ይሆናል። አንዱ የተቀባ ከሆነ፣ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገንም የተቀባ ይሆናል። አንዱ ኃይለኛ ከሆነ፣ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገንም ኃይለኛ ይሆናል።

እኔ እግዚአብሔር እንዳገለግለው ጠርቶኛል ብዬ አምናለሁ። እኔ ልዩም የተለየሁም አይደለሁም። እኔ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ካስነሣቸው ዓይነት አንዱ ወገን ነኝ። ተመሳሳይ ጥሪ ያለውን ሌላ ሰው አግኝቼ በሚቻለኝ ዓቅም ሁሉ እርሱን ለመከተል እፈልጋለሁ።

ወደ ቤት መሄጃችን ሩቅ አይደለም፣ እንሄዳለን። ያዝ-ቀመስ ለማድረግ ጊዜ የለኝም። በሙከራም ጊዜዬን ለማጥፋት አልችልም። ምክንያቱም ጌታ በሚጠራኝ ሰዓት ምናልባት ገና በሙከራዬ አጋማሽ መንገድ ላይ መገኘትአልፈልግም።

የሚያስፈልገኝ በቀጥታ ወደ ነጥቡ መድረስ ነው። ቅባቱን እፈልጋለሁ፣ በፍጥነትም እሻዋለሁ! በደንብ መስበክ እፈልጋለሁ፣ በደንብ መስበክን አሁኑኑ እፈልገዋለሁ! ሕመምተኛን መፈወስና ሙታንን ማስነሣት እፈልጋለሁ፤ ደግሞም እግዚአብሔር በሰጠኝ ጊዜ ውስጥ እንዲደረግ እሻለሁ።

አንተስ? የአንዱ ዓይነት ሌላኛው ወገን እስከምትሆን ድረስ በስንት ዓመታት ሙከራ ታቅማማለህ?

የሚሠሩ ቤተክርስቲያኖች ዓይነታቸው በተወሰነመጋቢያን የምገባ አገልግሎት ይሰጣቸዋል።

የሚያድጉ ቤተክርስቲያኖች ዓይነታቸው በተወሰነ ወንዶችና ሴቶች ይመገባሉ። የአንተም ራእይ ይኸው እንደመሆኑ መጠን፣ ለምን የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን አትሆንም?





ለቅባቱ መንገዱ አሉስ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ለመሆን መንገዱ አሉስ ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ነገሮች ለመግባት ክፍቱ በር አሉስ ነው።

ማስመሰል አልችልም። እኔ የማደርገው ከሌሎች የተማርሁትን ነው። እኔ የማስተምረው ከአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን የተማርሁትን ነው። የማገለግለው ከሌላ ሰው በተማርሁት መሠረት ነው። የአንዱ ዓይነት ሌሎች ወገኖችን አጥብቄ በመከተሌ እፍረት አይሰማኝም። እግዚአብሔር መልካም ነው ካለ በእርግጥም በጣም መልካም ሊሆን ይገባዋል። ለእግዚአብሔር መልካም ከሆነ፣ ለእኔም መልካም ነው።

## 6. ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር ስለሌለ ልጅ አሉስ መሆን ይገባዋል።

አሉስ በምትሆንበት ወቅት፣ ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ትገነዘባለህ።

> የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፣ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው፤ ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም። ማንም እነሆ፣ ይህ ነገር አዲስ ነው ይል ዘንድ ይችላልን? እርሱ ከእኛ በፊት በነበሩት ዘመናት ተደርጎአል።
>
> መክብብ 1:9-10

በእርግጥ፣ ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም። ይህ መቀበል የሚገባህ እውነት ነው። የምታበረክተው ምንም አዲስ ነገር የለም፣ ደግሞም ሕይወትህ በእርግጥ ልዩ የሆነ ነገር ሊያመጣ አይችልም።

አንድ ጊዜ እንደ ብዙዎቹ አገልጋዮች፣ አዲስ ነገር እያስተዋወቅሁ ነኝ ብዬ አሰብሁ። ሌላ ማንም ከዚህ ቀደም ኖሮት የማይውቅ የሆኑ ስጦታዎችና ሃሳቦች ያሉኝ መሰለኝ።

ነገር ግን በጊዜ ሂደት ውስጥ አደርግ የነበረው ሁሉ ከዚህ ቀደም የተደረገ መሆኑን ተገነዘብሁ። የማደርገውና የምናገረው እያንዳንዱ ነገር ሌሎች ሰዎች ከእኔ በፊት ያደረጉት መሆኑን ደረስሁበት።

ስለ አገልግሎቴ እውነቱ ነገር ከልብ የማደንቃቸውን ሌሎች ሰዎች በብዙ ጥረት የምከተል መሆኔ ብቻ ነው። እንደ እነርሱ መሆን እፈልጋሁ፣ ይህን ለማለትም አላፍርም! መንፈሳቸውን እወደዋለሁ! አደራረጋቸውን እወደዋለሁ! የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን መሆን ከቻልሁ፣ ለእኔ ይህ ታላቅ ስኬት እንደሆነ አስባለሁ።

7. አሉስ መሆን፣ ከጅምሩስኬታማና ተግባራዊእንዲሆን ስለሚያደርገው ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

ሙከራ በማድረግ ከሚያጋጥም ጉዳት ነፃ ትሆናለህ። በዘመናት መካከል የሠሩትን መርሆች ስታገኝ፣ የዓመታት ጊዜያትን ከማባከን ነፃ ትሆናለህ።

8. አሉስ መሆን፣ አዲስ ስም ለመፍጠር ከሚደረግ ችግር ስለሚያድነውልጅ አሉስ መሆን ያፈልገዋል።

ስም ማስመዝገብ ቀላል ነገር አይደለም። ስሞች በብዙ ገንዘብ የሚሸጡት ለዚህ ነው። ጥሩ ስም በምድር ላይ እጅግ ውድ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው። የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን መሆን ማለት አንተ አንድ ስም የያዝህ ሌላኛው ወገን ነህ ማለት ነው። አሉስ ሆኖ መጠራት ካልከበደህ አሉስ በመሆንህ በእውነት ትጠቀማለህ።

9. አሉስ መሆን፣ በቡድን መካከል ያለውን ቦታ እንዲያውቅ ስለሚያደርገውልጅ አሉስ መሆኑአስፈላጊ ነው።

የቡድኑ አንድ አካል ብቻ መሆንህን ለመቀበል ትሕትና ይጠይቃል። ሰዎች በአገልግሎትህ ሲደነቁ፣ መልእክትህ የመጀመሪያው አለመሆኑን ለመግለጥ ቀላል አይደለም። ሰዎች በአንተ ስልት ሲደነቁ፣ ሁሉንም ነገር ከሌላ ሰው እንደተማርህ መግለጡ ቀላል አይደለም። አሉስ መሆን ስለሚሰጠው ትሕትና እግዚአብሔር ይመስገን።





አንዱ ይዘራል፣ አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና።

ዮሐንስ 4፡37

የአንዱ ዓይነት ሰዎች አንድ ላይ ሲሠሩ፣ በእውነት እንደ ቡድን ሆኖ፡ "አንዱ ይዘራል፣ አንዱም ያጭዳል" መሥራት ይቻላል። ሰዎች የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ካልሆኑ፣ አንድ ላይ መሥራት በጣም ከባድ ነው። በቤተክርስቲያን አመራር ግጭቶች የሚፈጠሩት የተለያዩ ራእዮች ያሏቸው ሰዎች አንድ ላይ ሲሠሩ ነው።

ለህብት ምኞት ያለኝ ከሆንሁ፣ የእኔ ውሳኔዎች ፍሬዎችን ለማፍራት ምኞት ካለው ሰው የተለዩ ይሆናሉ። ከተለያዩ ዓይነቶች ስለምንሆን የማያቋርጡ ግጭቶች ይፈጠራሉ።

የአንዱ ዓይነት መጋቢዎች አብረው በሚሠሩበት፣ መጋቢያንን ከአንዱ ቤተክርስቲያን ወደ ሌላኛው ቅርንጫፍ ቤተክርስቲያን ማዛወር ቀላል ነው። አንድን ቤተክርስቲያን የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን በሚረከብበት ጊዜ፣ ለቤተክርስቲያን ታላቅ ብርታት ይሆናል።

ሁሉቱም መጋቢያን ጌታን ለማስደሰት "የተወሰነ የጊዜ ገደብ ያላቸው" የጌታ ጊዜያዊ አገልጋዮች መሆናቸውን ይገነዘባሉ። በዚያ ለዘላለም የሚቀይ፣ በዚያ ለግል ጥቅም የሚሆን ማንም የለም። እያንዳንዱ መጋቢ በጊዜው ለጌታ ከሁሉም የላቀ ሥራን ለመሥራት ይመኛል። አንዱ ቤተክርስቲያንን ይተክላል፣ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ደግሞ ውኃ ያጠጣዋል። የአንዱ ዓይነት ስለሆኑ ለውጥ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁላቸውም ይገነዘቡታል። ይህን እንጂ በቤተክርስቲያን መዋቅር ውስጥ የሚደረጉ እንደነዚህ ያሉ ለውጦች፣ የተለያዩ ምኞቶች ያሏቸው ሰዎች በሚገኙበት ቤተክርስቲያን አይሠራም።

ጳውሎስና አጵሎስ አሉሶች ነበሩ፡ የአንዱ ዓይነት ነበሩ።

የእግዚአብሔር ጸጋ እንደተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፣ ሌላውም(አጵሎስ) በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።

1 ቆሮንቶስ 3፡10

ጳውሎስ ሌላው እንዲያንጽበት መሠረትን ማስቀመጥ አላስቸገረውም። ሌላው እንዲቀጥል መፍቀድ ያለበትን ሥራ መጀመር ጳውሎስን አላሳሰበውም። ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን መሠረተ፣ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን (አጵሎስ) አጠጣው። በአሉስ ውስጥ ስትገኝ የቡድን አካል ብቻ መሆንህን ትገነዘባለህ።

10. አሉስ መሆን፣ በሌላው የሚደገፍና በግ-መሰል እንዲሆን ስለሚያደርገውልጅ አሉስ መሆን ያፈልገዋል።

የበግ ባሕርይ ከአባብ ባሕርይ የተለየ ነው። ነፃና ብቸኛ መሆን የአባቦች ባሕርይ ነው። ይህ ከጌታ ጋር መራመድ ከፈለግህ መሆን ከሚገባህ ሁኔታ በጣም የሚጣረስ ነው። የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን መሆን፣ በሌላው ላይ መደገፍ፣ ከሌላው መማርና ሌላውን መከተል እንደሚገባህያመለክታል።

11. አሉስ መሆን፣ ለአንዱ ዓይነት የሠሩትን ቀመሮችና ዘዴዎች ስለሚሰጥ ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ለመሆን ስወስን፣ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች ቢኖሩ የእኔ አሉሶች የተጠቀሙባቸው መንገዶች ናቸው። ለእርሱ የሠራ ለእኔም ይሠራል። በአሉሶቼ ውጤቶችን ያስመዘገቡ ሥርዓቶችንና ዘዴዎችን እንዳሉ እቀዳቸዋለሁ። አንድ ዓይነት ለመሆን ስለምገሠግሥ፣ ለእርሱ የሠሩ አንድ ዓይነት ዘዴዎች በእርግጥ ለእኔም ይሠራሉ።

12. አሉስ መሆን፣ የአንድ ቡድን አባል እንዲሆን ስለሚያስችለው ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

አንድ ዓይነት የሆኑ የአንድ ቡድን ሰዎች ብዙ ነገሮች በጋራ አላቸው። ተመሳሳይ ተግዳሮቶችና ተመሳሳይ ተሞክሮዎች ስለሚኖራችሁ አሁን በነፃነት ኅብረት መፍጠር ትችላላችሁ። አሉስ የሆኑ መጋቢያንን በምገናኝበት ማናቸውም ጊዜ፣ ዘና ብዬ የእነርሱን





አብሮነት ልደሰትበት እችላለሁ። ተግዳሮቶቼን ላካፍላቸውና ተመሳሳይ ተሞክሮ ካላቸው የሌሎች ሁኔታም መበረታቻ ላገኝ እችላለሁ።

13. በአገልግሎት ውስጥ መንገዱን የሚያገኘው በዚሁ ሁኔታ ስለሆነ፣ ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

ለአገልግሎት የተጠሩ ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ጎዳና እንዴት እንደሚሄዱ አያውቁም። እግዚአብሔር እንደጠራቸው ያውቃሉ፣ ነገር ግን እንዴት ወደ ፊት እንደሚራመዱ ፍንጭ ያጣሉ። ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዴት አድርገው ወደ አገልግሎት ከፍታዎች እንደሚወጡ አያውቁም። ሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ታላላቅ ነገሮችን ሲያከናውኑ ያያሉ፣ ነገር ግን እነርሱም እነዚያኑ ማድረግ እንደሚችሉ አያውቁም!

አንድ ዓይነት ነገሮችን የማድረጊያ መንገዱ አሁን ግልጽ ነው። ልዩ፣ ፈንጠር ያልህ ወይም አምሳያ የሌለህ ለመሆን አትሞክር። ዝም ብለህ አሉስ ሁን። የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ሁን።

እነርሱ የተጠቀሙበትን ዘዴ ተጠቀም።

በቅርበት ተከታተላቸው።

እነርሱ የሰበኩትን ስበክ።

እነርሱ በጸለዩበት መንገድ ጸልይ።

እነርሱ እግዚአብሔርን በፈለጉበት መንገድ ፈልግ። ያለ ጥርጥር የአንዱ ዓይነት ሌላኛው ወገን ትሆናለህ።

### 14. ወደ አዳዲስ የአገልግሎት ዘርፎች በፍጥነት እንዲገባ ስለሚረዳው ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

አሉስ መሆን በሕይወትም ሆነ በአገልግሎት የእድገትህን መጠን ያፋጥናል። በሚገባ የተፈተነ መንገድ ስለምትከተል ከአንተ ከቀደሙት ዘንድ ትጠቀማለህ፡

ሌሎችን ባዘገዩ ነገሮች አትዘገይም። የአንተው ዓይነት ሌሎች እንዴት እንደምታሸንፋቸው ፍንጭ ስለሚሰጡህ እንቅፋቶችን በፍጥነት ትወጣቸዋለህ።

ሰዎች ነገሮችን መሞከር በማያስፈልጋቸው ጊዜ በፍጥነት ይራመዳሉ።

አንድ ቀን ከአንድ ሰው ጋር ወደ አንድ ቦታ እየሄድሁ ነበር። እርሱ በራሱ መኪና ከፊቴ ቀድሞ ሲሄድ እኔም በራሴ መኪና እከተለው ነበር። ብዙ ትራፊክ ውስጥ ሲገባ ስልክ ደወለልኝና ብዙ ትራፊክ ስላለ እኔ በመጣሁበት አትምጣ ብሎ ነገረኝ። በእርሱ ችግር ውስጥ እኔ እንዳልገባ እርሱ ስላዳነኝ ከእርሱ ቀድሜ ደረስሁኝ። ከአንተ ቀድሞ ካለ ሰው ግብአት ማግኘት የተለመደ አሠራር ነው። አሉስ መሆን በመሠረቱ የተለመደ አስተሳሰብን የመጠቀም ጉዳይ ነው።

### 15. አሉስ መሆን፣ ችግሮች ሲገጥሙ የሚረዳ ስለሆነልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

ዶክተሮች ለምን አስቸኳይ ሁኔታ ውስጥ የተረጋጉ እንደሚሆኑ ጠይቀህ ታውቃለህ? ምክንያቱ የአንዱ ዓይነት (አሉስ) ብዙ ሁኔታዎችን ስላዩ ነው። የደረሰብህን ዓይነት ችግር ቀደም ብለህስላወቅህየአሉስን ችግር ወይም ምስቅልቅል ሁኔታ ስትጋፈጥ የተረጋጋህ ትሆናለህ። ስለዚሁ ዓይነት ሁኔታ ስለተማርህ በቶሎም ትወጣዋለህ።





### 16. አሉስ የመሆንን ዘዴበመጠቀም የተባዛ ጉልበት ስለሚፈጠር ልጅ አሉስ መሆን አለበት።

አንድ ዓይነት የሆኑ ሰዎች በጋራ የሚያካሂዱት ጥረት የበለጡ ውጤቶችን ያስከትላል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ከአንድ እንደሚሻል ያስተምራል። ቀጥሎም በሦስት የተገመደ ገመድ በቀላሉ እንደማይበጠስም ይናገራል።

> አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ፤ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።
>
> መክብብ 4:12

የአንዱ ዓይነት ሁለቶች ከአንድ ይሻላሉ! የአንዱ ዓይነት ሦስቶች ፈጥነው አይበጠሱም። የአሉስ የተባዛ ጥንካሬ በጣም ከፍተኛ ነው። አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አብረው ሲጓዙና ሲሠሩ ታላቅ ኃይል ይለቀቃል።

> እርሱ አምላካቸው ካልሸጣቸው፣ እግዚአብሔርም አሳልፎ ካልሰጣቸው፣ አንድ ሰው እንዴት ሺህን ያሳድድ ነበር?ሁለቱሳ እንዴት አሥሩን ሺኅ ያሸሹ ነበር?
>
> ዘዳግም 32፡30

የአንዱ ዓይነት አንድ፣አንዱን ሺህ ያሸሻል፣ ነገር ግን የአንዱ ዓይነት ሁለት፣ አሥሩን ሺህ ያሳድዳል።

### 17. አሉስ መሆን፣ ተፈጥሮአዊ የማደጊያ መንገድ ስለሆነ ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

ሁሉም ፍጥረት የሚባዛበት ተፈጥሮአዊው መንገድ የአንዱን ዓይነት ሌላ ወገን በመውለድ ነው።

> ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ፣ ዘሩም ያለበትን ፍሬ የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔርም . . . ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፣ እንደ ወገኑ . . . ፈጠረ፣ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔርም የምድር አራዊትን . . . እንደ ወገኑ አደረገ፣ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።
>
> ዘፍጥረት 1፡12፣ 21፣ 25

ቤተክርስቲያን ከክብር ወደ ክብር የምታድግበት ተፈጥሮአዊ መንገድ የአንዱን ዓይነት መጋቢዎች፣ መሪዎችና እረኞች በማፍራት ነው።

ወደ ፊት ለመራመድ ሌሎችም መንገዶች የሉም ብዬ አልከራከርም። ነገር ግን እኔ ማካፈል የምችለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማየውን ነው። አሎስ! አሎስ! አሎስ! እግዚአብሔር እንደሰጠኝ አባቶች መሆን እፈልጋለሁ። በቀጥታ እንደ ክርስቶስ መሆን እፈልጋለሁ።

> በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።
>
> 1 ዮሐንስ 4፡17

## 18. አሎስ መሆን፣ ለመቀባት ቁልፍ ስለሆነ ልጅ አሎስ መሆን ያስፈልገዋል።

> እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ (አሎስ) አጽናኝ ይሰጣችኋል፤
>
> ዮሐንስ 14፡16

ከላይ በቀረበው ክፍል መሠረት፣ ኢየሱስ አጽናኙን የአንዱ ዓይነት ሌላ ወገን ነው ይላል። በዚህ ቁጥር ሌላ የሚለው ቃል፣ አሎስ የተሰኘው የግሪኩ ቃል ነው። ይህም ማለት የአንዱ ዓይነት ሌላኛ አጽናኝ ማለት ነው። ኢየሱስ ሌላ ተብሎ ሊተረጎም የሚችለውንም ሄትሮስ የተሰኘውን ቃል መጠቀም በቻለ ነበር። ነገር ግን ሄትሮስ ቢሆን ኖሮ ትርጉሙ የተለየ ዓይነት እርዳታ የሚል ይሆን ነበር።

መንፈስ ቅዱስ (አጽናኙ)ቅባቱ እርሱ ነው። ኢየሱስ የአንዱን ዓይነት ሌላ አጽናኝ እሰጣችኋለሁ ብሎ ተስፋ በገባ ጊዜ፣ የአንዱን ዓይነት ሌላ ቅብዓት እሰጣለሁ ማለቱ ነበር። እርሱ ያገለገለበት ያው ዓይነት ቅብዓት ለሐዋርያትም ተጠብቆአል ማለት ነው።

አብዛኞቹ መጋቢያን ይህን ግልጽ እውነት ቢረዱ በአገልግሎታቸው ይገሠግሡ ነበር። እግዚአብሔር ሊሰጥህ የሚፈልገው አዲስና ልዩ





ቅብዓት የለም። የሚሰጥህ ያንኑ የአንዱን ዓይነት ሌላ ወገን ነው። ሐዋርያትም እንኳ ተስፋ የተገባላቸው የአንዱን ዓይነት ሌላ ወገን ነው።

ብቃትን የማግኛ መንገዱ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ እንደሆነ የዓለም ሥርዓት ያስተምራል። ነገር ግን በአገልግሎት ምንም ነገር ለመሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊው አምሳል ወይም ቅርጽ አሎስ መሆን ነው። አሎስ መሆን እግዚአብሔር አገልጋዮችን የሚያፈራበት ተፈጥሮአዊው መንገድ ነው። ብዙ ጊዜ አሎስ እንዳንሆን የሚያግዱን ትዕቢትና ኩራት ናቸው።

አገልግሎት በጣም ከባድ ነገር ነው። እግዚአብሔርን ማስደሰት ብዙ ጸጋንይጠይቃል። ትሕትና በአገልግሎት ታላቅ ስኬት ቢሆንም በቀላል የሚደረስ አይደለም። አብዛኞቻችን የምንከተለው የታላቅነት ሰብአዊ አመላካቾችን ነው። ነገር ግን ክርስቶስ እውነተኛ ታላቅነት ምን እንደሆነ አሳይቷል። አንድን ሰው በቅንነት መከተል፣ ታዛዥ መሆንና በትሑት መንፈስ ፍሬን ማፍራት ተራ ሥራ አይደለም። እግዚአብሔር ከእኛ ብዙ አይፈልግም። የሚጠብቅብን የአንድ የሚሠራ ነገር አሎስ እንድንሆን ነው።

### ኤልያስ፣ ኤልሳዕና መጥምቁ ዮሐንስ

ኤልያስ ሁለት የታወቁ አሎሶች ነበሩት፡ ኤልሳዕ በኤልያስ የነበረውንቅብዓት ሁለት እጥፍ ጠየቀና አገኘ (2 ነገሥት 2፡9)። ኢየሱስ ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስን እንደ ኤልያስ ገልጾታል። በትክክል፣ "ሊመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው" ብሎታል (ማቴዎስ 11፡14)።

የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን የሆነ ቅብዓት በሚኖርህ ማናቸውም ጊዜ፣ አንድ ዓይነት ሥራን ይሠራል። እነዚህን ሁለት አሎሶች በቅርበት መመርመር ይህ አባባል ምን ያህል እውነት እንደሆነ ያሳያል። ይህ መገለጥ የአሎስን ቅብዓት እንድታገኝ ሊያነሣሣህ ይገባል።

## ኤልሳዕ የኤልያስ አሎስ የሆነባቸው ስድስት ምክንያቶች

1. ኤልያስ የትንሹ ልጅ ሕይወት እንዲመለስ ጸለየ (1 ነገሥት 17:17-24)፣ ኤልሳዕም ደግሞ የሞተው ልጅ እንዲነሣ ጸለየ (2 ነገሥት 4:32-37)።

2. ኤልያስ ታምራዊ ነገሮችን አደረገ (1 ነገሥት 21:28-29)፣ ኤልሳዕም እንዲሁ ታምራዊ ነገሮችን አድርጓል (2 ነገሥት 8:12)።

3. ኤልያስ በአገልግሎቱ አስራ ስድስት ታምራትን ያደረገ ሲሆን ኤልሳዕ ደግሞ ሠላሳ ሁለት ታምራትን አድርጓል።

4. ኤልያስ ለሦስት ዓመታት ተኩል ረሃብ እንዲሆን አደረገ (1 ነገሥት 17:1፤ ያዕቆብ 5:17)፣ ኤልሳዕ ደግሞ በጸለየ ጊዜ ለሰባት ዓመታት ረሃብ ሆነ (2 ነገሥት 8:1-2)።

5. ኤልያስ ለመበለቲቱ ዱቄቱንና ዘይቱን አብዝቶላታል (1 ነገሥት 17:8-16)፣ ኤልሳዕ ደግሞ የመበለቲቱ ዘይት እንዲጨምር አድርጓል (2 ነገሥት 4:1-7)።

6. ኤልያስ የዮርዳኖስን ወንዝ አድርቋል (2 ነገሥት 2:8)፣ ኤልሳዕም የዮርዳኖስን ወንዝ አድርቋል (2 ነገሥት 2:13-15)።

## መጥምቁ ዮሐንስ የኤልያስ አሎስ የሆነባቸው አስራ አንድ ምክንያቶች

1. ኤልያስ በመንፈስና በኃይል የተቀባ ነበር (2 ነገሥት 1:9-10)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ በመንፈስና በኃይል የተሞላ ነበር (ሉቃስ 1:17)።





2. በአንድ ወቅት ኤልያስ በምድረበዳ ይኖር ነበር (1 ነገሥት 17:3፣ 19:4)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ በምድረበዳ በመኖር ይታወቅ ነበር (ሉቃስ 1:80)።

3. ኤልያስ ልዩ የሆነ አለባበስ ነበረው (2 ነገሥት 1:8)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ ከግመል ጠጉር የተሠራ ልብስ ይልብስ ነበር (ማቴዎስ 3:4)።

4. ኤልያስ ከቁራዎች አፍ ባዕድ የሆነ ምግብ ይመገብ ነበር (1 ነገሥት 17:4)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ አንበጣና የበረሃ ማር ይመገብ ነበር (ማቴዎስ 3:4)።

5. ኤልያስ በዘመኑ የነበረውን ንጉሥ፣ ንጉሥ አካዝን ተጋፍጧል (1 ነገሥት 18:17-18)፣ መጥምቁ ዮሐንስም በዘመኑ የነበረውን ገዥ፣ ንጉሥ ሄሮድስን ተፋጧል (ማቴዎስ 14:3-4)።

6. ንጉሡ ኤልያስን ለመግደል ፈለገ (2 ነገሥት 1:9)፣ መጥምቁ ዮሐንስንም እንዲሁ ንጉሡ ለመግደል ፈልጎአል (ማቴዎስ 14:3-5)።

7. ኤልያስ ስለ ጽድቅ ሰብኳል (1 ነገሥት 18:20-24)፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ዋና መልእክት ንስኃ ነበር (ማቴዎስ 21:32)።

8. ኤልያስ በንጉሡ ሚስት የተጠላ ነበር (1 ነገሥት 19:1-7)፣ መጥምቁ ዮሐንስም በሄሮድስ ሚስት የተጠላ ነበር (ማቴዎስ 14:3-10)።

9. ኤልያስ በምድሩ ታዋቂ ሰው ነበር (1 ነገሥት 18:25-41)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ በዘመኑ በነበረበት አካባቢ ታዋቂ ሰው ነበር (ማርቆስ 11:32)።

10. ኤልያስና መጥምቁ ዮሐንስ በትንቢት የተቆራኙ ነበሩ (ሚልክያስ 3:1፤ ሚልክያስ 4:5-6፤ ኢሳይያስ 40:3)።

11. ኤልያስ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀዳሚ ሰው ይሆናል (ሚልክያስ 4:5-6)፣ መጥምቁ ዮሐንስም እንዲሁ የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ቀዳሚ ሰው ነበር (ሚልክያስ 3:1)።

19. አሎስ መሆን፣ ለማስተማርና ለመስበክ ጥበብ ቁልፍ ስለሆነ ልጅ አሎስ መሆን ያስፈልገዋል።

ሌላ (አሎስ) ምሳሌ ስሙ፡ የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፣ መጥመቂያም ማሰለት፣ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ።

ማቴዎስ 21:33

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል ታይቶ በማይታወቅ እጅግ ውበት በተላበሰና ቅብዓት በተሞላ መንገድ አስተምሯል። ልጆች መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ከተዉ ረጅም ጊዜም በኋላ እንኳ የእርሱን ምሳሌዎች ያስታውሷቸዋል። ትምህርቶቹ ካቀረባቸው ሁለት ሺህ ዓመታት በኋላም ተዛማጅነታቸው የተጠበቀ ነው።

የኢየሱስ ትምህርቶች በብዙ ሰዎች ተነባቢነትን፣ በብዙ ደራሲያን ተጠቃሽነትን፣ በብዙ ቋንቋዎች ተተረጓሚነትን ያገኙ፣ ብዙ ሙዚቃ የተሠራባቸውና ከሌሎች ማናቸውም ትምህርቶች በብዙ ሥነጥበባዊ ሥራዎችውክልና ያገኙ ናቸው።

አንድ ሰው እንዳለው፣ የሶቅራጥስን ትምህርቶች፣ የፕሌቶንና የአርስቶትልን ትምህርቶች ከክርስቶስ ትምህርቶች ጋር ማወዳደር አንድን ራእይ ከጥያቄ ጋር እንደማወዳደር ነው!

ከዓመታት በፊት ውዴን እንደ ኢየሱስ የቃሉ አስተማሪ ለመሆን እፈልጋለሁ አልኳት። "የኢሱስ ትምህርቶች በቀላሉ የሚረሱ አይደሉም፣ በልጆችም እንኳ ሳይቀር" ብዬ አሰብሁ። አሎስ ለመሆን





ወሰንሁ። መጋቢ ከመሆኔ ከዓመታት በፊት፣ ታሪኮችን መሠረት አድርጌ ለማስተማርና ለመስበክ ፈለግሁ።

ኢየሱስ ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሯል። እንዲህ ይል ነበር፡

*"አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት . . ."*

*"አንድ ሰው ታላቅ ግብዣ አደረገ . . ."*

*"ሐምራዊ ልብስ የለበሰ አንድ ሰው ነበር . . ."*

*"አንድ ሀብታም ሰው ሞተ . . ."*

*"አንድ ሰው ከኢያሪኮ ይሄድ ነበር . . ."*

*"አገልጋይ የነበረው አንድ ሀብታም ሰው ነበር . . ."*

*"የአንድ ሀብታም ሰው እርሻ ብዙ ምርት አስገኘ . . ."*

*"አንድ የከበረ ሰው ወደ ሩቅ አገር ሄደ . . ."*

እንደ ኢየሱስ ዓይነት አስተማሪ ለመሆን ፈለግሁ። ምንም ዓይነት አዲስ ነገር ለመሆን አልፈለግሁም፤ አሎስ ብቻ ለመሆን ፈለግሁ።

ታላቅ ሰባኪ የመሆን ቁልፉ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን መሆን ነው። የሰዎችን ሕይወት የሚነካ አገልግሎት ያለውን ሰባኪ ፈልግና የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን ሁን።

ልክ እንደ እርሱ በመሆን እንዴት መስበክ እንደምትችል ተማር። በአንድ ዓይነት መንገድ ስበክ፣ አስተምር ከዚያም በጣም ስኬታማ ትሆናለህ። ምንም አዲስ ነገር ስለሌለ አዲስ ነገር አትሞክር።

መልካም የሆነውን ነገር እንዴት አድርገህ በክብር "እንደምትገለብጥ፣ ፎቶ ቅጂ እንደምታደርግ፣ ፎቶውን እንደምትወስድ፣ ደጋግመህ እንደምትሰማ፣ ወደኋላ ተመልሰህ እንደምትሰማ፣ እንደምትደጋግም" ተማር።

በዚህ ጊዜ አሎስ ስትሆን ራስህን ታገኘዋለህ። ይህን አውቀህ አደረግህም አላደረግህም፣ እውነታው ግን የአንዱ ሰው አሎስነትህ

አይቀሬ መሆኑ ነው። ታዲያ የምታደንቀው ሰው አሉስ ለምን አትሆንም?

## 20. አሉስ መሆን፣ በሌሎች በርካታ የአገልግሎት ዘርፎች የአሉስ መርህ ምን እንደሆነ እንዲያውቅ ስለሚረዳው ልጅ አሉስ መሆን ያስፈልገዋል።

የአሉስን መርህ ስትረዳ በበርካታ የሕይወትና የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ እንደሚሠራ ታውቃለህ። አንተ የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን እንደመሆንህ፣ ሌሎች ነገሮችም የአንዱ ዓይነት ሌሎች ወገኖች መሆናቸውን ትገነዘባለህ።

ውድ ወዳጄ፣ አንተን ልዩ የሚያደርግ ምንም ነገር የለም። በአገልግሎት ስለሚገጥሙህ ችግሮች ምንም ልዩ ነገር የለም። ሌላ ሰው ከአንተ በፊት ገጥሞታል፣ የሚቀጥለው ሰው አንተ ነህ።

በራእይ መጽሐፍ፣ ዮሐንስ አስፈሪ አውሬ (ችግር) ከባሕር ውስጥ ሲወጣ አየ። የዚህ ልዩና አስፈሪ አውሬ መልክ በጣም አስፈራው።

> አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፣ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ። ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፣ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፣ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ።
>
> ራእይ 13፡1-3

ነገር ግን ይህ መጨረሻው አልነበረም። ወዲያውኑ አንድ አሉስ አየ! የአንዱ ዓይነት ሌላኛ ወገን! መጽሐፍ ቅዱስ የአንዱ ዓይነት ሌላ አውሬ ከውቅያኖስ ውስጥ ሲወጣ እንዴት እንዳየ ያስረዳል።

> ሌላም (አሉስ) አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፣ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት፣ እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።
>
> ራእይ 13፡11

አንድ ዓይነት ተፈጥሮ ያላቸው ችግሮች ሲነሡ ማወቁ አስፈላጊ ነው። ይህ ነገሮችን ተረጋግተህ እንድትወጣቸው ይረዳሃል።





አባሎቿ በእውነት በተባረኩባት አንድ ቤተክርስቲያን አንድ ጊዜ እሰብክ ነበር። የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢም በመልእክቱ በእውነት ተደስቶ ነበር። ይሁንና፣ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይህ መጋቢ በቤተ ክርስቲያኑ ስለተናገርኋቸው አንዳንድ ነገሮች ደስተኛ እንዳልነበረ ነገረኝ። ደነገጥሁ፣ ምክንያቱም መጀመሪያ ላይ በመልእክቴ እንደተደሰተ ነግሮኝ ነበር።

ይህ መጋቢ ጉዳዩን መዘርዘሩን ቀጠለና፣ ከመጋቢዎቹና ከምእመኑ መካከል አንዳንድ ሰዎች በእኔ ስብከት ደስተኞች እንዳልነበሩ ነገረኝ። በዚህ ጊዜ በጉባኤው የፖለቲካ መንፈስ በሥራ ላይ እንደነበር ማወቅ ቻልሁ። ቤተክርስቲያኒቱ ትመራ የነበረው በአሉባልታዎች፣ በቅዋሜዎችና በሐሜቶች ጉልበት ነበር። የተለያዩ ቡድኖችና አንጃዎች ሁልጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚሆነው ነገር አስተያየት ነበራቸው። በመከፋፈል፣ በፖለቲካና በውስጣዊ ሽኩቻዎች የተበጣጠቀች ቤተክርስቲያን ነበረች።

በሌላ ጊዜ፣ በሌላ ቦታ ስብከት አቀረብሁ። መጋቢው በጣም ስለተደሰተ ከመልእክቱ በኋላ እንኳን ደስ አለህ ብሎ አበረታታኝ።

በመቀጠል ብዙ ሕዝብ በሚገኝበት የእሑድ አገልግሎት ላይ ያንኑ መልእክት በቤተክርስቲያኑ ብሰብክለት እንደሚወድ ነገረኝ። መላው ቤተክርስቲያን መልእክቱን እንዲሰማ ፈለገ። ነገር ግን እኔ ለዚያ አገልግሎት እንደማልገኝለት ነገርሁት።

በሚቀጥለው ቀን ግን፣ ይህ መጋቢ ጠራኝና በመልእክቱ ውስጥ ስለተናገርኋቸው ነገሮች ገሠጸኝ። ደነገጥሁኝ፣ ነገር ግን ወዲያውኑ ስለተናገርኋቸው ስሕተት ነገሮች ይቅርታ ጠየቅሁ። ከተለያየን በኋላ ከመሪዎቹ አንዳንዶቹ በመልእክቴ የተወሰኑ ክፍሎች ላይ ተቃውሞ እንዳሰሙ ገለጸልኝ።

እኔም በዚህ ቤተክርስቲያንና ቀደም ሲል በነበርሁበት ፖለቲከኛ ቤተክርስቲያን መካከል ተመሳሳይነት እንዳለ ተገነዘብሁ። ስለሆነም በሆነው ነገር ብዙ አልተደነቅሁም። ይኸኛው ቤተክርስቲያን ለስብከቴ ግሣጼ ለተሰነዘረብኝ ሌላኛው ቤተክርስቲያን አሉስ ነበር።

በዚህም የአንዱን ዓይነት ሌላኛ ተሞክሮ እያየሁ ነበር፡፡ የሰሊሆም መጥመቂያ በተመሳሳይ ችግሮች ምክንያት በታመሙ ሰዎች የተከበበ ነበር፡፡

ድውዩም፣ ጌታ ሆይ፣ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም፡ ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው (አሎስ) ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት፡፡

ዮሐንስ 5፡7



## ምዕራፍ 15

# አንዳንድ ልጆች አባትን ማክበር ለምን እንደሚከብዳቸው

መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤

ኤፌሶን 6፡2-3

አባትህንና እናትህን አክብር፡ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡

ዘፀአት 20፡12

## 1. ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው ኢየሱስን ስለማይከተሉ ነው፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስን ይቀድመው ነበር፡፡ ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ በአገልግሎት ላይ ነበር፡፡ ጌታ በእርሱ እጅ ለመጠመቅ ራሱን በማቅረብ በብዙ አከበረው፡፡ ይህ ብዙ አገልጋዮች ለማድረግ የማይችሉት ነገር ነው፡፡ ከእነርሱ በፊት የነበረውን ሰው፣ በተለይ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ አያከብሩትም፡፡

## ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስን መናቅ ይችል የነበረባቸው ሰባት ምክንያቶች

1. ኢየሱስ መጥምቁን ዮሐንስ ሳለማክበር በቂ ምክንያቶች ነበሩት፡ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጀመሪያው ነበር፣ ሁሉም ነገሮች በእርሱ የተፈጠሩ ነበሩ፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ግን ከእግዚአብሔር ፍጥረታት አንዱ ነበር፡፡

**ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጎ ለተርታ ሰው መስገድና ራሱን ማስገዛት ቻለ?**

2. **መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ማጥመቅ ቀርቶ የጫማውን ማሰሪያ እንኳ ለመፍታት ብቃት አልነበረውም።**

ሕዝቡም ሲጠብቁ ሳሉ ሁሉም በልባቸው ስለ ዮሐንስ፣ ይህ ክርስቶስ ይሆንን? ብለው ሲያስቡ ነበር፤

ዮሐንስ መልሶ፡- እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤

መንሹም በእጁ ነው፣ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፣ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል አላቸው።

ሉቃስ 3፡15-17

3. **የዮሐንስ ሕይወት ሁኔታ አጠያያቂ ነገር ነበረ። የተቀዳደደ ቁምጣ ልብስ ለብሶ ይሰብክ ነበር፣ ደግሞም ኑሮው በምድረበዳ ነበር።**

በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፣ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረበዳ እየሰበከ መጣ።

በነቢዩ በኢሳይያስ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረበዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።

ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው፣ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ።

ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም፣ ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤

ማቴዎስ 3፡1-6

4. **መጥምቁ ዮሐንስ በጊዜው ከነበረው መንግሥት ጋር ግንባር ለግንባር የተፋጠጠ ስለነበር በፖለቲካ ውስጥ የተዘፈቀ ይመስል ነበር።**





5. **የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ያበቃው እንደ ወንጀለኛ በድንገት ሲገደል ነበር።**

**ነገር ግን ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስን አከበረው። እርሱን በመቀበል ወደ ቤተክርስቲያኑ ሄደለት። ኢየሱስ ለመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ራሱን ሰጠ።**

ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ዮሐንስ ግን፣ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፣ አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር። ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት።

ማቴዎስ 3፡13-15

6. **መጥምቁ ዮሐንስ ታምራዊ አገልግሎት አልነበረውም። ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ያልሠራቸውን ታምራት ቢያደርግም እንኳ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ በአክብሮት ተናግሯል።**

እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ፡- ምን ልታዩ ወደ ምድረበዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ፣ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ። ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፣ ከነቢይም የሚበልጠውን። እነሆ፣ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና።

ማቴዎስ 11፡7-10

7. **መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ኢየሱስ ያሉ ኃይለኛ ትምህርቶች አልነበሩትም። ኢየሱስ ከዮሐንስ የተለየ ዓይነት መልእክት ሰበኳል። ነገር ግን እንዲህም ሆኖ የመጥምቁ ዮሐንስን ታላቅነትና ተዛማጅነት እውቅና ሰጥቶታል።**

እውነት እላችኋለሁ፣ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።

ማቴዎስ 11፡11

**ኢየሱስ ለመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ራሱን ከሰጠ በኋላ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚል ድምፅ**

ከሰማያት መጣ። ኢየሱስ ይህን መጠሪያ - "ይህ የምወደው ልጄ ነው" የተሰኘውን በሚቀበልበት ወቅት አንድም ነፍስ አልማረከም ነበር! ያደረገው ነገር ቢኖር ከእርሱ በፊት ለነበረ ሰው ራሱን ማስገዛቱ ብቻ ነበር። ከእነርሱ ያረጀውን ወይም አንጋፋ የሆነውን የመዋጋት ጦስ ላለባቸው ሁሉ ይህ ጠቃሚ ነጥብ ነው።

## 2. ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው የንጉሥ ዳዊትን ምሳሌ ስለማይከተሉ ነው።

ንጉሥ ዳዊት ሳኦል ከእርሱ በፊት የመጣ የተቀባ ንጉሥ መሆኑን ተቀበለ። ምንም እንኳ ሳኦል ብዙ ችግሮች እያሉትም፣ ዳዊት አላጠቃውም። እንዲያውም"አባት" ብሎ ጠራው። ዳዊት ሳኦልን "የኢየሩሳሌሙ ዕብድ ብሎ አልጠራውም"። ይልቅ ጌታ የቀባው ብሎ ጠራው። "ጋኔን የሰፈረበት ንጉሥ" ወይም "ጋኔን የተቆራኘው አባባ" ብሎ አልጠራውም። የዳዊት መንግሥት ለዘላለም የሚጸናው ለዚህ ነበር።

> እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።
>
> ሉቃስ 1:32

ማናቸውም ተራ ልጅ በአባቱ ላይ እንዲያምፅ ምክንያት ሊሆኑለት የሚችሉ አራት ነገሮች በሳኦል ሕይወት ይታዩ ነበር። ነገር ግን ዳዊትየተሻለ ያውቅ ስለነበር ይህን አላደረገም። የዕድሜው ርዝማኔ ለአባቶች ከሚያሳየው አያያዝ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ በዘጸአት 20:12 ላይ ያለውን ቃል ያውቅ ነበር።

## ዳዊት ሳኦልን ላለማክበር አራት ምክንያቶች ነበሩት

### 1. ሳኦል በነቢዩ ሳሙኤል አማካኝነት በእግዚአብሔር ተጥሎ ነበር።

> . . . የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ . . .።
>
> 1 ሳሙኤል 15:23





### 2. ሳኦል በአጋንንት ተይዞ ነበር። በክፉ መናፍስት ቁጥጥር ሥር ነበር፣ ዳዊትም ይህን ሁኔታ ያውቅ ነበር።

> በነጋውም ሳኦልን ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው፤ በቤቱም ውስጥ ትንቢት ተናገረ። ዳዊትም በየቀኑ ያደርግ እንደነበረ በእጁ በገና ይመታ ነበር። ሳኦልም ጦሩን በእጁ ይዞ ነበር።
>
> 1 ሳሙኤል 18:10

### 3. ሳኦል መጋቢያንን ገድሏል። ነፍሰ ገዳይ ሆኖ ነበር፤ ተጠቂዎቹም ከእግዚአብሔር ካህናት በቀርሌሎች አልነበሩም።

> አብያታርም ሳኦል የእግዚአብሔርን ካህናት እንደፈጀ ለዳዊት ነገረው።
>
> 1 ሳሙኤል 22:21

### 4. ሳኦል በጠንቋይ እጅ ወደቀ። በምድር ላይ የመጨረሻ ሌሊቱ ያለፈው በጠንቋይ ቤት ነበር።

> ሳኦልም ባሪያዎቹን፦ ወደ እርስዋ ሄጄ እጠይቅ ዘንድ መናፍስትን የምትጠራ ሴት ፈልጉልኝ አላቸው። ባሪያዎቹም፤ እነሆ፣ መናፍስትን የምትጠራ አንዲት ሴት በዓይንዶር አለች አሉት።
>
> 1 ሳሙኤል 28:7

በብዙ ቢገፋፋትም ዳዊት በሳኦል ላይ የነበረውን አቋም እንደጠበቀ ጸንቷል። እንደ አባት እንጂ እንደ ሌላ ላለማየት ወሰነ። በአባቶች ላይ በሚያዩት ስሕተት ቁጣ የተሞላበት ጥቃት የሚያካሂዱ ብዙ ጅል ሰዎች አሉ። መንግሥቱ ለዘላለም ከጸናለት ዳዊት ለምን አንማርም? በአባት ላይ ለማመፅ ዳዊት ከነበረው፣ የተሻሉ ጥሩ ምክንያቶች እንደማይኖሩህ እርግጠኛ ነው!

> ደግሞም፣ *አባቴ ሆይ፣* የልብስህ ዘርፍ በእጄ እንዳለ ተመልከትህ እወቅ፡ የልብስህንም ዘርፍ በቆረጥሁ ጊዜ አልገደልሁህም፤ ስለዚህም በእጄ ክፋትና በደል እንደሌለ፤ አንተም ነፍሴን ልትወስድ ምንም ብታሳድደኝ እንዳልበደልሁህ ተመልከትህ እወቅ።
>
> 1 ሳሙኤል 24:11

### 3. ሰዎች ልባቸው ከአባቶች የራቀ ስለሆነ አባቶችን ማክበር ይከብዳቸዋል፡፡

*መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፡፡*

ሚልክያስ 4:6

ልጆች አባቶቻቸው የሚያደርጉት ነገር የማያስደስታቸው ጊዜያት አሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ ልጆች የሚያስደስቷቸው አባቶቻቸው ከሚያደርጉት ግንባር-ገጠም ተቃራኒ ነገሮች ናቸው፡፡ ታዲያ ወደ እርግማን የሚወስደው ይህ ሁኔታ ነው፡፡ የዚህ ሁኔታ በርካታ ምሳሌዎች አሉ፡፡

ለምሳሌ፣ አባት የዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር ከሆነ፣ ልጅ በልቡ ውስጥ፣ "እኔ የዩኒቨርስቲ ሌክቸረር መሆን አልፈልግም" ሊል ይችላል፡፡ አባት ፖለቲከኛ ከሆነና የልጅም ልብ ከአባቱ ሸፍቶ ከሆነ፣ ልጅ ምንም ዓይነት ግንኙነት ከፖለቲካ ጋር እንዳይኖረው በምስጢር እየወሰነ ያድጋል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ አባት በአገልግሎት መጋቢ ሊሆን ይችላል፣ ልጅ ደግሞ "እኔ የሕግ ሰው፣ ወይም የጠፈር ሊቅ እንጂ መጋቢ መሆን አልፈልግም" ይላል፡፡ እነዚህ ሁሉ የልጆች ልብ ከአባቶች የመሸፈቱ ውጤቶች ናቸው፡፡

ልቡ ወደ አባቱ እንዲመለስ ለልጅህ መጸለይ አስፈላጊ ነው፡፡ የልጆች ልብ ከአባቶቻቸው የሸፈተ ከሆነ፣ እንዳፈለጋቸው የሚያደርጉና ዓመፀኞች ይሆናሉ፡፡

## የመጋቢው ሴት ልጅ

አንድ ጊዜ በአንድ መጋቢ ቤት ተገኝቼ ነበረና ከሴት ልጁ ጋር ንግግር ጀመርሁ፡፡ ከእርሷ ጋር ስጫወት ሳለሁ፣ እንዴት የሕግ ድግሪዋን እያጠናች እንዳለች ነገረችኝ፡፡ እቅዷ በንግድ ማኅበራት በተወሳሰበች ዓለም ውስጥ የንግድ ሥራ መሥራት ነበር፡፡ በዚህ





ጊዜ አባቷ በሺዎች የሚቆጠሩአባላት ባሉበት አንድ ታላቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ በመጋቢነት ያገለግል ነበር፡፡ እርሷ ግን እርሱ በሚያደርገው ነገር ፍላጎት አላደረባትም፡፡

ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ ወደዚያ ከተማ ተመልሼ መጣሁና በዚሁ መጋቢ ሴት ልጅ አማካኝነት በከተማ ውስጥ በመኪና እዘዋወር ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ይህች ልጅ ትናገር የነበረው ሁሉ ስለ አገልግሎት ነበር፡፡ ስለ ሕግ የነበራት ሕልሞቿ ወዴት እንደበነኑ ገረመኝ፡፡ በወቅቱ ስለ ንግዱ ዓለም ምንም ንግግር አልነበረም፡፡ ነገሩ እግዚአብሔርና የራሱ ሥራ መሆኑ ነበር፡፡

ስለዚህ "ተለውጠሻል! እግዚአብሔርንና አገልግሎትን በተመለከተ እውነተኛ ለውጥ በአንቺ ላይ መጥቷል" አልኋት፡፡ እንደገና መልሼ፣ "ተለውጠሻል አይደል?" ብዬ ጠየቅኋት፡፡

እርሷም፣ "አዎን፣ ተለውጫለሁ" ስትል መለሰች፡፡

እኔም፣ "ገና ከአንቺ ጋር እንደተገናኘሁ ነገሩን አውቄዋለሁ፡፡ እዚህ በነበርሁ ባለፈው ጊዜ አሁን ከሆንሺው በጣም የተለየሽ ነበርሽ" አልኋት፡፡

"እውነት ነው" ስትል ተስማማች፡፡

ከዚያም፣ "ሁልጊዜ ከአገልግሎት ሕይወት ለመራቅ እፈልግ ነበር፡፡ በአገልግሎቱ ምክንያት ቤተሰባችን በብዙ ተሠቃይቷል፡፡ የማደርገው ነገር ቢኖር ከአባቴ ጋር መጓዝና በአገልግሎቱ እርሱን መርዳት ነበር" አለች፡፡

ነገር ግን እኔ ምን እንደደረሰባት ገባኝ፡፡ እግዚአብሔር እርግማንን ለማስወገድ የልጅን ልብ ወደ አባት ለውጧል፡፡ ልብን መመለስ መንፈሳዊ ነገር ሲሆን ይህን የሚያደርገውም እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው መጸለያቸው ተፈላጊ ነገር ነው፡፡ አለበለዚያ ልባቸው መልካም ከሆነው ሁሉና ወላጆች ከሚመክሩት ሊሸፍት ይችላል፡፡

## የአባትን ልብ መመለስ

አባት ለልጆቹ ፍላጎት የሚያጣባቸው ጊዜያትም አሉ። ይህ ብዙ ጊዜ የሚሆነው አባት ሲጎዳ ወይም ስለ ልጆቹ ትክክል ማየት ሲሳነው ነው። በዚህ ጊዜ ያለ ምንም አባታዊ ድጋፍ ስለሚሆኑ ሁኔታውበልጆቹ ላይ እርግማንን ያስከትላል።

አንድ ቀን፣ ከተባባሪ መጋቢዎቼ ለተወሰኑ ዓመታት በውጭ አገር የነበረ አንዱ ተመልሶ መጣ። አገሪቱን ለቆ ከመሄዱ በፊት፣ ለአንድ መጋቢ ምስጢር አጫውቶ ነበር። "ቄሱ በአንዳንዶቻችን ላይ ፍላጎት ያጣ መስሎኛል። ቀደም ሲል ለእኛ የነበረው ፍላጎት አሁን የሌለ ሆኖ ይሰማኛል" አለ።

ነገሩን በእንዲህ ያለ ፍጥነት ማወቁ ገረመኝ፣ ምክንያቱም የተናገረው ትክክል ነበር። በእነርሱ ላይ የነበረኝ ፍላጎቴ ስለተሟጠጠ በአንዳንዶቹ መጋቢዎች ግራ ተጋብቼና አዝኜ ነበር። ለስብሰባ አልጠራቸው፣ ብዙም አላናግራቸው ነበር። ለሁሉም ሰው ፈገግ እየመገብሁ፣ "ተባረክ!" እል ነበር። ነገር ግን ከማናቸውም ጋር ጥልቅና ቁምነገር ወዳዘለ ውይይት ውስጥ ለመግባት አልፈቅድም ነበር። አየህ ልቤ ከእነዚህ መጋቢዎች ሸፍቶ ነበር።

ነገር ግን እግዚአብሔር ልቤን እንደገና ወደ እነርሱ መመለስ ጀመረ። እንድጸልይላቸው አደረገኝና ቀስ በቀስ ለእነዚህ መጋቢዎች የነበረኝን ፍቅርና ፍላጎት መልሼ ማግኘት ቻልሁ። ከዚያ በኋላ የአባት ልብ ከልጆቹ መመለሱ ምን ማለት እንደሆነ እፍታውን መቅመስ ቻልሁ። በእርግጥ እንዲህ ያለ ነገር አደገኛና እርግማን የሚጋብዝ ነው።





4. ሰዎች አባትን ማክበር የሚከብዳቸው አባት የሚከበር ሆኖ በመገኘት የእነርሱን አክብሮት እንዲቀበል ስለሚሰማቸው ነው።

ብዙ ወንድና ሴት ልጆች በአባትና በእናታቸው ሕይወት የሚያዝኑ መሆናቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ በወላጆቻቸው ጋብቻ ያዝናሉ።

ብዙ ልጆች ወላጆቻቸው ገንዘብን፣ ግንኙነቶችንና ሌሎች የሕይወት እድሎችን አስመልክቶ ካደረጉት የተሻለ እናደርጋለን ብለው ያስባሉ። እንዲያውም አንዳንዶች የራሳቸውን ልጆች ወላጆቻቸው ለእነርሱ ካደረጉት በተሻለ እንክባከባለን ብለውም ያስባሉ።

ብዙዎቹ ወላጆች ከዓይነተኛ አባትነትና እናትነት መጉደላቸው እውነት ነው። እያንዳንዱ ወላጅ ሊሆን የተመኘውን ያህል መሆን ችሏል። ወላጆች እንደ ማንም ሰዎች ናቸው። ሕይወታቸው በግላጭ ስለሚታይ አባቶች ለነቀፋ የተጋለጡ ናቸው።

በተጨማሪ "ፍጹም ያልሆነ" አባት "ፍጹም" የሆነ ልጅ ወደ ዓለም ማምጣጥ መቻሉና ጥሩ ሰው ደግሞ ክፉ ሰው ወደ ዓለም ማምጣቱ እውነት ነው። ለምሳሌ፣ ሂትለርና ስታሊን ወደ ቤተክርስቲያን የሚወስዷቸው እናቶች የነበሯቸው ሰዎች ናቸው።

ስታሊን እንዲያውም ለተወሰነ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ ተምሯል። የእነዚህ ጅምላ ገዳዮች ወላጆች ቤተክርስቲያን አዘውታሪዎችና ክርስቲያኖች እንደነበሩ ግልጽ ነው። በማይታወቅ መንገድ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ሞት የሚያስፈጽሙ ልጆችን ወደ ዓለም ይዘው መጡ።

የብዙ "መልካም" ሰዎች ወላጆች "መልካሞች" እንዳልነበሩ እግዚአብሔር ያውቃል። እንዲህም ሆኖ አባቶችና እናቶች እንዲከበሩ ጥቅል ትእዛዝ ሰጠ። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሕይወትና በአገልግሎት ሊልቁ ለሚችሉ ሰዎች ራሱን እንደ እንቅፋት ያስቀምጣል።

ገሃድ የሆነው ነገር የአባቶች የሞራል፣ የንዋይና የጋብቻ ውድቀቶች እግዚአብሔር እንድንሰጣቸው ካዘዘን ክብር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ ነው።

እግዚአብሔር አባቶችን ስለ ሞራላዊ፣ ንዋያዊና ትዳራዊ ኃጢአቶቻቸው ሊቀጣ ከፈለገ፣ ያደርገዋል። ይህ ልጅ ለአባቱ እንዲያደርግ ከሚጠበቅበት ክብር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

ኢየሱስ፣ "የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ" ማለቱን አስታውስ። እያንዳንዱ አባት ማንም ይሁን፣ በእግዚአብሔር ለእርሱ እንዲሰጥ የታዘዘለትን ክብር ማግኘት ይገባዋል። ቄሣር ለእርሱ የሚገባውን ግብር በመቀበሉ እግዚአብሔር ምንም አይጎድልበትም። ኢየሱስ ሰዎች ለቄሣር ግብር መክፈልን እንዲቀጥሉ የተናገረው ለዚህ ነበር።

አባቶች ለእነርሱ የሚገባውን ክብር በማግኘታቸው የእግዚአብሔር መንግሥት የሚጎድልበት ምንም ነገር የለም። አባት ክብርን ሲያገኝ የእግዚአብሔር መንግሥት ሞራል፣ ቅድስናና ጽድቅ ተመቻመቸ ማለት አይደለም።

ብዙ ሰዎች የአባቶችን ኃጢአት በተመለከተ"እጅግ ጻድቃን"፣ ግለ-ጻድቃንና ፈራጆች ናቸው። የአባቶቻቸውን ስሕተቶች፣ ጉድለቶችና ግልጽ ኃጢአቶች የሚገባቸውን ክብር ለመንፈግ እንደ ምክንያት ይጠቀማሉ።

እንደ ፈሪሳውያን ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ሕጎች አንዱ ከአንዱ የማይገናኝ አድርገው ያያሉ። በሌላ አነጋገር፣ አባት ማናቸውንም ዓይነት ኃጢአቶች እየፈጸመ እያለ፣የሞራል መለኪያን ጠብቀህ ለአባት ክብርን መስጠት አትችልም ማለታቸው ነው።

ፍጹም አባቶች ብቻ ክብርን የሚያገኙ ቢሆን ኖሮ፣ በዚህ ምድር ላይ ፍጹም የሆነ አባት ስለሌለ የአምስተኛ ትእዛዝ፣ (አባትህን . . . አክብር) አስፈላጊ ባልሆነ ነበር!





5. ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው በአምስተኛው ትእዛዝ ላይ ጭማሪ ስለሚያደርጉ ነው።

አምስተኛውን ትእዛዝ በጥሞና ብትከታተል፣ ማክብር የሚገባህን እናት ወይም አባት ዓይነት እንደማይገልጽ ትረዳለህ።

የሚናገረው እንዲሁ አባትህንና እናትህን እንድታከብር ብቻ ነው። ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌለ ነገር በመጨመር፣ ለመታዘዝ የማይቻል ያደርጉታል። ሰዎች በአምስተኛው ትእዛዝ ላይ እንዴት እንደሚጨምሩ እዚህ ላይ ጥቂት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡

ሀ) ሰዎች አባቶችን ለማክበር የሚከብዳቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "መልካም እንዲሆንልህና በምድር ላይ ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *ፍጹም የሆነውን አባትህን* አክብር" ይላል ብለው ስለሚያስቡ ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚለው ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር"አባትህንና እናትህን አክብርነው።

ለ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ "መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ላይ ረጅም ዕድሜ እንዲኖርህ *ሀብታም የሆነውን አባትህን* አክብር" ብሎ ይናገራል ብለው ስለሚያስቡ ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንዲኖርህ አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

ሐ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *ለእናትህ ጥሩ ባል የሆነውን አባትህን* አክብር" የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚለው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

መ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ“. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ላይ ረጅም ዕድሜ እንዲኖርህ *የትምህርት ቤት ክፍያዎችህን የሚከፍልልህን አባትህን* አክብር”ይላል ብለው ስለሚያስቡ ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ሠ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንዲኖርህ*እናትህን ያልፈታውን አባት* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ረ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *አንድ ሚስት ያለውን አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚለው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ሰ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *ከአንዲት እናት ብቻ ልጆች ያለውን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።





ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ሸ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *በኃጢአት ያልወደቀውን አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ቀ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ሁልጊዜ በቤት የሚገኘውን አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

በ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ለቤተሰቡ ቤት የሠራ አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ተ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ርስትን የተወልህን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ቸ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ከልጆቹ ሁሉ ጋር መልካም ግንኙነት ያለውንአባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ኀ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ምንም ድካም የሌለውን አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ነ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ብዙ ገንዘብ ያለውን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ኘ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“በሕይወቱ ብዙ ስኬት ያገኘውን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።





ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

አ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“ታላቅ ሰው የነበረውን አባትህን* አክብር”የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ከ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“በሕይወትህ ታላቅ ሚና የተጫወተውን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ኸ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“እንደ ልጁ የተቀበለህን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር” ነው።

ወ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ “. . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *“አብረኸው የኖርኸውን አባትህን* አክብር” የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

ዐ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *"ያልተቆጣህንና ያልገሠጸህን አባትህን* አክብር*"* የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

ዘ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *"ብዙ ገንዘብ የሰጠህን አባትህን* አክብር*"* የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

ዠ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *"ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አባትህን* አክብር*"* ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

የ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *"ማይም ያልሆነ አባትህን* አክብር*"* የሚል ስለሚመስላቸው ነው።





ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

ደ) ሰዎች አባቶችን ማክበር የሚከብዳቸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር *"ጠንቋይ ያልሆነ አባትህን* አክብር*"* የሚል ስለሚመስላቸው ነው።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚናገረው፡ ". . . መልካም እንዲሆንልህና በምድርም ረጅም ዕድሜ እንድትኖር አባትህንና እናትህን አክብር" ነው።

በእርግጥ አባቶችን ማክበርና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ መንፈሳዊ ተግባር ነው። ይህ ለተፈጥሮአዊው ሰው ትርጉም ላይሰጥ ይችላል፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታላላቅ መርሆች አንዱ ነው። በዚህ አምስተኛ ትእዛዝ፣ መላው የሰው ዘር መነሣትና መውደቅ ይችላል።

በዚህ አባትና እናትህን በምታከብርበት አምስተኛ ትእዛዝ ሁሉም አገልግሎቶች ሊነሡና ሊወድቁ ይችላሉ።

አባቶችን የማክበር ጽንሰ-ሃሳብ መታገል አይሁንብህ!

አንድ ቀን ክብርን ትቀበል ዘንድ ሌሎችን ማክበር ይሁንልህ!

አንድ ቀን መልካም አባት ትሆን ዘንድ መልካም ልጅ ያድርግህ!

# በዳግ ሂዋርድ-ሚልስ የተጻፉ ሌሎች መጽሐፍት

## የታማኝነትና ታማኝ አለመሆን ርዕሶች

- አባቶች እና ታማኝነት
- መሪዎችና ታማኝነት
- ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን
- የሚወነጅሉህ
- ዝንጉዎች
- ትተውህ የሚሄዱ
- አስመሳዮች

## የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ርዕሶች

- የቤተ ክርስቲያን እድገት
- ቤተ ክርስቲያን መትከል
- ሜጋ ቤተ ክርስቲያን(2ኛ እትም)

## የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ርዕሶች

- ቅባቱን ያዝ
- በምልክቶች እና በድንቆች ማገልገል
- ወደ ቅባቱ የሚያደርሱ እርምጃዎች

## የስኬት ርዕሶች

- አሥራት የማይከፍሉ ክርስቲያኖች ለምን ይደኸያሉ . . . እና አሥራት የሚከፍሉ ክርስቲያኖች እንዴት ሀብታም እንደሚሆኑ

## የመጋቢነት አገልግሎት ርዕሶች

- የአመራር ጥበብ 2ኛ እትም
- የእረኝነት ጥበብ
- የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ

## የክርስቲያን ሕይወት ርዕሶች

- ወደኃላ ማፈግፈግ
- የጋብቻ ሞዴል
- ልጄ ሆይ፣ ትችያለሽ
- ኢጋንንቶች እና እንዴት እነርሱን ማሸነፍ እንደሚቻል
- ሰይመው! ይገባኛል በል! ውሰደው!
- የጥሞና ጊዜ
- ንገራቸው!

## የአገልግሎት ሥራ ርዕሶች

- በእግዚአብሔር ፍጹም ፍቃድ ውስጥ መሆን እንዴት እንደሚቻል
- ማጣት፣ መከራ መቀበል፣ መሥዋዕት መሆን፣ መሞት
- የተጠሩ ብዙዎች ናቸው
- ፕሩቶን
- የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሕግጋት
- የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሕግጋት